# ኤርምያስና መልእክቱ

## መግቢያ

ትምህርቶቹ የቀረቡት እናንተ የምትፈልጉትን መምረጥ በሚያስችላችሁ ሁኔታ ነው። መጽሐፉንም በቀጥታ ምዕራፍ በምዕራፍ መዝለቅ ከፈለጋችሁ ምንም አያስቸግራችሁም። የአሁኑ ዝግጅት፡-

ሀ. ትምህርት 1-5፡- የተደረገው ምን እንደሆነና

ለ. ትምህርት 6-9፡- ለምን እንደተደረገ ያሳየናል

እያንዳንዱ ትምህርት ሰባት ክፍሎች አሉት። ለእያንዳንዱም ክፍል ታሪካዊ የሆኑ መሠረታዊ ነጥቦች ለማቅረብ ተሞክሯል። ቀጥሎም ነቢዩ በዚህ ክፍል ውስጥ የሰጠውን መልእክት እንመለከታለን። ከዚያም በሦስተኛ ደረጃ የምዕራፎቹን ግብራሪያ አቅርበን በአራተኛ ደረጃ የምዕራፎቹን ልዩ ጠቃሚ ነጥቦች እንጠቁማለን። በአምስተኛ ደረጃ ደግሞ በምዕራፎቹ ውስጥ የምናገኛቸውን ትምህርቶች በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ በሌላ ስፍራ ከሚገኙት ትምህርቶች ጋር እናዛምዳቸዋለን። ከዚያም በመቀጠል የክለሳ ጥያቄዎችን አቅርበን በመጨረሻ ላይም ለማመሳከሪያ ሊረዳ ይችላል ብለን ያሰብነውን ለክፍሉ የተዘጋጀ ማውጫ አቅርበናል።

አጠቃላይ መጽሐፉ ስለምን እንደሚናገር ጠቅለል ያለ ሐሳብ ግግኘት እንድትችሉ ከትምህርት አሥር መጀመር ሳይጠቅማችሁ አይቀርም። ይህንን ትምህርት መልሶ መላልሶ ለማጥናት አስፈላጊ ነው፤ ምክንያቱም ደጋግማችሁ በምታጠኑበት ወቅት ከጊዜ ወደ ጊዜ ግልጽ እየሆነላችሁ ይሄዳል።

ሌላው መታወስ የሚኖርበት በጣም ጠቃሚ የሆነው ነጥብ፡- ይህ መጽሐፍ ዋናው የመማሪያ መጽሐፋችሁ እንዳልሆነ ነው። ዋናው የመመሪያ መጽሐፋችሁ መጽሐፍ ቅዱስ ነው። ይህ መጽሐፍ ግን የተዘጋጀው መጽሐፍ ቅዱሳችሁን በደንብ እንድታውቁ ለመርዳት ነው። ስለዚህ ይህንን መጽሐፍ ማጥናት ከመጀመራችሁ በፊት ለእያንዳንዱ ክፍል የተመደቡትን ምዕራፎች ከመጽሐፍ ቅዱሳችሁ አንብቡ።

ይህ መጽሐፍ ትንቢተ ኤርምያስን ለመረዳት የሚያስችል የመጀመሪያው እርምጃ ብቻ ነው። ስለዚህ ለትንቢተ ኤርምያስ ጥናት ብቻ የሚያገለግል የግል ማስታወሻ ደብተር ገዝታችሁ የራሳችሁን ማስታወሻ ውሰዱ። ምክንያቱም ለመማር አማራጭ የሌለው መንገድ ይህ ነው።

ትምህርት አንድ፡- ኤር. 1 እና 52

ይህ ትምህርት በ627 ዓ.ዓ. ኤርሚያስ ነቢይ
እንዲሆን መጠራቱን፡ በ586 ዓ.ዓ. ደግሞ
ትንቢቱ መፈጸሙን ይነግረናል። . . . . . 3

ትምህርት ሁለት፡- ኤር. 46-51

ኢየሩሳሌም የተደመሰሰችው በ586 ዓ.ዓ. ነበር።
ይህም ትምህርት የሚነግረን ከዚያ በኋላ ምን
እንደተደረገ ነው። . . . . . 10

ትምህርት ሦስት፡- ኤር. 26-32

ሕዝቡ ከነከተማቸው መትረፍ እንዲችሉ
ኤርምያስ ንስሐ ግቡ በማለት ይማፀናቸዋል። . . . . . 20

ትምህርት አራት፡- ኤር. 33-39

ሕዝቡ የተላከላቸውን መልእክተኛ ሊገድሉት
ቢፈልጉም የእግዚአብሔር የተስፋ ቃሎች
ግን አይሻሩም። . . . . . 29

ትምህርት አምስት፡- ኤር. 40-45

የማይታዘዝ ሕዝብ የሚቀበለው ነገር ቢኖር
ፍርድ ብቻ ነው። ስለዚህ በዚህም ስፍራ
የምናነበው ስለ ኢየሩሳሌም ውድቀት ነው። . . . . . 37

ትምህርት ስድስት፡- ኤር. 2-6

ስለሚፈጸመው ነገር ሁሉ ተጠያቂዋ ይሁዳ ናት።
ኤርምያስ በዚህም ክፍል የሕዝቡን ኃጢአተኝነት
ይጠቁማል። . . . . . 44

ትምህርት ሰባት፡- ኤር. 7-12

ሕዝቡ እግዚአብሔር ከኛ ጋር ቃል ኪዳን
ስለ መሠረተ ምንም ችግር አይደርስብንም
በማለት ለመከራከር ሲሞክሩ የሚያሳይ ነው። . . . . . 52

ትምህርት ስምንት፡- ኤር. 13-18

ቤተ መቅደስ እንዳላቸውና እንደሚያድናቸውም
በመከራከር የባሕሪያቸው መልካምነት ይናገራሉ። . . . . . 61

ትምህርት ዘጠኝ፡- ኤር. 19-25

ይህ ትምህርት የሚናገረው ስለ ይሁዳ ነቢያት፥
ካህናትና ነገሥታት ነው። በመሠረቱ ከነዚህ ሰዎች
የሚጠበቀው መመሪያ መስጠት ነበር፤ በዚህ ፈንታ
ግን ራሳቸው ኤርምያስን ተቃወሙት። . . . . . 69

ትምህርት አሥር፡- ማጠቃለያ

ይህ ትምህርት 52ቱንም ምዕራፎች የሚሸፍንና
አጠቃላይ የሆነ አጭር ጥናት የሚያቀርብ ነው። . . . . . 77




ትምህርት አሥር፡

2-6፡ ትምህርት ስድስት

7-12፡ ትምህርት ሰባት

13-18፡ ትምህርት ስምንት

19-25፡ ትምህርት ዘጠኝ

ትምህርት አንድ

26-32፡ ትምህርት ሦስት

33-39፡ ትምህርት አራት

40-45፡ ትምህርት አምስት

46-51፡ ትምህርት ሁለት

# የትንቢተ ኤርምያስ የዘመን ቅደም ተከተል ቻርት

650 ዓመተ ዓለም፡- የኤርምያስ ልደት (በግምት)

648 ዓመተ ዓለም፡- የኢዮስያስ ልደት

641 ዓመተ ዓለም፡- ዓሞን የዳዊትን ዙፋን ወረሰ

640 ዓመተ ዓለም፡- ኢዮስያስ በዙፋኑ ላይ ተተካ

632 ዓመተ ዓለም፡- ኢዮስያስ እግዚአብሔርን መከተል ጀመረ፤ 2ኛ ዜና 34፡3

628 ዓመተ ዓለም፡- ኢዮስያስ ተሐድሶ ጀመረ

627 ዓመተ ዓለም፡- ኤርምያስ ለነቢያት አገልግሎት ተጠራ

626 ዓመተ ዓለም፡- ናቦፓላሳር የባቢሎንን ዙፋን ወረሰ

622 ዓመተ ዓለም፡- የአሪት መጽሐፍ በቤተ መቅደሱ ውስጥ ተገኘ፥
- ፋሲካ ተከበረ

612 ዓመተ ዓለም፡- ነነዌ ወደቀች

609 ዓመተ ዓለም፡- ኢዮስያስ ተገደለ- ኢዮአክስ ለሦስት ወራት ነገሠ

- የአምር - ግብፅ ሠራዊት ካራንን ለቆ ወደ ከርከሚሽ አፈገፈገ

- በይሁዳ ኢዮአቄም በኢዮአክስ ቦታ ተተካ

605 ዓመተ ዓለም፡- በዓመቱ መጀመሪያ ላይ ከከርከሚሽ የመጡ ግብፃውያን ባቢሎንን በቁራጣቲ አሸነፉ

- የይሁዳ መጀመሪያ ምርኮ

- ኢዮአቄም ከባቢሎን ጋር ጎብረት ለመፍጠር ተዋዋለ

- ናቡከደነፆር የባቢሎንን ዙፋን ወረሰ

601 ዓመተ ዓለም፡- በባቢሎናውያንና በግብፃዊያን መካከል ውጤት አልባ ውጊያ ተደረገ

598 ዓመተ ዓለም፡- ኢዮአቄም ሞተ

- ኢየሩሳሌም ተከበበች

597 ዓመተ ዓለም፡- የአኪን ሦስት ወራት ከነገሠ በኋላ ተማረከ

- የይሁዳ ሁለተኛ ምርኮ
- ሴዴቅያስ ነገሠ

588 ዓመተ ዓለም፡- ጥር 15 ቀን ኢየሩሳሌም ተከበበች

- ሆፍራ የግብፅን ዙፋን ወረሰ

586 ዓመተ ዓለም፡- ሐምሌ 19 ቀን ባቢሎናውያን ኢየሩሳሌምን ወረሩ

- ነሐሴ 15 ቀን ቤተ መቅደሱ ተቃጠለ
- ነዶልያስ ተገደለ
- ወደ ግብፅ መሰደድ

## ክፍል አንድ፡- ኤር. 1ና 52

### ንዑስ ክፍል አንድ፡- ታሪካዊ አቀማመጥ

1. 627 ዓመተ ዓለም ኢዮስያስ የነገሠበት 13ኛ ዓመቱ ሲሆን ኤርምያስም አገልግሎቱን እንዲጀምር የተጠራበት ዘመን ነበር። ኢሳይያስ ከሞተ በኋላ ምናልባትም ከምናሴ ዘመነ መንግሥት ከ687 ዓመተ ዓለም ገደማ አንሥቶ እስከዚህ ዘመን ድረስ ምንም ነቢይ አልተነሣም ነበር። በዚህ ረዘም ባለ ከስልሳ ዓመታት በሚበልጥ ጊዜ ውስጥም በይሁዳ ሁለት እጅግ ኃጢአተኛ የሆኑ ነገሥታት ነግሠዋል። እነርሱም ምናሴና ዓሞን ነበሩ። የይሁዳ ሕዝብም እግዚአብሔር ረስቶናል ብለው ያሰቡበት ጊዜ ነበር። በእንድ በኩል ሲታይ ይህ እውነት ነበር ምክንያቱም የኃጢአታቸው ብዛት እግዚአብሔር እነርሱን ለፍርድ አሳልፎ እንዲሰጣቸው አድርጎት ነበርና ነው።

| | |
|---|---|
| ኢሳይያስ ሞተ | ሕዝቅያስ 687 ዓመተ ዓለም |
| | ምናሴ |
| በይሁዳ ምንም | ዓሞን |
| ነቢይ አልነበረም | |
| | ኢዮስያስ |
| ኤርምያስተጠራ | 627 ዓመተዓለም |

2. የኢዮስያስ አባት ዓሞን እጅግ ኃጢአተኛ ሰው ቢሆንም እንኳ ልጁ ኢዮስያስ ግን በተቃራኒው እግዚአብሔርን እንዲከተል ለማድረግ ብርቱ ጥረት አድርጓል። ይህንንም የሚያመለክት ታሪክ በ2ኛ ነገ. 21-23 ውስጥ ቀርቧል። ኢዮስያስ ብዙ ውጫዊ ተሐድሶ ቢያደርግም እንኳ የሕዝቡ ልብ እንዳልተለወጠ ግልጽ ነበር። ኤርምያስም 627 ዓመተ ዓለም ጀምሮ ኢየሩሳሌም እስከወደቀችበት ዘመን እስከ 586 ዓመተ ዓለም ድረስ እና ከዚያም በኋላ አገልግሎቱን አላቋረጠም ነበር። በዚህ ሁሉ አገልግሎቱም ከ40 ዓመታት በላይ በግልጽ እንደመጣ ይታይ ከነበረው የእግዚአብሔር ፍርድ እንዲያመልጡ የኢየሩሳሌምንና የይሁዳን ሕዝብ ንስሐ እንዲገቡ ያሳስባቸው ነበር።

3. ስለዚህ ዘመን ትንቢት ይናገሩ የነበሩት ሰዎች በሙሉ የትንቢቶቻቸውን ፍጻሜ በዓይናቸው ተመልከተዋል። ምናልባትም ሰፎንያስ ኢየሩሳሌም ስትደመሰስ በሕይወት ሳይኖር አይቀርም። ሕዝቅኤልም በባቢሎን ነበር። እርሱ ትንቢቱን ሲናገር የሰሙት ሰዎች የከተማይቱን መደምሰስ እንዲሁም የአብዛኛው ሕዝብ በምርኮ ወደ ባቢሎን መወሰድ በዓይናቸው ተመልከተዋል። ኤርምያስም ናቡከደነፆር እና ሠራዊቱ ከተማይቱን በወረሩበት ወቅት እዚያው ስለነበረ የከተማይቱን መደምሰስ ተመልክቷል። ኤርምያስም ከእግዚአብሔር የተላከ ነቢይ ለመሆኑ ይህ እያንዳንዱ ሰው ሊከደው የማይችል ጉልህ ማረጋገጫ ሆኗል። እርሱ የተናገረውም ነገር እያንዳንዱ ፍጻሜ አግኝቷል።

## ንዑስ ክፍል ሁለት፡ - የነቢዩ ሽክም

1. ኤርምያስ ወደፊት የሚሆነው ነገር ምንድነው? ለሚለው ጥያቄ መልስ ሰጥቷል። ሰማርያ በ722 ዓመተ ዓለም የተደመሰሰች ሲሆን ይሁዳ ግን ከባቢሎን ከሚደርስባት ጥቃት እንዳመለጠች አድርጋ ታስብ ነበር። ኢሳይያስን የመሳሰሉት ሌሎች ነቢያት ግን የእግዚአብሔር ቃል ኪዳን ከባድ ውጤቶችን ቢያስከትልም እንኳ ሊታጠፍ እንደማይችል ይሁዳን አስጠንቅቀት ነበር። እግዚአብሔር

በመምጣት ላይ የነበረው ወረራ ፍጹም እንደማይቀር በኤርሚያስ አማካኝነት አሳስቧቸዋል። እግዚአብሔር እራሱ የባቢሎናውያንን ሠራዊት በይሁዳና በኢየሩሳሌም ከተማ ላይ እንደሚያመጣባቸው ተናግሯቸዋል። ይህም ነገር በግልጽ ተግባራዊ እስኪሆን ድረስ ሕዝቡ እውነት መስሎ አይታያቸውም ነበር።

2. ሕዝቡን በጣም ግራ ያጋባቸው ነገር ይህ ሁኔታ የሚፈጸመው ለምንድነው? የሚለው ጥያቄ ነበር። የእግዚአብሔርን ቃል ኪዳን በመተላለፍ ኃጢአት መሥራታቸውን በጭራሽ ሊገነዘቡ አልቻሉም ነበር። እነርሱ በፈለጉት መንገድ ቢኖሩም እንኳ እግዚአብሔር ጥበቃ ሊያደርግላቸው ቃል ኪዳኑ ያስገድደዋል ብለው ያስቡ ነበር። ስለዚህ ኤርምያስ ከኃጢአታቸው የተነሣ ከቃል ኪዳኑ የሚያገኙትን የእግዚአብሔር ጥበቃ እንደሚነጠቁ በአጠቃላይ መጽሐፉ ውስጥ በተደጋጋሚ አሳስቧቸዋል። ይህም ሁኔታ በእነርሱና በከተማቸው ላይ ለሚደርሰው ነገር ሙሉ ለሙሉ ተጠያቂ ሊያደርጋቸው በቅቷል። እግዚአብሔርም በእነርሱ ላይ በሚፈርድበት ወቅት ቃል ኪዳኑን መጠበቁ ነው።

3. በመጨረሻው ምዕራፍ ግለት በምዕ. 52 ውስጥ የተደረገው ምን እንደሆነ እንመለከታለን። ይህም ታሪክ ብቻ ሳይሆን እግዚአብሔር በነብዩ አማካይነት ከተናገረው ነገር አንፃር ሲታይ ያደረገው ምን እንደሆነ የሚያሳይ መረጃ ነው። ይህም ዘወትር የማንኛውም ነቢይ የትንቢት አገልግሎት የመጨረሻ ማረጋገጫ ነው። ምክንያቱም አንድ ሰው ከእግዚአብሔር የተላከ ነቢይ መሆኑን ማረጋገጥ የሚቻለው የተነበያቸው ነገሮች ፍጻሜ ሲያገኙ ብቻ ነው። ስለዚህ ኤርምያስ ሕዝቡና ከዚያም በኋላ የሚመጡት ሰዎች በኋለኛው ዘመን የሚኖሩትን ጨምሮ እነዚህ ነገሮች ልክ እግዚአብሔር በተናገረው መሠረት መፈጸማቸው እንዲመለከቱ በጥያቄ መመዝገብ ነበረበት።

## ንዑስ ክፍል ሦስት፡- ማብራሪያ

1. ኤርምያስ የተወለደው ከኢየሩሳሌም በስተሰሜን በምትገኝ መንደር ውስጥ ከካህን ቤተሰብ ነበር። ስለዚህ ለከተማይቱና ለአገሪቱም ሕዝብ እንግዳ አልነበረም። የዓሞን ልጅ ኢዮስያስ የነገሠው በ640 ዓመተ ዓለም ሲሆን እግዚአብሔር ኤርምያስን ለትንቢት አገልግሎት የጠራው ደግሞ በ627 ዓመተ ዓለም ነበር። ከዚህ ጊዜ ጀምሮ ኢየሩሳሌም በናቡከደነፆር እስከተደመሰሰችበት እስከ 586 ዓመተ ዓለም ድረስ አገልግሎቱን አላቋረጠም፤ ይህም ለ40 ዓመታት ያህል በኢየሩሳሌምና በአካባቢዋ ለነበሩት ሕዝብ ይናገር እንደነበር ያሳያል፤ ኤር. 1፡1-3።

2. ኤርምያስ የተወለደው ከካህን ቤተሰብ እንደመሆኑ መጠን ከሠሩት ኃጢአት የተነሣ በሕዝቡ ላይ ስለሚመጣው ፍርድ የተነገሩትን የቀድሞ ትንቢቶች ያውቃል።

በተጨማሪም የሕዝቡን ኃጢአተኝነት በራሱ ዓይን ሊመለከት ከመቻሉም በላይ አሦስር ሰሜናዊውን መንግሥት ድል ማድረጉን ያውቅ ነበር፤ ሆኖም እነዚህ ነገሮች እርሱን ለነቢይነት ብቁ አላደረጉትም፤ ምክንያቱም ኤርምያስ እግዚአብሔር ለዚህ ልዩ አገልግሎት እንደጠራውና እንደቀባው ያውቅ ነበር፤ የአገልግሎቱም መሠረት ይህ ነበር፤ ኤር. 1:4-10።

3. ቀጥሎም እግዚአብሔር ለኤርምያስ ሁለት ራእዮች ሰጥቶታል። በመጀመሪያ የተመለከተው ራእይ በመሬት ውስጥ ሊተከል ወዲያው ማቆጥቆጥ የሚችል በትር ነበር። ከዚህም በትር ላይ ቁራጩን ቆርጠው ቢተክሉት እንደገና ማደግ እንደሚችል አይቷል። ይህም የተደረገው እግዚአብሔር ዛፍን በከፊል አበላሽቶ ከዚያ አንድ ትንሽ አዲስ ቁራጭ በመውሰድ እንደገና እንዲያቆጠቁጥ ማድረግ እንደሚያስችል ተገንዝቦ ኤርምያስ እንዲጽናና ነበር። ይህም ራእይ ሁሉም በአጠቃላይ እንደማያጠፋ አሳይቷል፤ ኤር. 1:11-12።

4. ባቢሎን የምትገኘው ከይሁዳ በስተሰሜን ምሥራቅ በኩል ቢሆንም እንኳ በኤርምያስ ዘመን ለነበሩት ሰዎች «ሰሜን» የሚለው ቃል ፍቺው እንድ ብቻ ነበር፤ ይኸውም ባቢሎን ማለት ነበር። በሕዝቡ ላይ የተበየነው ፍርድ ገና ድሮውኑ ያለቀ ስለሆነ ኤርምያስ ይህን ማወጅ ነበረበት። ሆኖም ፍርዱ የተወሰነው ከኃጢአታቸው የተነሣ በመሆኑ ንስሐ ገብተው ወደ እግዚአብሔር ቢመለሱ እግዚአብሔር ይቅር እንደሚላቸው ግልጽ ነበር። ኤርምያስ ይህንን መልእክት ለኢየሩሳሌም ሕዝብ ለ40 ዓመታት ያህል ተናግሯል። በመጨረሻም የፍርዱ እርግጠኝነትና የሕዝቡም ልብ ደንዳናነት የኤርምያስን ልብ አሳዝኖታል፤ ኤር. 1:13-19።

5. በይሁዳ የነገሠው የመጨረሻው ንጉሥ ከኢዮስያስ ልጆች መካከል አንዱ የሆነው ሴዴቅያስ ነበር። በኤርምያስ መጽሐፍም ውስጥ በብዙ ስፍራዎች ስለ እርሱ የተጻፉ ነገሮች እናነባለን። ሴዴቅያስ ኃጢአተኛ ንጉሥ ነበር፤ በተጨማሪም ሕዝቡ ተስፋ እስከማይኖራቸው ድረስ በኃጢአታቸው ረክሰው ነበር። ስለዚህ በባቢሎን አማካይነት የሚመጣው ጥፋት የማይቀር ነበር፤ ኤር. 52:1-3።

6. ሴዴቅያስ ራሱን ለናቡከደነፆር ለማስገዛትና እርሱንም ለመታዘዝ ተስማምቶ ነበር፤ በኋላ ግን ዓመጸ። ከዚያም ከተማይቱ ለ18 ወራት የተከበበች ሲሆን በዚህ ዘመን ስለነበረውም ስቃይ በሰቆቃው ኤርምያስ ውስጥ ማንበብ እንችላለን፤ በመጨረሻም ንጉሡና ጥቂት ተከታዮቹ የማምለጥ ሙከራ ቢያደርጉም ተይዘዋል። ልክ ኤርምያስ አስቀድሞ ሴዴቅያስን አስጠንቅቆት በነበረው አኳኋንም እስረኛ ሆኖ ወደ ባቢሎን በመሄድ በወህኒ ሊጣል በቅቷል፤ ኤር. 52:4-11።

7. ከአንድ ወርም በኋላ የባቢሎናዊያን ጦር አዛዥ ወደ ኢየሩሳሌም በመግባት ሙሉ በሙሉ ደምስሶታል፤ ኤር. 52:12-16። ሠራዊቱም የሚቃጠለውን ነገር ሁሉ

አታጥሉ የሚሰበረውን ነገር ሁሉ ሰባብሯል። ከደሆችም በስተቀር የተቀረው ሀብት በሙሉ ወደ ባቢሎን ተወስዷል።

8. በኤር. 52፡17-23 ውስጥ ከቤተ መቅደሱ ጋር ግንኙነት ያላቸው መሣሪያዎችና ዕቃዎች በሙሉ ተጠቅሰዋል፤ እነዚህም ከወርቅ፥ ከብርና ከነሐስ የተሠሩት ዕቃዎች በሙሉ በአህያና በፈረስ ተጭነው ወደ ባቢሎን ተወስደዋል። ነገር ግን ከዕንጨት ስለተሠራው ታቦት ምንም ነገር አልተጠቀሰም፤ ምናልባትም በኤርምያስ 52፡13 ውስጥ በተጠቀሰው መሠረት በእሳት ሳይቃጠል አልቀረም።

9. በኤር. 52፡7 ላይ የተጠቀሱት ኮብላዮች በሙሉ ተይዘው የተገደሉ ሲሆን አንዳንዱ ታላላቅ ሰዎች ግን በከተማይቱ ውስጥ ሳይቀሩ አይቀርም፤ የጥቂቶቹ ስም በኤር. 52፡24 ውስጥ ተሰጥቷል። እነዚህም ሰዎች በሙሉ ተሰብስበው ሪብላ በተባለው በባቢሎናዊያን ጊዜያዊ የጦር ሰፈር ተገድለዋል፤ ኤር. 52፡24-27።

10. ከተማይቱ ተወርራ ሕዝቡ በሦስት የተለያዩ ወቅቶች በምርኮ ተወስደዋል፤ ኤር. 52፡28፥ 29 ና 30። 4600ዎቹ ሰዎች ከከተማይቱ የተወሰዱ መሪዎችና ታላላቅ ሰዎች ብቻ ነበሩ።

11. የአኪን የተያዘው በ597 ዓ.ዓ. ሲሆን፥ የተፈታው ከ37 ዓመታት በኋላ በ560 ዓ.ዓ. ነበር። ሰዴቅያስ የሞተው በእስር ቤት ውስጥ እንዳለ ነበር። በዚህ ወቅት ዳንኤልና ሕዝቅኤል በባቢሎን ያገለግሉ ነበር፤ ሆኖም በዚህ ቦታ ስማቸውን አይጠቅሱም፤ ኤር. 52፡31-34።

## ንዑስ ክፍል አራት - ልዩ ጠቃሚ ነጥቦች

1. እግዚአብሔር የወሰነው ነገር ተግባራዊ ሆኗል። እንደዚህ ማለት በተደረገው ነገር ውስጥ ሕዝቡ ድርሻ አልነበራቸውም ማለት አይደለም። ምክንያቱም እግዚአብሔር በኤርምያስ አማካይነት ያስተላለፋቸው ትንቢቶች በምርጫ ላይ የተደገፉ በመሆናቸው ኢየሩሳሌም በግድ መጥፋት አልነበረባትም፤ ይኽም ምርጫ ሕዝቡ ኃጢአት መሥራታቸውን ከቀጠሉ በኢየሩሳሌም ላይ ጥፋት እንደሚደርስ ሲሆን ኃጢአታቸውን ትተው ከልብ ንስሐ ቢገቡ ደግሞ ከፍርድ ሊያመልጡ እንደሚችሉ ነበር። ሕዝቡ ግን ኃጢአት መሥራት ስለቀጠሉ እግዚአብሔር በኤርምያስ በኩል ለሕዝቡ የተናገረው ቃል ሙሉ በሙሉ ፍጻሜ አግኝቷል።

2. በኤር. 52 ውስጥ የተዘረዘሩት ነገሮች የተፈጸሙት ኤርምያስ በኢየሩሳሌምና በአካባቢዋ አገልግሎት ከጀመረ ከ40 ዓመታት በኋላ ነበር። ከዚህ ጊዜ በፊት ግን ሕዝቡ ብዙ ማስጠንቀቂያዎች ተሰጥቶዋቸው ነበር፤ ከነዚህም መካከል በጣም

ከባዱ በ722 ዓ.ዓ. ድረስ ለ40 ዓመታት የኖረው በሕዝቡ መካከል ነበር። ገና አገልግሎቱን ከመጀመሩ ከበስተሰሜን በኩል የሚፈላው ድስት ሊገለበጥ ተቃርቦ ነበር። ይህም የሚያሳየው ባቢሎን ይሁዳን እንድትወር እግዚአብሔር ያዘጋጃት እንደነበር ነው። ሕዝቡ ግን ምልክቶቹን እንዳይመለከቱ ዓይናቸው ታውሮ ነበር፤ የእግዚአብሔርን ማስጠንቀቂያ እንዳይሰሙ ጆሮአቸው ደንቁሮ ነበር፤ እንዲያድናቸው እንዳይጮኹ አፋቸው ታስሮ ነበር።

3. በኤር. 52 ውስጥ የተዘረዘሩት በጣም አስከፊ ነገሮች በሙሉ የሕዝቡ ያለመታዘዝ ውጤት ናቸው። ምክንያቱም እነዚህ ነገሮች የግድ መፈጸም ያለባቸው ነገሮች በመሆናቸው ብዙ ማስጠንቀቂያዎች ተሰጥቶዋቸው ነበር። ይህንን ቢሰሙ ኖሮ በእነርሱና በአገራቸው ላይ የደረሰውን መከራ ማስወገድ ይችሉ ነበር። በአጠቃላይ በእግዚአብሔር ሕዝብ ላይ የሚደርሰው አብዛኛው መከራ መንሥኤው ከላይ የተጠቀሰው ምክንያት ነው። እግዚአብሔር የመጨረሻውን ፍርድ ሳያመጣባቸው አስቀድሞ ሁለት ማስጠንቀቂያዎች ሰጥቶዋቸዋል። ስለዚህ ፍርዱ የተፈጸመው ያለምንም ምሕረት ነበር። በዚህም ፍርድ ከተማይቱ ተደመሰሰች፤ ቤተ መቅደሱ ሙሉ በሙሉ ፈረሰ፤ እንዲሁም መሪዎች በሙሉ በምርኮ ተወሰዱ።

## ንዑስ ክፍል አምስት - ከአዲስ ኪዳን ጋር ያለው ዝምድና

1. መጽሐፍ ቅዱስ እስከ አሁን ፍጻሜ ያላገኘ ብዙ ትንቢቶች በውስጡ ይዟል። እነዚህንም ትንቢቶች በቀላሉ እናገኛቸዋለን፤ ነገር ግን አንዳንድ ጊዜ በትክክል ተፈጻሚ እንደሚሆኑ እንዘነጋለን። እግዚአብሔር በኤርምያስ አማካኝነት የተናገረውን ትንቢት እንዲሆን በማድረግ የቃሉን እውነተኛነት አረጋግጧል። ኢየሱስ በማቴ. 24-25፤ በማር. 13ና በሉቃስ 21 ውስጥ የኢየሩሳሌምን ጥፋት ከመጨረሻው ፍርድ ጋር አያይዞታል። የመጨረሻው ፍርድ እስከ አሁን ድረስ ፍጻሜ አላገኘም፤ ሆኖም ኢየሱስ ከእነዚህ ምዕራፎች ውስጥ የተናገረው የኢየሩሳሌም ጥፋት በ70 ዓ.ም. ተፈጽሟል። እርሱ ወደዚህ አመል እንደሚመጣ የሚናገሩት ትንቢቶችም እስካሁን ፍጻሜ አላገኙም። ስለዚህም በእምነት ፍጻሜያቸውን እንጠባበቃለን።

2. አዲስ ኪዳንም በብዙ ማስጠንቀቂያዎች የተሞላ ነው። ሆኖም እነዚህ ነገሮች በአፋጣኝ ሲፈጸሙ አናይም። ነገር ግን እስከመጨረሻ ምንም ፍጻሜ አይኖራቸውም ማለት አይደለም። ምክንያቱም እነዚህ ማስጠንቀቂያዎች እንደ ጠቋሚ የማስታወቂያ ሰሌዳዎች የሚያገለግሉን ናቸው። እነርሱም መሄድ የማይኖርብን በየትኞቹ መንገዶች እንደሆነ ያመለክቱናል። ከላይ እንዳየነው የይሁዳና የኢየሩሳሌም ሕዝብ እግዚአብሔር ለኤርምያስ የሰጠውን ማስጠንቀቂያዎች ለመስማት እምቢ ስላሉ ጥፋት መጣባቸው፤ ዛሬም ደግሞ እኛ

ይህንን የአዲስ ኪዳን ማስጠንቀቂያ በቸልተኝነት ስናልፈው እንገኛለን። በዚሁ በመቀጠል በተሳሳቱ አቅጣጫዎች ብንሄድና እግዚአብሔር የማይወዳቸው ነገሮች ብናደርግ ቅጣት እንቀበላለን። ስለዚህ የተስፋ ቃሎቹን በመቀበል ማስጠንቀቂያዎቹን እናስተውላቸው።

3. ከሕዝቡ ያለመታዘዝ የተነሣ ኢየሩሳሌም የተደመሰሰችው በ586 ዓ.ዓ. ነበር። በዚህም ስፍራ በሞላው መጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ በፍጹም ያልተለወጠ ነገር ይገኛል፤ ይኸውም መታዘዝ በረከትን፥ ያለመታዘዝ መከራን እንደሚያስገኝ ነው። እግዚአብሔር ሕዝቡ እንዲጓዝበት የሚፈልገውን መንገድ ሁልጊዜ በግልጽ ያመለክታል። ይህንንም ከቃሉ መረዳት እንችላለን። የእግዚአብሔርን ቃል በየዕለቱ ማጥናት የሚያስፈልገንም ለዚሁ ነው። በተጨማሪ እኛ እንድናደርጋቸው የሚፈልገውን ነገሮች ማድረግ እንድንችል ጌታ ማስተዋልና ብርታት ይሰጠናል። የእርሱን ቃል ለመታዘዝ ፍቃደኞች ስለሆንን በረከቱን፤ ጥበቃውንና እርዳታውን በሕይወታችን ውስጥ መለማመድ እንጀምራለን።

## ንዑስ ክፍል ስድስት - የክለሳ ጥያቄዎች

1. ኤርምያስ አገልግሎቱን እንዲጀምር የተጠራው መቼ ነበር?
2. ኢሳይያስ መቼ ሞተ?
3. ከኢዮስያስ በፊት የነገሡት ሁለት ነገሥታት ማንና ማን ነበሩ?
4. 2ኛ ነገ. 21-22 የሚነግሩን ስለምንድነው?
5. ኤርምያስ የተነበየው ለስንት ዓመታት ያህል ነው?
6. በኢዮስያስ ዘመነ መንግሥት ትንቢት ይናገር የነበረው ሌላ ነቢይ ማን ነው?
7. በ586 ዓ.ዓ. በባቢሎን የነበሩት ሁለት ነቢያት ማንና ማን ናቸው?
8. ኤርምያስ ነቢይ መሆኑን ያረጋገጠለት ድርጊት ምን ነበር?
9. በኤርምያስ ዘመን ዓለምን በቁጥጥሯ ሥር ያደረገችው ኃያል መንግሥት ማን ነበረች?
10. እሥራኤልን ግለት ሰሚናዊውን መንግሥት የደመሰሰቻት ማን ነበረች?
11. ሕዝቡ የተቀጣው ለምንድነው?
12. ኤር. 52 የሚያወራው ስለምንድነው?
13. ኤርምያስ የተወለደው የት ነው?

14. ኤርምያስ ነቢይ የሆነው ለምንድነው?

15. በመጀመሪያው ራእይ ውስጥ ምን ተመለከተ?

16. የሁለተኛው ራእይ ትርጉም ምን ነበር?

17. የይሁዳ የመጨረሻው ንጉሥ ማን ነበር?

18. ዋናው የሴዴቅያስ ስሕተት ምን ነበር?

19. የባቢሎናዊያን ሠራዊት በከተማይቱ ላይ ምን አደረሰ?

20. በከተማይቱ ውስጥ የነበሩት የብረት ዕቃዎች በሙሉ ምን ተደረጉ?

21. ብዙዎቹ የይሁዳ ታላላቅ ሰዎች የተገደሉት የት ነበር?

22. ኢየሩሳሌም በባቢሎናውያን ቅጣት የደረሰባት ስንት ጊዜ ነው?

23. በ560 ዓ.ዓ. ከእሥራት የተፈታው የይሁዳ ንጉሥ ማን ነበር?

24. ኢየሩሳሌም ለምን ተደመሰሰች?

25. ምን ጊዜም ያለመታዘዝ ውጤት ምንድነው?

## ክፍል ሁለት - ኤር. 46-51

### ንዑስ ክፍል አንድ - አጭር ታሪካዊ መግለጫ

1. የኤርምያስ ትንቢቶች በአንድ ላይ ተሰብስበው የተቀመጡት በተነገሩበት ዘመን ቅደም ተከተል ነው የሚል ግምት ሊኖረን አይገባም። ምክንያቱም ምዕ. 46-51 በውስጥ የያዘው ተመሳሳይ የሆኑ ነገሮች እንደሆነ ግልጽ ነው። ኤርምያስ እነዚህን ትንቢቶች የተናገራቸው በተለያዩ ጊዜያት ሊሆን ይችላል፤ ስለዚህ አስፈላጊ የሆነው ነገር የተናገረበት ዘመን አይደለም። ምዕ. 1 ና 52 ከኤርምያስ አገልግሎት ጅማሬና ፍጻሜ ጋር አስተዋውቀውናል፤ ከምዕ. 46-51 ያለው ክፍል ደግሞ በይሁዳ ጠላቶች ላይ የተነገሩትን አብዛኛዎቹን ትንቢቶች ያቀርብልናል። እነዚህም ኤርምያስ የተናገረው በትክክል መፈጸሙን ለማሳየት ተጨማሪ ማረጋገጫ ሆነው በመጽሐፉ መጨረሻ ላይ ሰፍረዋል።

2.




የኤር. 46-51 መግለጫ ካርታ

3. ናቡከደነፆር በ606፥ በ597ና በ586 ዓ.ዓ. ለሦስት ጊዜ ያህል ይሁዳን ወሯታል። በኤር. 46-49 ውስጥ የሚገኙትም አንዳንድ ትንቢቶች ከነዚህ መናት በአንዱ ውስ የተፈጸሙ ናቸው። ግብፅ የተሸነፈችው በ605 ዓ.ዓ. ነበር፤ 2ኛ ነገ. 24:7። በኤር. 49 ውስጥ የተጠቀሱትም ስፍራዎች በቁጥጥር ሥር የዋሉት ባቢሎን በ597 ዓ.ዓ. በዚያ አካባቢ ባደረገችው ወረራ ሳይሆን ይቀርም። በተቃራኒው ደግሞ በኤር. 50-52 የተገለጸው ከዚህ በጣም የተለየ ው። ምክንያቱም ባቢሎን እስከ 538 ዓ.ዓ. ወይም 537 ዓ.ዓ. ድረስ አለመደምሰሷ ግልጽ ነው። ምናልባትም ኤርምያስ ይህንን ሁሉ የጻፈው ሴዴቅያስ በነገሠ በአምስተኛው ዓመት በ597 ዓ.ዓ. ሳይሆን አይቀርም። በምርኮ ተወስደው ስለነበሩት ሰዎች የሚናገሩትም ኤር. 50:4፥ 17ና 51:34፤ እንዲሁም ቤተ መቅደሱ እንደተደመሰሰ አድርገው የሚያቀርቡት ኤር. 50:28ና 51:11 ምናልባት ትንቢታዊ እንጂ ገላጭ ላይሆኑ ይችላሉ።

## ንዑስ ክፍል ሁለት - የነቢዩ ሽክም

1. ሁሉም ነገር በእግዚአብሔር ቁጥጥር ሥር እንደሆነ ግልጽ ነው። ኤርምያስ ኃያላን የነበሩትን የግብፅ፥ የፍልስጥኤምና የባቢሎን መንግሥታት ጠቅሷቸዋል። በእነዚህ መንግሥታትም ኃይል ሁሉ በእነርሱ እጅ ያለ መስሎ ይታይ ነበር። ሦስቱ የይሁዳ ረቤት አገሮች የሆኑት ዓሞን፥ ሞዓብና ኤዶም ግን ይሁዳን ለብዙ ዘመናት ቢወጉትም ኃይላቸው እስከዚህም አልነበረም፤ ሆኖም እነርሱም ቢሆኑ በእግዚአብሔር ቁጥጥር ሥር ነበሩ። በስተሰሜን በኩል የሚገኙትም ኃያላን ከተሞችም ማለት ደማስቆ፥ ቁዳርና አሶርም በእግዚአብሔር እጅ ውስጥ ነበሩ። እነርሱም ሆኑ ሌሎች ግን በእግዚአብሔር ቁጥጥር ሥር መሆናቸውን በግልጽ አይገነዘቡትም ነበር። ስለዚህም እያንዳንዳቸው በየተራ ድል ተደርገው ኃይላቸው ይነጠቃል፤ እግዚአብሔርም ያዋርዳቸዋል።

2. ይሁዳ ብዙ ጊዜ እርዳታ ለማግኘት ወደ እነዚህ መንግሥታት ፊቷን አዙራለች። እግዚአብሔር ግን ሊቀጣት ሲመጣ ሊያድናትና ሊረዷት በፍጹም አይችሉም። ለዚህም ምሳሌ የሚሆነው ኢሳይያስ በኖረበት ዘመን አካዝ ከአሦር እርዳታ አገኛለሁ ብሎ ጠብቆ ነበር፤ በኤርምያስ ዘመን ዓመፀኛዋ ይሁዳ ባቢሎንን ድል እንዳደርግ ግብፅ ትረዳኛለች የሚል ግምት ነበራት። በዚህ ፈንታ ግን እነዚህ ነገሥታት ሁሉ በእግዚአብሔር ድል ተመቱ። ቢረዱት ግን በራሱ አሠራር መንገድ ይሁዳን ሊያድን የሚችል እግዚአብሔር ብቻ ነበር። ይኸም የሚሆነው ከልብ ንስሐ ገብታ ወደ እርሱ ብትመለስ ነበር። እነዚህ ባዕድ መንግሥታት ግን በጭራሽ እውነተኛ እርዳታ ሊሰጧት አይችሉም። ምክንያቱም የእነርሱ ፍላጎት ይሁዳን በቁጥጥራቸው ሥር ማዋል ብቻ ነበር።

3. እግዚአብሔር የሚናገረው ስለ ይሁዳ ብቻ ሳይሆን ስለነዚህ ባዕድ መንግሥታትም ጭምር ነው። እግዚአብሔርም ስለነርሱ የተናገራቸው ነገሮች በሙሉ ፍጻሜ አግኝተዋል። የእግዚአብሔር ቃል ፍጹም እውነተኛ ስለመሆኑ ሌላ ማረጋገጫዎች ቢያስፈልጉም፥ እነዚህ ተጨማሪ መረጃዎች ናቸው። አብዛኞቹ አይሁዶች የኢየሩሳሌምን ውድቀት የሚተረጉሙት ከሃይማኖት አቅጣጫ ሳይሆን ከውትድርና አንፃር ነበር። የኤርምያስ መጽሐፍ ይህንን ትርጉም ይቃወማል። እንደተናገረውም ውድቀትና ድል የእግዚአብሔር ፈንታ እንጂ የይሁዳ ደካማነት ወይም የባቢሎን ብርታት አይደለም። ምክንያቱም ይህ ነገር እንደሚሆን እግዚአብሔር አስቀድሞ አሳስቦአቸዋል፤ የሚሆንበትንም ምክንያት ነግሮአቸዋል፤ እንዴት ሊያስወግዱትም ይችሉ እንደነበር ገልጾላቸዋል።

## ንዑስ ክፍል ሦስት - ማብራሪያ

1. የግብፅን ውድቀት በሚመለከት በኤር. 46 ውስጥ ሁለት ትንቢቶች ተጠቅሰዋል። ቁ. 2-12 የሚያመለክተው በ606-5 ዓ.ዓ. ባለው ጊዜ የግብፃውያን ሠራዊት ከርከሚሽ በተባለው ሥፍራ ድል ስለመሆናቸው ነው። ኤርምያስ በቁ. 13-14 ውስጥ የሚናገረው ግን ከዚህ ቆየት ብሎ ናቡከደነፆር የግብፅን አገር እንደወረራት ነው፤ ይህም ተፈጻሚነት ያገኘ ትንቢት ነው። ይህንንም ነገር የሚያደርገው እግዚአብሔር ራሱ ነው፤ ኤር. 46፡25-26። በመጨረሻም በቁ. 27-28 ውስጥ ምን ጊዜም ለርሱ ልዩ ለሆኑት ሕዝቦች የመጽናኛ ቃል ሊሰጣቸው ይታያል።

2. ከቀድሞ ጀምሮ ፍልስጥኤማውያን የእግዚአብሔር ሕዝብ ጠላቶች ነበሩ። በመጨረሻም ናቡከደነፆር ጋዛን በ605-4 ዓ.ዓ. ደመሰሳት። ይህም ነገር የተፈጸመው ኤርምያስ ትንቢቱን ከተናገረ በኋላ ነው። የተጠቀሱትም ከፍልስጥኤማውያን አምስት ከተሞች መካከል ሁለቱ ብቻ ናቸው። እነዚህ ሁለቱ መጥፋት ነበረባቸው። በዚህ ክፍል የተጠቀሱትም ሰዎች በሙሉ ጨርሰው ጠፍተዋል። ስለዚህ በዛሬ ዘመን በዚህ ስም የሚጠራው ሕዝብ ከነዚህ ጋር በምንም አይዛመድም። ባቢሎንን እነርሱን ለማጥፋት የተጠቀመባት እግዚአብሔር ራሱ ነው።

3. በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ከሚገኝ ከማንኛውም ምዕራፍ ይልቅ ኤር. 48 ስለ ሞዓብ በይበልጥ ይናገራል። ሞዓብ ከጨው ባሕር በስተምሥራቅ የምትገኝ ባለፀጋ የእርሻ አገር ነበረች። በተጨማሪም ሀብታምና ከፍተኛ የሕዝብ ብዛት የነበራት አገር ነበረች። ለዚህም በምዕ. 48 ውስጥ የተጠቀሱትን የሞዓብ ከተሞች ቁጥራቸው በመጨረሻ የኤርምያስ ትንቢት ተፈጽሟል። ከመጠሪያ ስሟ በስተቀር ሌላ ምንም ነገር እስከማይተርፍ ድረስ ወረራ አድርገው እንዲደመስሷት እግዚአብሔር በተለያዩ መንግሥታት ተጠቅሟል። ምክንያቱም ሞዓብ ለብዙ

መቶ ዓመታት የይሁዳ ጠላት ነበረች። ስለዚህም የእግዚአብሔር ሕዝብ ሲተርፍ ሞዓብ ግን ለዘላለም ጠፍታለች።

4. ቀጥሎም ኤርምያስ ትንቢቱን በተለያዩ ስድስት አገሮች ላይ ተናግሯል። እነዚህም በኤር. 49 ስለ ዓሞን ቁ. 1-6፡ ስለ ኤዶም ቁ. 7-22፡ ስለ ደማስቆስ ቁ. 23-27፡ ስለ ቄዳርና አሶር ቁ. 28-33፡ እንዲሁም ስለ ኤላም ቁ. 34-39 ይናገራል። ዓሞን የምትገኘው ከሞዓብ በስተሰሜን ሲሆን ምዕ. 48፥ ኤዶም ደግሞ ከሞዓብ በስተደቡብ ነበር። የተቀሩት አገሮች በሙሉ ከይሁዳ በስተሰሜን በኩል ርቀው የሚገኙ ነበሩ። በተለይም ኤላም የምትገኘው በጣም ርቃ በባቢሎን አካባቢ ነበር። እግዚአብሔርም በባቢሎን መንግሥት ተጠቅሞ በእነዚህ መንግሥታት በአብዛኛዎቹ ላይ ፈርዶባቸዋል። እነዚህም ትንቢቶች በሙሉ ተፈጽመዋል።

5. ኤር. 50 የተጻፈው በከፊል ግጥምና በከፊል ስድ ንባብ መልክ ነው፤ ይህም ኤርምያስ በተለያዩ ወቅቶች የተናገራቸው ትንቢቶች ስብስብ መሆኑን ይጠቁመናል። በዚህ ምዕራፍ ኤርምያስ የባቢሎንን በፋርስ መሸነፍ ይነግረናል፤ ቁ. 1-3። ይሽውም እሥራኤል ከኃጢአትም የተነሣ 6-7 ተነጥቀው ወደነበረው ወደ አገሯ መመለስ እንድትችል ለማድረግ ነበር፤ ቁ. 4-5። እግዚአብሔርም ባቢሎንን ሊያጠፋትና የራሱንም ሕዝብ መልሶ ሊያቋቁም ስለሆነ አይሁድ ከባቢሎን ከተማ መውጣት ነበረባቸው፤ ቁ. 8-10፥ 11-16 ና 17-20። ባቢሎን በበኩሏ ግን ልጠፋ አልችልም ብላ ገምታ ነበር። ሆኖም እግዚአብሔር ስላልደገፋት ወዲያው ፈራርሳለች፤ ቁ. 21-27፥ 28-30 ና 31-32። ምክንያቱም እግዚአብሔር በዚህ ጊዜ የቆመው እሥራኤልን ደግፎ ነበር፤ 33-34። ቁጣውም በሰይፍ ተመስሎ ቀርቧል፤ ቁ. 35-38። ይህም የመጣው በፋርስ አማካይነት ሲሆን፥ ቁ. 41-43፥ እግዚአብሔርም ኃያሏን ባቢሎንን ለመቅጣት ፋርስንና ንጉሥ ቂሮስን ተጠቅሞባቸዋል፤ ቁ. 39-40። ባቢሎንም በመቃወም የተነሣችው ፋርስ ሳትሆን እግዚአብሔር እራሱ ነበር፤ ቁ. 44-46። ስለዚህም ምንም ማምለጫና መዳኛ አልነበራትም።

6. በኤር. 51 ውስጥም ካለፈው ጋር ተመሳሳይ የሆነ ጽሑፍ እንመለከታለን። እግዚአብሔር ባቢሎንን ስለተቃወማት ሚዶናውያንን ሊያስነሣባት እንደሆነ ይናገራል፤ ይህም የተሸነፈች ያህል ያስቆጥራታል፤ ቁ. 1-5፥ 6-10 ና 11-14። ማንኛውንም ነገር ማድረግ የሚቻለው በራስ ብርታት ስላይደለ እግዚአብሔር ታላቅነቱን በዚህ አማካይነት ገልፅዋል፤ ቁ. 15-19ና 20-23። ስለዚህም እግዚአብሔር እራሱ በባቢሎን ላይ ስለተነሣባት በሰው ሳይሆን እርሱ በራሱ ጥቃት ይደርስባታል፤ ቁ. 24-26 ና 27-33። በባቢሎን ላይ በታወጀው ፍርድ መሠረት ይህ የመጨረሻ መጥፊያዋ ይሆናል፤ ቁ. 34-37 ና 38-40። ምክንያቱም በባቢሎን ላይ የተፈረደው ፍርድ ፍጹም እርግጠኛ ስለሆነ

የእግዚአብሔር ሕዝብ ከዚያ እንደሚያመልጥ ግበረታቻ ተሰጥቶታል፤ 41-46። እርሷም በአጥፊዎችዋ እጅ ልትወድቅ ተቃርባለች፤ 47-57። ባቢሎን ፈጽማ መነሣት እስከማትችል ድረስ ሆና ትደመሰሳለች፤ 52-58። ኤርምያስም በመጽሐፍ ውስጥ በመጨረሻ ያሰፈረው ጽሑፍ ይህ ነው። ማንኛውም ሰው ይህ ነገር ፍጻሜ እንደሚያገኝ ጥርጣሬ ሊኖረው አይገባም። ምክንያቱም ባቢሎን ሙሉ በሙሉ መደምሰስ ብቻ ሳይሆን በእርግጥም ለብዙ መቶ ዓመታት እንደተረሳች ቀርታለች፤ ቁ. 59-64። የእግዚአብሔር ቃል ግን ለዘላለም ይኖራል።

## ንዑስ ክፍል አራት - ልዩ ጠቃሚ ነጥቦች

1. ኤርምያስ በአካባቢው ያሉትን መንግሥታት በሙሉ እንዲመለከት እግዚአብሔር አነሣሥቶት ነበር። ከነዚህ መንግሥታት መካከል አንዳንዶቹ ጠንካራ ሌሎቹ ደግሞ በጣም ደካማ ነበሩ። አንዳንዶቹ በጣም ቅርብ ሲሆኑ ሌሎቹ ደግሞ እጅግ ሩቅ ነበሩ። ሆኖም እግዚአብሔር ሳይመለከተው የታለፈ አንድም አገር አልነበረም። ይህም ለእነርሱና ለይሁዳ እግዚአብሔር በሁሉ ላይ ገናና መሆኑን ግላሰቢያ ነበር። እነዚህ መንግሥታት እያንዳንዳቸው የራሳቸው አምላኮች ነበሯቸው፤ ሆኖም እነዚህ ትንቢቶች በሚፈጸሙበት ጊዜ የእነርሱ ጣዖታት ጨርሶ እውነተኛ አምላኮች እንዳልነበሩ ያሳይሉ። ኤርምያስ ሌሎች ተጨማሪ መንግሥታት መጥቀስ ይችል ነበር፤ ነገር ግን ግናቸውም ከእግዚአብሔር ቁጥጥር ውጭ አለመሆናቸውን ለመጠቆም እነዚህ በቂ ናቸው።

2. ለሁሉም የተሰጣቸው ዕድል አንድ ዓይነት ነበር። ብዚህም ዕድል በአካባቢው ላሉ መንግሥታት ሁሉ ደኅንነት ወይም ጥፋት ሁለት አማራጭ ብቻ ቀርቦላቸዋል። የእግዚአብሔርን ምሕረት ለመለማመድ የተሰጣቸው አንድ መንገድ ብቻ ነው፤ ይኸውም ለሕዝቡ በሰጠው ቃል ኪዳን አማካይነት ነው። በእነዚህ ምዕራፎች ውስጥ የተጠቀሱት መንግሥታት በሙሉ ምን እንደሚጠበቅባቸው ከእሥራኤል የሥርዓት አከባበሮች ሊረዱ ይችሉ ነበር። በመጨረሻም እግዚአብሔር በነቢዩ ኤርምያስ አማካይነት ስለነርሱ የተናገረው ሁሉ ተፈጽሟል። ስለዚህ መንግሥታት በሙሉ የእግዚአብሔርን ፍርድ ተቀብለዋል። የእግዚአብሔር ታላቅነትም እንዲገለጥ ሁሉም ተደምስሰዋል።

3. በዚያ ዘመን ባቢሎን ዓለምን በቁጥጥር ሥር አድርጋ ስለነበር ይህ ክፍል በይበልጥ ትኩረት ያደረገው በእርሷ ላይ ነው። ባቢሎን ለዘላለም ለመምራት የሚያስፈልጋት ነገር ሁሉ ግለትም ሀብት፥ ኃይል፥ ወዘተ... ነበራት። ኤርምያስ ግን በትንቢቱ ባቢሎን ልትደመሰስ ነው ሲል አስቀምጧል፤ ከዚህ ኃያል ከተማ ውስጥ ምንም የሚተርፍ ነገር እንደሌለ ተናግሯል። ከተማዋም የሚደርስባት ነገር ድል መሆን ብቻ ሳይሆን በአሸዋ ውስጥ ተቀብራ ከትውልድ

እስከ ትውልድ ዘመን የተረሳችም እንደምትሆን ነው። እግዚአብሔርን የሚቃወም ኃይል ሁሉ መጨረሻው ይህ ነው። ለጊዜው አስፈሪ መስሎ ሊታይ ይችላል፤ እግዚአብሔርም ዓላማዎቹን ከግቡ ለማድረስ ይጠቀምበታል፤ በመጨረሻ ግን ያጠፋዋል።

## ንዑስ ክፍል አምስት፡- ከአዲስ ኪዳን ጋር ያለው ዝምድና

1. አዲስ ኪዳን እግዚአብሔር ታላላቅ መንግሥታትን፥ ታናናሽ መንግሥታትን፥ ታላላቅ ሰዎችንንና እኛ ትናንሽ የምንላቸውንም ሳይቀር በቁጥጥሩ ሥር ያደረጋቸው መሆኑን በብዙ ስፍራዎች ያሳስበናል። በራሳችን ላይ ያሉት ጠጉሮቻችን ሳይቀር የተቆጠሩ ናቸው። እግዚአብሔር የእርሱ ለሆኑት ሰዎች ጥበቃ ያደርግላቸዋል፤ እግዚአብሔርም ካልፈቀደ በስተቀር የእርሱ በሆኑት ሰዎች ላይ ምንም ጉዳት አያደርስባቸውም። በአጠቃላይ እግዚአብሔር ሳያውቀው የሚሆን ምንም ነገር የለም። ከርቀት የተነሣም የእርሱ ጥበቃ የማይደርሳቸው ሰዎች የሉም። ምክንያቱም የሩቁም የቅርቡም ለእርሱ እኩል ነው። እርሱም የሁሉም ፍላጎት ያውቃል፤ አስፈላጊ የሆነውንም ነገር ሁሉ ያቀርብላቸዋል። ዓለምና በውስጡዋ ያለው ሁሉ አሁንም ወደፊትም በእርሱ ቁጥጥር ሥር ነው። ስሙ የተባረከ ይሁን።

2. በብሉይ ዘመን ይፈርድ የነበረው እግዚአብሔር አሁንም መፍረዱን አላቋረጠም። ፍርዱም ከመንግሥታት እስከ ዓለም ሁሉ ይደርሳል። እርሱም ፈጣሪ እንደመሆኑ መጠን ሁሉም መንግሥታት ለእርሱ መልስ እንዲሰጡት የመጥራት መብትና ሥልጣን አለው። ፍርድም ኃይልና ስልጣን ሁሉ የእርሱ መሆኑ የሚያሳይ አኳኋን በተለያዩ መንገዶች ይገልጻል። በኤርምያስ መጽሐፍ ውስጥ ስለ አሕዛብ መንግሥታት ስናነብ ጊዜው በጣም የራቀ መስሎ ይታየናል። ሆኖም እንደነዚያ መንግሥታት መልስ መስጠት እንደነበረባቸው ሁሉ በአሁኑም ዘመን ያሉት መንግሥታት ደግሞ አንድም ሳይቀሩ ለእግዚአብሔር መልስ ለመስጠት ይጥራሉ።

3. በብሉይ ዘመን ከነበሩት ኃያላን መንግሥታት መካከል እጅግ ኃያሏ ባቢሎን ነበረች። ባቢሎን በእርግጥ ሕልውና የነበራት መንግሥትና ከተማ ነበረች። ከዚህ ሁሉ በላይ ባቢሎን የእግዚአብሔርን ሥራ የሚቃወም የማንኛውም ዓይነት ቡድን ምሳሌያችን ናት። ባቢሎን በአዲስ ኪዳን ውስጥ ያላት መሠረታዊ ትርጉም ይህ ነው። ለዚህም ማረጋገጫ የሚሆነው በዓለም ታሪክ ውስጥ ክርስትናን የሚቃወም ማኅበረሰብ መመሥረት የጀመሩ ብዙ የተደራጁ ቡድኖች ነበሩ፤ ነገር ግን እያንዳንዳቸው በየተራ ጠፍተዋል። እግዚአብሔር በኤርምያስ ዘመን የነበረችውን ባቢሎንን እንዳጠፋ ሁሉ በዘመናችንም ሆነ ወደፊት የሚነሣ

ባቢሎንን ሊያጠፋ እንደሚችል እርግጥ ነው።

## ንዑስ ክፍል ስድስት፡- የክለሳ ጥያቄዎች

1. በኤር. 46-51 ውስጥ ያለው ምን ዓይነት ጽሑፍ ነው?
2. እነዚህ ትንቢቶች ፍጻሜ ያገኙት መቼ ነበር?
3. ኤር. 50-51 የሚያወራው ስለምንድነው?
4. የከርከሚሹ ታላቅ ጦርነት የተደረገው መቼ ነበር?
5. በዚህ ክፍል የተጠቀሱት ሦስት ታላቅና ኃያል መንግሥታት እነማን ናቸው?
6. የይሁዳ የቅርብ ጎረቤት የነበሩት ሦስት አገሮች ማን ማን ነበሩ?
7. በጣም ሩቅ የነበሩት መንግሥታት ማን ማን ናቸው?
8. በኢሳይያስ ዘመን ከአሦር እርዳታ የጠየቀው ንጉሥ ማን ነው?
9. እነዚህ ምዕራፎች የሚያሳዩን ታላቅ እውነት ምንድነው?
10. በኤር. 47 የተተነበየው የማን መደምሰስ ነው?
11. ኤር. 48 የሚገልጸው የትኞቹን የይሁዳ ጎረቤት አገሮች ነው?
12. በ612 ዓ.ዓ. አሦርን ድል አድርጋ እስከ 538-7 ዓ.ዓ. ድረስ በዓለም ላይ እጅግ ኃያል መንግሥት የሆነችው ማን ናት?
13. ይሁዳን በሚመለከቱ ጉዳዮች ላይ የባቢሎን ዝነኛ ንጉሥ ማን ነበር?
14. ኤር. 50 ና 51 ፍጻሜ ያገኘው እንዴት ነበር?
15. በኤር. 46-51 ውስጥ የተጠቀሱት የአሕዛብ አምላኮች ምን ደረሰባቸው?
16. ባቢሎን የማን ምሳሌ ናት?

## ንዑስ ክፍል ሰባት አስተዋፅኦ

### በግብፅ ላይ የተፈረደው ፍርድ፡- ኤር. 46፡1-28

1-6 · በ606-5 - የተደረው የከርሚሽ ጦርነት

7-12 - የግብፃውያን ጽኑ ፍላጎት

13-19 - የናቡከደነጾር መምጣት

20-24 - የግብፅ መሸነፍ
25-28 - ቅጣትና መጽናኛ

ለፍልስጥኤማውያን የተነገረ ቃል፡- ኤር. 47፡1-7

1-7 - የፍልስጥኤማውያን ውድቀት

የይሁዳ ጎረቤት አገር ሞዓብ - ኤር. 48፡1-17

1-2 - የሞዓብ ከተሞች ውድቀት
3-9 - የሞዓብ አምላኮች ተደመሰሱ
10-13 - የሞዓብ ምኞትና ቸልተኝነት
14-17 - ድል የተመታው ሠራዊት
18-20 - የሞዓብ ከጥቅም ውጭ መሆን
21-33 - የከተሞቹ ዕርቃናቸውን መቅረት
34-36 - የሞዓብ ተስፋ መሟጠጥ
37-44 - ፍርሃትና ድንጋጤ በየቦታው
45-47 - የሐሴቦንና ሴዎችን መቃጠል

ዓሞን፥ ኤዶም፥ ደማስቆ፥ ቄዳርና ኤላም - ኤር. 49፡1-39

1-2 - የረባት መደምሰስ
3-6 - የዓሞን ዕርቃኗን መቅረት
7-16 - የኤዶም ለቅጣት መዘጋጀት
17-22 - የኤዶም መጥፎ ዕድል
23-27 - በደማስቆ ላይ የተፈረደው ፍርድ
28-33 - ቄዳርና አሶር
34-39 - የኤላም መደምሰስ

## በባቢሎን ላይ የተነገሩ ትንቢቶች - ኤር. ምዕ. 50 ምዕ. 51


1-3 - የባቢሎን አምላኮች ተደመሰሱ

4-5 - በእሥራኤልና በይሁዳ የተደረገው ንስሐ

6-7 - ተቅበዝባዥ ሕዝብ

8-10 - ከባቢሎን የመውጫ ወቅት

11-16 - ባቢሎንን ለሚወሩ የተሰጠ ምክር

17-20 - ለእሥራኤል የተደረገው ይቅርታ

21-27 - በባቢሎን ላይ የእግዚአብሔር ተቃውሞ

28-32 - የእግዚአብሔር ፍርድ

33-34 - የእግዚአብሔር የማዳን ኃይል

35-38 - የሰይፍ መዝሙር

39-40 - የከተማይቱ ሰው አልባ መሆን

41-43 - ባቢሎን ተወረረች

44-46 - ባቢሎንን በመቃወም እግዚአብሔር ያወጣው ዕቅድ


## ምዕራፍ 51


1-5 - የወራሪዎች ዝግጅት

6-10 - ከባቢሎን የመውጫ ጥሪ

11-14 - የሚዶን መንግሥት

15-19 - የእግዚአብሔር ታላቅነት

20-23 - እግዚአብሔር ለሕዝቡ የሰጠው ተስፋ

24-33 - የባቢሎን አወዳደቅ

34-37 - የናቡከደነፆር ሞጥፎ ዕጣ

38-40 - የእግዚአብሔር ዕቅድ

41-46 - የባቢሎን ውድቀት

47-49 - የማይቀረው ጥፋት

50-51 - የይሁዳ ማምለጥ

52-53 - የባቢሎን ትዕቢት

54-57 - የጥፋት ጩኸት

58 - የባቢሎን ሽልማት

59-64 - በ594-3 ዓ.ዓ. የተጻፈ ጽሑፍ

## ክፍል ሦስት - ኤር. 26-32

### ንውስ ክፍል አንድ - አጭር ታሪካዊ መግለጫ

1. እስካሁን ድረስ የትንቢተ ኤርምያስን ሁለት ክፍሎች ተመልክተናል። በምዕ. 1 ና 52 ውስጥ የኤርምያስን ጥሪና በአገልግሎቱ ዘመን ማብቂያ ላይ የተደረገውን ነገር አይተናል። የተነበያቸው ነገሮች እውነተኛነት ከመረጋገጡም በላይ ከተማይቱ ተደምስሳ ሕዝቡም በምርኮ ተወስደዋል። ምዕ. 46-51 በአንድ ላይ የቀረበበት ምክንያት በውስጡ የያዘው ሐሣብ ተመሳሳይ በመሆኑ ነው። ኤርምያስ እነዚህን ትንቢቶች የተናገረው በተለያዩ ጊዜያት ሊሆን ስለሚችል ትንቢቶቹ የተቀመጡት በተጻፉበት ዘመን ቅደም ተከተል አለመሆኑን መገንዘብ ጠቃሚ ነው። ኤርምያስን በምዕ. 46-51 ባለው ክፍል ውስጥ እግዚአብሔር በእነዚህ መንግሥታት ሁሉ ላይ የበላይ እንደሆነና በመጨረሻ በሁሉም ላይ እንደሚፈርድባቸው ያሳያል።

2. ከኤር. 26-45 ያለው ክፍል ደግሞ በዚህ ትንቢት ውስጥ አንድ የተለየ ነገር ይፈጥራል። በእነዚህ ምዕራፎች ውስጥ የቀረቡት ሐሣቦች ከመጨረሻ ሁኔታ ጋር ተመሳሳይነት አላቸው። ኤርምያስ ለአገልግሎት የተጠራው በ627 ዓ.ዓ. እንደሆነና ኢየሩሳሌምም በ586 ዓ.ዓ. እስከ ተደመሰሰች ድረስ እንዲሁም ከዚያ በኋላ አገልግሎት መስጠቱን እንዳላቋረጠ አይተናል። በምዕ. 26-45 ውስጥ የሰፈረው ሐሳብ ኢየሩሳሌም ከተያዘችበት ዘመን አካባቢ ጋር የሚዛመድ ነው። ለዚህም ማረጋገጫ የሚሆነው በነዚህ ምዕራፎች ውስጥ የተለያዩ ነገሮች ግለትም ታሪክ፥ ስብከትና ስለ ወደፊቱ የሚያወሩ ትንቢቶች መገኘታቸው ነው። በዚህ ሥፍራ ነቢዩ የ586ቱ ዓ.ዓ. አስጨናቂ ፍርድ ከመምጣቱ በፊት የመጨረሻ ማስጠንቀቂያውን ለሕዝቡ ሲሰጥ ይታያል።

3. በእነዚህ ምዕራፎች ውስጥ የምናገኘው ሌላ ነገር ግልጽ እየሆነ በመምጣት ላይ ስላለው የእግዚአብሔር የተስፋ ቃል ነው። ይህም ትንቢተ ኤርምያስ ስለ ፍርድ ወይም በፍርድ ላይ ብቻ የሚያተኩር መጽሐፍ እንዳልሆነ ያሳያል። ፍርድ ብቻውን የመጨረሻ ነገር አይደለም። እግዚአብሔር የሚፈርደው ለዓላማው ነው። ይህም ዓላማ ሕዝቡን ለማጥራትና ከፍርዱም በኋላ መልሶ ለማቋቋም ነው።

ከምዕ. 2-25 ባለው ክፍል ውስጥ እምብዛም በተስፋ ቃል የቀረቡ ነገሮች አናገኝም። ነገር ግን በነዚህ ምዕራፎች ውስጥ በጣም ግልጽ እየሆነ ሲመጣ እናያለን። በመጨረሻም እግዚአብሔር ከፍርዱ በኋላ ሕዝቡን መልሶ እንደሚያቋቁማቸው የተናገረው ትንቢትም በትክክል ተግባራዊ ሆኗል፤ ፍጻሜም አግኝቷል። በዚህም ምክንያት ዘሩባቤል በ536 ዓ.ዓ. የመጀመሪያውን ቡድን ሕዝብ እየመራ ከባቢሎን ወደ ይሁዳ ተመልሷል። ከዚህ በመቀጠል ሌሎች በ457 ዓ.ዓ. ከዕዝራ ጋር ሲመለሱ የተቀሩት ደግሞ ከ13 ዓመታት በኋላ ከነህምያ ጋር ተመልሰዋል።

## ንዑስ ክፍል ሁለት፡- የነቢዩ ሽክም

1. እግዚአብሔር በባሕሪው ኃጢአትን መጥላቱና የሕዝቡ ከኃጢአት አለመመለስ፥ የኢየሩሳሌምን መደምሰስ በ586 ዓ.ዓ ፍጹም ተግባራዊ አድርጎታል። እግዚአብሔር ከአብርሃምና ከሙሴ ዘመን አንሥቶ ጻድቅ አምላክ መሆኑን ግለትም ሕዝቡ ቃሉን እንዲታዘዙ የሚሻ መሆኑን ቢገልጽም እንኳ ሕዝቡ ግን ይህን መጠበቅ ተስኗቸው ነበር። ለዚህም ምክንያታቸው እንደፈለግን ሆነን ብንኖር የእግዚአብሔር ድጋፍ አይለየንም ብለው ያስቡ ስለነበር ነው። ኤርምያስም በኃጢአታቸው ላይ በጣም የሚያተኩረው ስለዚህ ነው። ኃጢአታቸውንም ከእግዚአብሔር ጽድቅ ጋር በማነፃፀር አሳስቧቸዋል። ሕዝቡም ንስሐ መግባት እንቢ ስላሉና ኃጢአት መሥራታቸውን ስለቀጠሉ ከፍርድ በቀር ሌላ ምንም አማራጭ አልነበራቸውም። ሕዝቡም ንስሐ አንገባም በማለታቸው ፍርዱን በገዛ ራሳቸው ላይ ያመጡት ነገር ነበር።

2. ሕዝቡን እንደገና ማሠልጠንና ማጥራት አስፈላጊ ስለነበር የባቢሎን ምርኮ የግድ አስፈላጊ ነበር። ምክንያቱም ሕዝቡ የሕግንና የነቢያትን መጽሐፍት ትምህርቶች ረስቶ ጣዖትን ወደማምለክ ተመልሶ ነበር፤ ስለዚህ ሕዝቡም ከቤተ መቅደሱና ከሥርዓቶቹ ይልቅ እንደገና በእርሱ ብቻ መታመን እንዲማር እግዚአብሔር ሕዝቡን ከተለማመደው ነገር ሁሉ ማራቅ ነበረበት። እነርሱ ግን ካላቸው ባሕርይ የተነሣ ይህንን ነገር ሊገነዘቡ አልቻሉም ነበር፤ የሚገምቱትም እግዚአብሔር ትቶናል ብለው ነበር። ኤርምያስንም ሊረዱት ያልቻሉበት ምክንያት ይህ ነበር። በመጨረሻ ግን ምርኮው ሊረሱት የማይችሉት ትምህርት አስተምሯቸዋል።

3. የእግዚአብሔር የተስፋ ቃሎች እውነተኝነትን ከምርኮ መመለሳቸው እርግጠኛ አድርጎታል። ምንም እንኳ ሕዝቡ ልበ ደንዳና ቢሆንም እግዚአብሔር የማይሻር ዕቅድ ነበረው። መሢሑን የሚቀበሉት ሰዎች በግዘጋጀት ላይ ነበር። እግዚአብሔር ሊያጠራቸው ለ50 ዓመታት ወደ ባቢሎን ቢልካቸውም እንኳ መመለሳቸውም እንደ እግዚአብሔር የተስፋ ቃል እርግጠኛ ነበር። ይህ ተስፋ ወደ ባዕድ አገር ለሄዱትና አብዛኛዎቹ እዚያው እንዳሉ ለሞቱት ሰዎች ምንም

ለውጥ አላመጣም። ሆኖም የይሁዳ መሸነፍ ምርኮውና በቂሮስ ዘመነ መንግሥት ከምርኮ መመለሳቸው በአጋጣሚ የሆነ ነገር እንዳልሆነ ግልጽ ነው። ይህ ሁሉ እግዚአብሔር ሕዝቡን ለማጥራት ባዘጋጀው ዕቅድ ውስጥ ያለ ነበር።

## ንዑስ ክፍል ሦስት - ማብራሪያ

1. ቤተ መቅደሱ በቅርብ ጊዜ ውስጥ የፍርስራሽ ክምር እንደሚሆን ኤርምያስ ለሕዝቡ ነግሮአቸዋል፤ ኤር. 26:1-6። ሕዝቡም ይህንን ሲሰሙ በጣም ተቆጡ፤ ኤር. 26:7-9። ኤርምያስን ሞት ይገባዋል በማለት ወሰኑ፤ ኤር. 26:10-11። ኤርምያስ ግን ዛቻውን ከምንም አልቆጠረውም ነበር፤ በተቃራኒው ግን ምንም በደል እንዳልፈጸመና ንጹሕ ደም እንዳያፈሱ አሳስቧቸዋል፤ ኤር. 26:12-15። ከዚያም አንዳንድ ሽማግሌዎች በሕዝቅያስ ዘመን ሚክያስ የተባለ ነቢይ ተመሳሳይ መልእክት ሰጥቷቸው እንደነበር በማስታወስ ተናግሯል። በዚያን ጊዜም ነቢይ አድርገው ተቀብለውት ነበር፤ ኤር. 26:16-19። በሌላ በኩል ግን አሪዮ የተባለው ነቢይ ፈርቶ በመሸሹ ገደሉት፤ ኤር. 26:20-24።

2. በዚህ ክፍል እንደሚታየው ሴዴቅያስ በባቢሎን ላይ ያደረገውን ዓመፅ ለመደገፍ መልእክተኞቹ ወደ ኢየሩሳሌም የሄዱ ሲሆን፥ እግዚአብሔር በኤርምያስ አማካይነት ምድራቱን ለጊዜው ለናቡከደነፆር እንዲሰጣት ይገልጽላቸዋል፤ 27:1-7። ሕዝቡም ማመፃቸውን ትተው ለእግዚአብሔር ዕቅድ ራሳቸውን ማስገዛት እንዳለባቸውና ሌላው ነገር ሁሉ ግን ቅጣት እንደሚያስከትልባቸው ያስገነዝባቸዋል፤ 27:8-11። ሴዴቅያስም ተመሳሳይ የሆነ መልእክት ደርሶታል፤ ስለዚህ ራሱን ለናቡከደነፆር ማስገዛት ነበረበት፤ 27:12-15። ካህናትና ሕዝቡም ደግሞ ራሳቸውን ለባቢሎን እንዲያስገዙና ሐሰተኛ ነቢያትን እንዳይሰሙ ተመክረዋል፤ 27:16-22።

3. ሐሰተኛው ነቢይ ሐናንያ ከኤርምያስ በጣም የተለየ ትንቢት ይዞ ብቅ ሲል ይታያል፤ 28:1-4። ኤርምያስም ትንቢቱ ሲፈጸም እርሱ የተናገረው እውነት ይሁን ሐሰት እንደሚረጋገጥ ለሐናንያ አስገንዝቦታል፤ ምክንያቱም የማንኛውም ትንቢት እርግጠኝነትመመዘኛ ይህ ስለሆነ ነው። በመጨረሻም ሐናንያ ቀንበሩን በመስበር ሕዝቡ ነፃ እንደሚወጣ የሚያሳይ ሥዕላዊ ትንቢት በውሸት አቀረበ፤ 28:10-11። እግዚአብሔር ግን በእንጨቱ ቀንበር ፈንታ የብረት ቀንበር ጭኖባቸዋል። ሐናንያም በሠራው ድፍረት ከሁለት ወራት በኋላ ሞቷል፤ 28:12-17። ሐናንያም ኤርምያስን ይዋጉ ከነበሩት ሐሰተኛ ነቢያት መካከል አንዱ እርሱ ነበር።

4. ወደ ባቢሎን የተማረኩት ሰዎች እዚያው መኖሪያቸውን እንዲሠሩ ኤርምያስ ደብዳቤ ልኮላቸዋል፤ 29:1-9። እግዚአብሔርም ወደ አገራቸው የሚመልሳቸው 70ው ዓመታት ከተፈጸመ በኋላ ብቻ እንደሆነ አስገንዝቧቸዋል፤

29:10-14። በኢየሩሳሌም ለነበሩትና የእግዚአብሔርን ቃል ለመቃወም በሚተሩት ሰዎች ላይ ግን ልዩ ፍርድ እንደሚሰጣቸው ተናግሯል፤ 29:15-23። ሽማያም በባቢሎን ሆኖ በኢየሩሳሌም ለሚገኙ ሕዝብና ካህናት ኤርምያስን አስረው ጸጥ እንዲያሰኙት ደብዳቤ ጽፎላቸዋል፤ 29:24-28። ሽማያም የውሸት ትንቢት በመናገሩ እንደሚቀጣ ተነግሮታል። ምክንያቱም ሽማያን እግዚአብሔር አላከውም ነበር፤ 29:28-32።

5. የኤርምያስ አገልግሎት የተሰጠው ለዚያ ዘመን ብቻ ሣይሆን የወደፊቱም ትውልድ እንዲጠቀምበት ጭምር ነው፤ ስለዚህ በጽሑፍ እንዲያሰፍረው ታዟል፤ 30:1-3። አሁን ግን በደረሰባቸው ጭንቀት የተነሣ እግዚአብሔር ያለው ዕቅድ እነርሱን ማዳን እንደሆነ ገልጸላቸዋል፤ 30:4-9። ለሕዙብም እንደሚረዳቸው የተለየ የተስፋ ቃል ይሰጣቸዋል፤ 30:10-11። ሕዝቡም ወደ ምርኮ ሲወሰዱ በጣም ታላቅ ስቃይ ደርሶባቸዋል። ለዚህም የተነሣ ወደ እግዚአብሔርም ጩኸዋል፤ ነገር ግን ይህ ሁሉ የደረሰባቸው ከኃጢአታቸው የተነሣ ነበር። በመጨረሻም እግዚአብሔር በሕዝቡ ላይ ጉዳት የሚያደርሱትን ሰዎች በመቅጣት ሕዝቡን ነፃ የሚያወጣበት ዕቅድ እንዳለው ተናግሯል፤ 30:12-17። ከምርኮ ሊያድናቸውም ያወጣው ዕቅድ ልክ ወደዚያ ሲወሰዳቸው እንዳቀደው ዕቅድ ሰፊ ነበር። ለዘላለም የተረሱ እንደማይሆኑ ተናግሯል፤ 30:18-22። እግዚአብሔር ሕዝቡን በሚያሰቃዩት ሰዎች ላይ ያለው ቁጣ የሚያስፈራ ነው፤ 20:23-24።

6. እግዚአብሔር ሕዝቡን ወደ ባቢሎን ቢያስግርካቸውም እንኳ ጨርሶ አልረሳቸውም፤ 31:1-6። ወደ አገራቸው እንደሚመልሳቸው ተናገራቸው፤ 31:7-9። እግዚአብሔር ተደምሰሶ የነበረውን ነገር በሚያድስበት ወቅት ታላቅ ደስታ ይሆናል፤ 31:10-14። ስለዚህ በባቢሎን የደረሰባቸው ሐዘን የደስታና የሐሴት ዘመን ዋዜማ ነበር፤ 31:15-20። ረዳት የለሽ ከመሆናቸው የተነሣ እግዚአብሔር ያድናቸዋል፤ 31:21-16። ፍጹም ፍትሕ እንደተሰጠ እግዚአብሔር ያረጋግጥላቸዋል፤ 31:27-30። እግዚአብሔርም እንደ ፀሐይና ጨረቃ የጸና ቃል ኪዳን ከሕዝቡ ጋር ሊመሠርት ነው፤ 31:27-37 ስለዚህ የእግዚአብሔር መኖሪያ ሥፍራ በሕዝቡ መካከል መሆኑ የማይቀርና የማይሻር ለመሆን ቻለ።

7. ኤርምያስ ለእርሱና ለኢየሩሳሌም ሕዝብ የተናገረው ቃል ሴዴቅያስ አስተውሏል፤ 32:1-5። ለማረጋገጫም እንዲሆነው ኤርምያስ የቤተሰቡን የእርሻ መሬት እንዲገዛ ተናግሮታል። እግዚአብሔርም ሕዝቡን ከባቢሎን ወደ ይሁዳ እንዲመልስ ያረጋግጥለታል፤ 32:6-15። ኤርምያስም እግዚአብሔር በሚናገረው ነገር ግራ የተጋባ ቢሆንም እንኳ የጸለየው ጸሎት በእግርጠኝነት የተሞላ ነበር፤ ሁኔታው ሙሉ በሙሉ ግልጽ ባይሆንለትም እርሱ ግን

ለእግዚአብሔር ቃል ይታዘዝ ነበር፡ 32፡16-25። በመጨረሻም እግዚአብሔር የሚያደርጋቸውን ሁለት ነገሮች ገልጾለታል። ይኸውም ከሕዝቡ ንጹሕት የተነሣ ከተማይቱን እንደሚያጠፋት ሲሆን ጥቂት ሰዎችን ግን ከባቢሎን ወደ ኢየሩሳሌም መልሶ እንደሚያመጣቸው ነበር፡ 32፡26-44።

## ንዑስ ክፍል አራት - ልዩ ጠቃሚ ነጥቦች

1. ምርኮው በእርግጥ አይፈጸምም የሚል ጥርጣሬ በኤርምያስ አእምሮ ውስጥ አልነበረም። ኤርምያስም ከምርኮ ወደ አገራቸው እንደሚመለሱ ቢነግራቸውም እንኳ መቼ እንደሚማረኩ አልነገራቸውም ነበር፡ 29፡10። ንስሐ የሚገቡበትም ወቅት ያለፈ መስሎ ታይቶአቸው ነበር። ሆኖም ኤርምያስ የመመለስ ተስፋ እንዳላቸው በመናገር ሊያጽናናቸው ችሎአል። እነርሱም ማድረግ የሚችሉት አንድ ነገር ብቻ ነበር፤ ይኸውም፡- እጃቸውን ለባቢሎናውያን ሰጥተው እግዚአብሔር ያመጣባቸውን ቅጣት መቀበል ሲሆን፥ ይህንንም መቀበል እንዲችሉ እግዚአብሔር ጸጋ ሊሠጣቸው ይችላል። በዚያ ወቅትም እንኳ ቢሆን ምሕረት ሊያደርግላቸው ይችል ነበር። ኤርምያስ አገልግሎት በጀመረበት በ627 ዓ.ዓ.ና ኢየሩሳሌም በተደመሰሰችበት ከ586 ዓ.ዓ. መካከል የነበረው ጊዜ ረዘም ያለ ቢሆንም እንኳ ኤርምያስ ንግግሩን አልለወጠም ነበር።

2. ኤርምያስ ጀምሮ እስኪጨርስ በአገልግሎቱ ውስጥ ከተቃዋሚዎቹ ጋር ትግል ነበረበት። ይህም ተቃውሞ ሁለት ነገሮች አሳይቷል አንደኛ ሕዝቡ የኤርምያስን ትንቢት እንዳጣመሙት ጠቁሟል። በዚህም ምክንያት እግዚአብሔር ነቢይ ቢልከላቸውም እንኳ እነርሱ ግን አልተቀበሉትም። ሁለተኛ፥ ደግሞ የእርሱ ፍላጎት እግዚአብሔርን ማገልገል እንጂ ሕዝቡን ማስደሰት እንዳልሆነ ኤርምያስን በመፈተን ማረጋገጫ ሰጥቷል። ሴዴቅያስን የመሳሰሉ ባለስልጣናች ተቃውሞ ሰንዝረውበታል፤ ሐሰተኛ ነቢያት ከሰውታል፤ በቤተ መቅደስ የነበሩ ካህናት ሐሰተኛ የሚል ስም ሰጥተውታል፤ ተራው ሕዝብ እንኳ እርሱን ለመስማትና የእግዚአብሔርን ቃል ለመታዘዝ ፈቃደኛ አልነበሩም።

3. የተረጋገጡ ሁለት ነገሮች ነበሩ፤ እነርሱም፡- በባቢሎናውያን ሠራዊት አማካይነት የሚፈጸመው ጥፋትና ከምርኮ በኋላ የሕዝብ እንደገና መመለስ ናቸው። በኤርምያስ ትምህርት ውስጥ አንድ ነገር ግልጽና የተረጋገጠ ነበር። ይኸውም እግዚአብሔር በ586 ዓ.ዓ. የባቢሎናውያንን ሠራዊት በኢየሩሳሌም ላይ ሊያስነሣ ዓላማው ሕዝብን ለመቅጣት እንደነበር ሲሆን። ሕዝብን ግን ሙሉ በሙሉ ጨርሶ ለማጥፋት ዕቅድ እንዳላወጣ ያሳያል። ኤርምያስ ከምርኩ በኋላ ወደ አገራቸው እንደሚመለሱ ደጋግሞ ተስፋ የሰጠበት ምክንያት ለዚህ ነበር። ይህም ትንቢት በ536 ዓ.ዓ. ፍጻሜ አግኝቷል። ወደ ይሁዳ የተመለሱት ሁሉም ሳይሆኑ እግዚአብሔርን የወደዱ፥ ሊያገለግሉት የሚፈልጉትን፥ ለትንቢቱ ቃል

የታዘዙ ብቻ ነበሩ። በተጨማሪ የኤርምያስ ትንቢት ስለሚፈጸም ሌላ ዓይነት መመለስን ይጠቁም ይሆናል።

## ንዑስ ክፍል አምስት - ከአዲስ ኪዳን ጋር ያለው ዝምድና

1. እግዚአብሔር በኤርምያስ ዘመን እንዳደረገው ሁሉ አሁንም ሕዝቡን ይንከባከባል። በዚህ ዘመንም ትኩረት የሰጠው ለእስራኤል ብቻ ሳይሆን በኢየሱስ የእርሱ ቤተሰብ ለሆኑት ሁሉ ነው። የእርሱም የመጀመሪያ ፍላጎት ሕዝቡን ከጉዳት መጠበቅ አይደለም፤ ነገር ግን እርሱን የሚያንፀባርቅ ሕይወት ይኖሩ እንደሆነ ማየት ነው። ይህንንም የማያደርጉ ከሆነና ከጥፋታቸውም ንስሐ ገብተው ካልተመለሱ አሁንም ይፈርድባቸዋል። ይህ ዓይነቱ ፍርድ የሚጀምረው ከእግዚአብሔር ቤተሰብ ነው። ከዚህም በተጨማሪም ሁላችንም በእግዚአብሔር የፍርድ ወንበር ፊት እንደምንቀርብ ማስጠንቀቂያ ተሰጥቶናል፤ ይህም የሚደረገው እንደ ባዕድ ሳይሆን እንደቤተሰብ አካል ተቆጥረን ነው። የሚሰጠውም ፍርድ ካላመኑት ሰዎች ለየት ያለ ነው።

2. በእግዚአብሔር ሕዝብ ሁሉ የሚደረግ ሕይወትን የማጣራትና የቅጣት ወቅቶች ይኖራሉ። ምክንያቱም የእግዚአብሔር ዕቅድ በእርሱ የተጠሩና የእርሱ የሆኑ ሰዎች እንዲኖሩት ብቻ አይደለም፤ ነገር ግን እርሱን በተሻለ ሁኔታ እንዲያገለግሉት እነርሱን ማጥራትና ማሳደግ ነው። የባቢሎንውያን ምርኮ ቅጣት ነበር፤ በተጨማሪም እግዚአብሔር የእርሱ የሆኑትን ሰዎች ለማጥራትና ለማሳደግ ተጠቅሞበታል። እግዚአብሔር በሕይወታችን ውስጥ የመከራና የፈተና ወቅቶች እንዲፈጠሩ ለምን እንደሚፈቅድ ያስገርመን ይሆናል። ምናልባትም በእነዚህ ወቅቶች እግዚአብሔር የረሳንና የተወን መስሎ ይሰማን ይሆናል። እግዚአብሔር ግን እርሱን በተሻለ ሁኔታ እንድናገለግለው እነዚህን ወቅቶች ከእጁ እንደተሰጡን አድርገን በትዕግሥት እንድንቀበለው ይፈልጋል።

3. የእግዚአብሔር የተስፋ ቃሎች በምንም ዓይነት አይሻሩም። አንዳንድ ጊዜ እግዚአብሔር የረሳን መስሎ ይታየን ይሆናል። በዚህም ሁኔታ ወራትና ዓመታት ልንገፋ እንችላለን፤ በመጨረሻም የእግዚአብሔር የተስፋ ቃል ጨርሶ እውነተኛ ፍጻሜ አያገኝም ማለት እንጀምራለን። በሌላ አንፃር ደግሞ እግዚአብሔር የሰጠውን የተስፋ ቃል እንደሚፈጸም እርግጠኞች ልንሆን እንችላለን። ነገር ግን እግዚአብሔር ተስፋውን እኛ በወሰነው ወቅት ወይም በምንፈልገው መንገድ ላይፈጸም ይችላል፤ ሆኖም የተስፋው ቃል ሁሉ ፍጻሜ ያገኛል። የተስፋው ቃል የተሰጣቸው ሰዎች ሊቀበሉት ባይችሉም እንኳ እግዚአብሔር ሊቀበሉት ለሚችሉ ይሰጣቸዋል። ይኸውም የእግዚአብሔር ቃል ካለው ባሕርዩ ጋር የተጣጣረ በመሆኑ ነው። እርሱ ሊናገር የሚችለው እውነቱን ብቻ ነው። አደርጋለሁ ብሎ የተናገረውን ነገር ያደርጋል። ስለዚህ ነገሩ ፍጻሜ የማያገኝ መስሎ ቢታየንም

እንኳ መጠራጠር አያሻንም፡ ምክንያቱም የእርሱ ቃል ምን ጊዜም እውነት ነው።

## ንውስ ክፍል ስድስት - የክለሳ ጥያቄዎች

1. የኤር. 1ና 52 ይዘት ምንድነው?
2. ኤር. 46-51 የሚያስተምረው ስለምንድነው?
3. ከ586 ዓ.ዓ. በኋላ ስለተፈጸሙ ድርጊቶች የሚነግሩን ምዕራፎች የትኞቹ ናቸው?
4. የኤር. 26-52 አቢይ ትምህርት ምንድነው?
5. በእግዚአብሔር ፍርድ ውስጥ የተገለጸው የእርሱ ልዩ ባሕርዩ ምንድነው?
6. የባቢሎናውያን ምርኮ ሕዝብን የሚያነጻቸው ከምን ዓይነት ኃጢአት ነው?
7. የይሁዳ ሕዝብ በባቢሎን ጠፍቶ እንደማይቀር እርግጠኛ የሆነው ለምን ነበር?
8. ስለ ኢየሩሳሌም ጥፋት የተናገረው የቀድሞ ነቢይ ማን ይባላል?
9. ኦሪዮ ምን ሆነ?
10. ሕዝቡና ንጉሡም ሞምር ራሳቸውን ማስገዛት የነበረባቸው ለማን ነበር?
11. በኤር. 28 ውስጥ ታሪኩን የምናነበው ሐሰተኛ ነቢይ ማን ይባላል?
12. ሽማያ የጻፈው ምን ነበር?
13. በኤር. 30 ውስጥ የሚገኙ ልዩ የተስፋ ቃሎች የሚናገሩት ስለምንድነው?
14. እግዚአብሔር ከሕዝቡ ጋር ስለሚገባው አዲስ ቃል ኪዳን የሚገልጸው ምዕራፍ የትኛው ነው?
15. ሕዝቡ ከባቢሎን እንደሚመለስ የሚያረጋግጠውና እግዚአብሔር ለኤርምያስ የሰጠው መልእክት ምንድነው?
16. ኤርምያስ ለሕዝብ ያስተላለፈው መልእክት ምንድነው?
17. ኤርምያስ ከተለያዩ የጎብረተሰብ ክፍሎች የተቀበለው አፀፋው ምንድነው?
18. ልክ በባቢሎን አግካይነት እንደመጣው ጥፋት መፈጸም የሚያቀረው ነገር ምንድነው?

ንዑስ ክፍል ሰባት - አስተዋፅኦ

ኤርምያስንና አሪዮ - ኤር. 26፡1-24

1-6 - በቤተ መቅደስ የተሰጠ መልእክት

7-9 - በኢየሩሳሌም ላይ የተደረጉ ዛቻዎች

10-11 - የካህናትና የነቢያት ሐሳብ

12-15 - የኤርምያስ መልስ

16-19 - የመሪዎችና የባለስልጣናች መልስ

20-24 - አሪዮ

የተተነበየው ምርኮ - ኤር. 27፡1-22

1-7 - ስለ ቀንበሩ የተነገረው ትንቢት

8-11 - የተሰጠው ትርጉም

12-15 - ለሴዴቅያስ የተሰጠ ቃል

16-22 - ለካህናት የተሰጠ መልእክት

ኤርምያስና ሐናንያ - ኤር. 28፡1-17

1-4 - የሐናንያ ሐሰተኛ ትንቢት

5-9 - የኤርምያስ መልስ

10-11 - ሐናንያ ቀንበሩን ሰበረ

12-17 - ሐናንያ ሞተ

ሐሰተኛ ነቢያት - ኤር. 29፡1-32

1-9 - የኤርምያስ ደብዳቤ

10-14 - የሰባ ዓመታት ምርኮ

15-23 - ሐሰተኛ ነቢያት በባቢሎን

24-28 - ነቢዩ ሼማያ

29-32 - በሽግያ ላይ የተነሣረው ትንቢት

## ከምርኮ መልስ - ኤር. 30፡1-24

1-3 - የመመለሻ ቀን

4-7 - ፍርሐትና ሐዘን

8-11 - ደኅንነት

12-17 - የምርኮው ስቃይ

18-24 - የመመለስ ደስታ

## ለወደፊቱ የተሰጡ የተስፋ ቃሎች - ኤር. 31፡1-40

1-6 - መዝሙሮችና በረከት

7-9 - የተሰበሰበ ብዙ ሕዝብ

10-14 - ደስታና ዝግሬ

15-20 - የእግዚአብሔር ምሕረት

21-26 - የይሁዳ መታደስ

27-30 - የግል ኃላፊነት

31-34 - አዲስ ቃል ኪዳን

35-37 - የማይለወጥ ቃል ኪዳን

38-40 - የከተማይቱ እንደገና መገንባት

## 587 ዓ.ዓ. - ኤር. 32፡1-44

1-5 - ከበባው ተጀመረ

6-8 - የአናምኤል ጥያቄ

9-15 - የእርሻ መሬት መግዛት

16-25 - የኤርምያስ ጸሎት

26-35 - የጌታ መልስ

## ክፍል አራት - ኤር. 33-39

### ንውስ ክፍል አንድ - ታሪካዊ አቀማመጥ

1. ሴዴቅያስ በኢየሩሳሌም የነገሠው ከ598 እስከ 587 ዓ.ዓ. ድረስ ነበር። በእነዚህ ምዕራፎች ውስጥ የእርሱ ስም ብቻ ተጠቅሶ ስለሚገኝ ምዕራፎቹ በሙሉ የሚመለከቱት በ598 ና በ586 ዓ.ዓ. መካከል ያሉትን ዓመታት መሆኑን ግልጽ ነው። እነዚህም ኢየሩሳሌም ከመውደቋ በፊት የነበሩት የመጨረሻዎቹ 12 ዓመታት ናቸው። ኤርምያስም ሕዝቡን በማስጠንቀቅና ዘወትር እግዚአብሔር እንደሚፈልገው አንኖርም ማለታቸውን በማሳየት የእግዚአብሔርን ቸርነት ገለጠ እንጂ ሁሉንም ነገር በዘመን ቅደም ተከተል ለማስቀመጥ አልሞከረም። በአብዛኛው ትንቢቱ ውስጥ የምናገኘው ቅደም ተከተሉን ጠብቆ የሰፈረ ጽሑፍ ሳይሆን ርዕስ ብቻ ነው። ሆኖም በዚህ ሥፍራ የቀረቡት ምንባቦች ወቅቱ ከምን እስከምን እንደሆነ የጊዜውን ገደብ በግልጽ ይጠቁማሉ።

2. እነዚህም ኤርምያስ በኢየሩሳሌም ከተማ ላይ የሰጠው ረጅም አገልግሎት የመጨረሻ ዓመታት ናቸው። ኤርምያስም በኢየሩሳሌም መስበክ የጀመረው በ627 ዓ.ዓ. ነበር። ይህም የሚያሳየው በዚህ ክፍል ውስጥ የሰፈሩት ነገሮች ፍጻሜ ከማግኘታቸው በፊትም እንኳ ለ30 ዓመታት ውስጥ ሁሉ የሰጠው መልእክት አንድ ዓይነት ነበር። በእነዚህ ዘመናት ውስጥ ያገኘው ልምምድ እርሱን ከማስደነቅ ይልቅ አስደንግጦታል። በኢዮስያስ ቀስቃሽነት ይደረጉ የነበረ መነቃቃት የሕዝቡን ልብ ሙሉ በሙሉ አልለወጡም ነበር። በዚህም ምክንያት በአገልግሎቱ መጨረሻ ላይ ልክ በመጀመሪያ ላይ ያደረጉት እንደነበረው ዓይነት ተመሳሳይ መልስ ይሰጡት ነበር፤ ሆኖም ኤርምያስ ተግኝነቱን ይዞ እስከመጨረሻው ጸንቷል።

3. ሴዴቅያስ የሕዝቡን ማንነት የሚያሳይ ምሳሌ ነው። ሴዴቅያስ በኤርምያስ እግካይነት የተሰጠውን የእግዚአብሔርን ቃል አልቀበልም ማለቱን የግል ምርጫ ብቻ እንደሆነ አድርገን እናስብ ይሆናል። ነገር ግን ሴዴቅያስ የሚያንፀባርቀው ሕዝቡን ነው፤ ሕዝቡ ደግሞ የሚከተሉት የእርሱን አርአያ ነው። እንደ ኤርምያስ እግዚአብሔርን ለመታዘዝ ፈቃደኞች ከሆኑ ከጥቂት ሰዎች በስተቀር እግዚአብሔር በእርሱ አማካይነት የሚናገረውን አብዛኞቹ አያምኑም ነበር። ሕዝቡም ከባቢሎን ጋር ለመዋጋት የሚያስፈልጉትን ነገሮች ሁሉ ነበራቸው። ከባቢሎን ጋር በምናደርገው ውጊያ ግብፅ ትረዳናለች የሚል ግምት ነበራቸው። እግዚአብሔርም በእርግጥ ሊቀጣቸው እንደሆነ ማመን ተስኗቸው ነበር።

## ንዑስ ክፍል ሁለት፡ - የነቢዩ ሸክም

1. ሕዝቡ እግዚአብሔር እንደማያውቅ አድርገው በመቁጠርና ስለ ራሳቸው ደንታ እንደሌለው በማሰብ በተደጋጋሚ ኃጢአት ያደርጉ ነበር። እግዚአብሔርም ከእነርሱ ምን እንደሚጠበቅባቸው የሚያውቁበት የቃል ኪዳኑ ሕግ በእጃቸው ነበር። ንስሐ በሚገቡበት ወቅት ይቅርታ ለማድረግ የሚያስችላቸውን ዝግጅት የሚያሳይ መመሪያ በዚሁ ሕግ ውስጥ አስቀምጦላቸዋል። በተለይም ቀደም ባሉት ምዕራፎች ውስጥ ኤርምያስ በተደጋጋሚ ስለሚፈጽሙት ኃጢአት ጠንከር ያለ ዝርዝር ያቀርባል። ኢሳይያስ፥ ኤርምያስ፥ ሕዝቅኤል ኃጢአት ፍርድ እንደሚያስከትል ሕዝቡን ደጋግሙው አስጠንቅቀዋል። ሕዝቡ ግን ኃጢአት መሥራታቸውን የእግዚአብሔርን ቃል ኪዳን እንደማፍረስ አልቆጠሩትም። እግዚአብሔርም የሰጣቸውን ትምህርት ችላ በማለት ከከነዓናውያን ጋር ተደባልቀው ነበር።

2. የባቢሎናውያን ሠራዊት መምጣቱ የማይቀር ነገር ነው። ምክንያቱም የባቢሎናውያን መረራ በአስተዳደር ጉድለት ብቻ የሆነ ተደርጎ የሚወሰድ አይደለም። ከሕዝቡ ኃጢአተኝነትና ከእግዚአብሔር ቅዱስነት ጋር የተያያዘ ነገር ነበር። ኤርምያስ ለይሁዳ የሰጠው ልዩ መልእክት ነበር፤ ይኸውም እጃችሁን ለባቢሎን ስጡ፤ እጃችሁን ከሰጣችሁ የኢየሩሳሌም ከተማ አትደመሰስም የሚል ነበር። ሕዝቡ የኤርምያስን መልእክት እንደ ዓመፅ የቆጠሩት ሲሆን እርሱንም የባቢሎን ሰላይ እንደሆነ አድርገው አስበውት ነበር። በባቢሎናውያን ሠራዊት እጅ እንዳይሰቃይ እግዚአብሔር ሊያስጠነቅቃቸው የላከው ነቢይ መሆኑን ማስተዋል አልቻሉም ነበር።

3. ከትጣቱ በፊን በኋላ እግዚአብሔር ወደ እርሱ ለመመለስ ፈቃደኛ የነበሩትን ሰዎች አድኖአቸዋል። ኃጢአታቸው ቅጣት ቢያመጣባቸውም እንኳ ይህ ግን የመጨረሻ ነገር አይደለም። ምክንያቱም እግዚአብሔር የሰጣቸውን ቃል ኪዳኖች አይረሳም። በመጨረሻም የዳኑት ሰዎች ጥቂት ብቻ ቢሆኑም እንኳ የእግዚአብሔር ሕዝብ እምብርት ሊሆን በቅተዋል። እርሱን የሚወዱትንና የሚያገለግሉትን ቅሬታ ሰዎች ከባቢሎን መልሶ አምጥቷል። ይህም በዘሩባቤል፥ በዕዝራና በነህምያ ዘመን ተፈጽሟል። መሢሑ በሚመጣበት ወቅት እርሱን ለመተባል ተዘጋጅቶ የነበረው ሕዝብም ይህ ነበር። ይህም ዳውሎስ በሮሜ 9-11 ውስጥ አስፋፍቶ ያቀረበው ዋና ትምህርት ነው።

## ንዑስ ክፍል ሦስት - ግብራሪያ

1. በክተማይቱ ላይ ለሚደርሰው ፍርድ መንሥኤ የሆነው ኃጢአትዋ ነው። ሆኖም እግዚአብሔር መልሶ የሚያቋምጠውን ዕቅድ ያወጣል፤ 33፡1-9። በቀድሞ ዘመን የነበሩት ቢረከቶች እንደገና ይሰጣሉ፤ 33፡10-11። ከከተማይቱ ውጭ

ያለው የገጠሩ ክፍል የወታደሮች መስፈሪያ በመሆን ፈንታ እንደገና የእረኞች መሰማሪያ ይሆናል፤ 33:12-13። የሚያድናቸውም ከእስራኤል ውጭ ይመጣል፤ 33:14-16። እግዚአብሔር ለሕዝቡ የገባላቸው ቃል ኪዳናት በሙሉ ይፈጸማሉ፤ 33:17-18። ምክንያቱም የእግዚአብሔር ቃል ኪዳን አይለወጥም፤ 33:19-22፤ የይሁዳ ኃጢአትም እንኳ ቢሆን እግዚአብሔር የአሠራር መንገዱን እንዲቀይር አያደርጉትም፤ 33:23-26።

2. ኤርምያስ ሴዴቅያስን በተደጋጋሚ አስጠንቅቆታል፤ ስለዚህ ቶሎ መሞቱ እንደማይቀር ሌላ ማሳሰቢያ ቢሰጠው አያስደንቅም፤ 34:1-5። በዚህም ወቅት በቁጥጥር ሥር ያልዋሉት ሁለት ከተሞች ለኪስና አዜቃ ብቻ ነበሩ። በኋላም ናቡከደነፆር የተቀሩትን ከተሞች በሙሉ ድል አድርጓቸዋል፤ 34:6-7። ሕዝቡም እርስ በእርሳቸው አንዱ ለሌላው ታማኝ አለመሆናቸው ለእግዚአብሔር ታማኝ እንዳልሆኑ ያሳያል፤ 34:8-11። እጅግ ግልጽ የነበሩትንም ትዕዛዛት ስለማይፈጽሙ አለመታዘዛቸው ይፋ ነበር።

3. ሬካባውያን በኢየሩሳሌም ይኖሩ ከነበሩት አይሁዶች በቁጥር በጣም ትንሽ ነበሩ። ኤርምያስ እነዚህን ሰዎች ያስቀመጠው ያላቸውን ባሕርይ ከሴዴቅያስና ከሕዝብ ባሕርይ ጋር ሲያነፃፅር ነበር። ሬካባውያን በመጀመሪያው ቃለ መሐላ ላይ ጸንተዋል፤ 35:1-11። ይህም በጣም ጥቂት የሆነ ሕዝብ ለመላው ኢየሩሳሌም ምሳሌ ሆኖ ነበር። እነዚህ ሰዎች ያሳዩት ጥሩ ምግባር የመሪያቸውን ትዕዛዝ መታዘዝ ነበር፤ 35:12-17። ሬካባውያን ያደረጉት ነገር እስከዚህም ትልቅ ባይሆንም እንኳ እግዚአብሔር እንደሚባርካቸው ቃል ገብቶላቸዋል፤ 35:18-19።

4. ኤርምያስ የተሰጡትን መልእክቶች ሁሉ በጽሑፍ እንዲያሰፍራቸው በእግዚአብሔር ታዘአል። ይሽውም ለኢዮአቄምና ለወደፊቱ ትውልድ አገልግሎት እንዲሰጡ ነው፤ 36:1-3። የኤርምያስ ረዳት የነበረው ባሮክ እነዚህን መልእክቶች ለሕዝቡና ከዚያም ለሹማምንቱ እንዲያሰማ ተናገረው፤ 36:4-8። ባሮክ ልክ እንደተነገረው አድርጓል፤ 36:9-10። ሹማምንቱም ይህንን ሲሰሙ ወዲያው ንጉሡ በዚህ ነገር እንደሚቆጣ ተረዱ፤ ስለዚህ ለባሮክ እርሱና ኤርምያስን ከኢዮአቄም እንዲሸሽጉ መከሩት፤ 36:11-19። ልክ እነርሱ አስቀድመው እንዳሰቡት ኢዮአቄም መልእክቱን አልቀበልም አለ፤ 36:20-26። ኤርምያስ ነገሩን ሁሉ እንደገና እንዲጽፍ ታዘዘ። እርሱም እንደታዘዘው አደረገ፤ 36:27-32።

5. የኢዮአቄም ልጅ ኢኮንያን ወይም ዮአኪን ጥቂት ወራት ብቻ ከነገሠ በኋላ የኢዮስያስ ልጅ ሴዴቅያስ በእርሱ ፈንታ ነገሠ፤ 37:1-2። የግብፃውያንም ሠራዊት ከባቢሎን ጋር ለመዋጋት ወደ ሰሜን መጡ፤ 37:3-5። ግብፃውያን ስለሚሸነፉ ሴዴቅያስ በእነርሱ እንደማይተማመን ኤርምያስ እንደገና

አስጠንቅቆታል፡ 37:6-10። ሕዝቡም ኤርምያስን እንደ በላይ ስለቆጠሩት ይዘው እስር ቤት አስገቡት፡ ሴዴቅያስም ባዘዘው ትዕዛዝ መሠረት ኤርምያስ የተሻለ ማረፊያ ቤት አግኝቷል፡ ነገር ግን ሴዴቅያስ ከዚህ ምንም ያገኘው ጥቅም አልነበረም፡ 37:16-21።

6. የኤርምያስ መልእክት እስከመጨረሻው አልተለወጠም ነበር። ሕዝቡ እጃቸውን ለባቢሎን መስጠት እንዳለባቸው አሳስቧቸዋል። በዚህም የተነሣ ኤርምያስ ጥቃትና በጉድጓድ ውስጥ መጣል ደርሶበታል፡ 37:1-6። እግዚአብሔር ግን የሚያድነውን ሰው ከውጭ አዘጋጅቶለታል፡ 38:7-13። ሴዴቅያስም እንድ አዲስ ነገር እገኝ ይሆናል ብሎ ኤርምያስን እንደገና አስጠርቶታል 38:11-16። ኤር. 38:17-23 ኤርምያስ ለአርባ ዓመታት ይተነብያቸው የነበሩት ነገሮች ሁሉ ማጠቃለያ ነው። የእርሱ መልእክትም ባጭሩ እጃችሁን ስጡ፡ ትድናላችሁ የሚል ነበር። ሴዴቅያስ እንዲሁም የኢየሩሳሌምና የይሁዳ ሕዝብ በሙሉ መልእክቱን ለመቀበል ፈቃደኞች አልነበሩም፡ 38:24-28።

7. ልክ ኤርምያስ እንደተነበየው ሴዴቅያስ በባቢሎናውያን ተያዘ፡ ልጆቹም ተገዱሉ፡ የእርሱንም ዓይኖች አወጡ፡ 39:1-10። እርሱም በኤርምያስ አማካይነት የተሰጠውን ቃል ቢሰማ ኖሮ ከዚህ ሁሉ ችግር ይድን ነበር። በእርግጥም የባቢሎናውያን ንጉሥ ናቡከደነፆር ኤርምያስን አድኖታል፡ 39:11-14። እግዚአብሔር በኢየሩሳሌም የሚያደርገውን ነገር ከሴዴቅያስና ከአይሁድ መሪዎች ይልቅ ባቢሎናውያን ተረድተው ነበር። አቤሜሌክ ደግሞ ኤርምያስን ለማዳን ሕይወቱን መሥዋዕት ለማድረግ ፈቃደኛ በመሆኑ ከሰይፍ ድኗል፡ ኤር. 39:15-18። በአጠቃላይ እግዚአብሔር በትንሹና በትልቁም ነገር ላይ ያስተላለፈው መልእክት ተፈጽሟል።

## ንውስ ክፍል አራት - ልዩ ጠቃሚ ነጥቦች

1. ሰው ሁሉ ቢቃወመውም እንኳ ኤርምያስ የእግዚአብሔርን ቃል ለመታዘዝ ዝግጁና ፈቃደኛ ነበር። እግዚአብሔር የሰጠውን መልእክት ለሕዝቡ በትክክል ተናግሯል። እርሱ የሚናገረውን ነገር አብዛኛው ሕዝብ እንደማይቀበለውና ኃጢአት ማድረግ ትቶ ወደ እግዚአብሔርን እንደማይመለስ ሊመለከት ችሏል። ሆኖም እርሱ ግን ንግግሩን ከመቀጠል ሌላ ምርጫ አልነበረውም። በሌላ በኩል ደግሞ አብዛኛው ሕዝብ ነፍሰ ገዳይ መሆኑንና እርሱንም ቢገድሉ ምንም እንደማያሰማቸው ቢያውቅም አይፈራቸውም ነበር። ከነገሥታትም ምንም ዓይነት ዕርዳታና ጥበቃ አገኛለሁ ብሎ አይገምትም ነበር። ስለዚህም ለእግዚአብሔር ብቻ ታማኝ በመሆን ትንቢት መናገሩን ቀጥሏል።

2. እግዚአብሔር በነቢዩ ኤርምያስ አማካይነት ተናግሯል፡ በተጨማሪም ሌሎች ደግሞ ከዚህ መልእክት ትምህርት እንዲያገኙበት በጽሑፍ እንዲያሰፍሩው

ታዟል። ኤርምያስ በ586 ዓ.ዓ. ባቢሎናውያን ስለሚያደርጉት ወረራ የተነበየው ባቢሎናውያን ቀጥረውት ወይም በሕዝቡ ላይ ተቆጥቶ አይደለም። ኤርምያስ የጻፈውን ጥቅልሉን መጽሐፍ ንጉሡ ካቃጠለው በኋላ እንኳ እግዚአብሔር እንደገና እንዲጽፍ አዞታል። በባዕድ መንግሥታት ላይ የተነገረው ትንቢት እግዚአብሔር እነዚህን ኃያላን መንግሥታት እንኳ ሳይቀር በቁጥጥር ሥር እንዳደረጋቸው ለእግዚአብሔር ሕዝብ አረጋግጦለታል። ከምርኮም በኋላ ሕዝቡ እግዚአብሔር ታማኝ እንደነበር ለመመልከት ችለዋል።

3. እግዚአብሔር ይህንን ሁሉ ቢያደርግላቸውም እንኳ እርሱ ለማምለጫ ያዘጋጀላቸው መንገድ ነበር፤ እነርሱ ግን አልተቀበሉትም፤ ከተማቸው ልትድን የምትችልበት መንገድ ይህ ብቻ ነበር። እግዚአብሔር ከምሕረቱና ከቸርነቱ የተነሣ በመጨረሻው ወቅትም እንኳ ማምለጫ መንገድ ሰጥቷቸዋል። ማድረግ የሚያስፈልጋቸውም ከባቢሎናውያን እጅ ቅጣት መቀበል ብቻ ነበር። እጃቸውንም ቢሰጡ ኖሮ ይድኑ ነበር። ኃጢአታቸውን ተገንዝበው ቅጣት እንደሚገባቸው ቢያምኑ ኖሮ እግዚአብሔር ይምራቸውና ፍርዳቸውንም ያቃልላቸው ነበር።

## ንዑስ ክፍል አምስት - ከአዲስ ኪዳን ጋር ያለው ዝምድና

1. ፍርድ የእግዚአብሔር ባሕርይ ነፀብራቅ ነው። ይህ እግዚአብሔር ተስማሚ ሆኖ ሲገኝ ከሚያደርጋቸውም ወይም ከማያደርጋቸው ነገሮች መካከል አንዱ ብቻ አይደለም። በአንዳንድ መንገዶች የኢየሱስ ሥራ ከኤርምያስ ጋር ተመሳሳይነት አለው፤ ምክንያቱም ሕዝቡ ንስሐ እንገባም ስላሉ ኢየሱስ ራሱ ደግሞ ስለ ኢየሩሳሌም ጥፋት ተንብዮአል። ኢየሱስም ስለ ኢየሩሳሌም የተናገረው ትንቢት በ70 ዓ.ም. ተፈጽሟል። ከዚህ በኋላ እግዚአብሔር ብዙ ፍርድን በዓለም ላይ ሰጥቷል። የደኅንነት ሥራውንም በኩፈል የሚያከናውነው በፍርድ አማካይነት ነው። ብሉይና አዲስ ኪዳን ሁለቱም የእግዚአብሔር ፈቃድና ዕቅድ ስለሚገልጹ የወደፊት ፍርድ ደግሞ ይናገራሉ።

2. እግዚአብሔር በሕልሞች፥ በራእዮች፥ ወዘተ . . . ቢናገርም እንኳ አብዛኛውን ጊዜ በመልእክተኞቹ ይጠቀማል። ኤርምያስ ለይሁዳ ሕዝብ የእርሱ መልእክተኛ እንዲሆን መርጦታል። እግዚአብሔር ቃሉን ለኤርምያስ ሰጥቶት ስለነበር የተናገረውን ኋላም የጻፈውን ከጌታ የተቀበለውን መልእክት ብቻ ነው። እግዚአብሔር ከኤርምያስ ዘመን አንሥቶ እርሱን የሚያገለግሉና ስለ እርሱ የሚናገሩ ሰዎች መምረጡን አላቋረጠም። የኤርምያስ ታማኝነት በትንቢቱ መፈጸም ተረጋግጧል። የተናገራቸው ነገሮች በሙሉ ተፈጽመዋል። እግዚአብሔር የመረጠው ሰው በመሆኑ እርሱ ሊናገረው የሚፈልገውን ቃል ሰጥቶት ነበር።

3. ከእግዚአብሔር የሚመጣ ቃል ሁሉ ምንጊዜም እውነተኛ ነው። እግዚአብሔር የሚናገረው ነገር ብዙ የተለያዩ ነገሮችን ሊይዝ ይችላል። በትንቢተ ኤርምያስ ውስጥ ብዙ የፍርድ ትንቢቶች ተመልክተናል፤ ሆኖም ይህ እግዚአብሔር የሚናገረው ነገር አንዱ ክፍል ብቻ ነው። በተጨማሪም በዚህ መጽሐፍ ውስጥ የወደፊት በረከቶች ትንቢቶች ተሰጥተዋል። ለሕዝቡ የተሰጡ ማስጠንቀቂያዎችም ይገኛሉ። የምስጋናና የማጽናኛ ቃሎችም ይገኛሉ። እነዚህ ነገሮች የተሰጡት አንዳንድ ጊዜ ለግለሰቦች ሌላ ጊዜ ለእግዚአብሔር ሕዝብና አልፎ አልፎ ደግሞ ለሞላው ዓለም ነው። እግዚአብሔር የሚናገረው ምንም ቢሆን እውነት ነው። የእርሱ ቃል በጭራሽ አይወድቅም፤ ስለዚህ እኛም ልንደገፈውና ልናምንበት ይገባናል።

## ንዑስ ክፍል ስድስት፡- የክለሳ ጥያቄዎች

1. ሴዴቅያስ የነገሠው ከስንት እስከ ስንት ዓ.ዓ. ነበር?
2. አብዛኛዎቹ ትንቢቶች የተቀመጡት በዘመን ቅደም ተከተል ነው? ወይስ በአርዕስት ተከፋፍለው?
3. ኤርምያስ መስበክ የጀመረው መቼ ነው?
4. የሃይማኖት ተሐድሶ ያስጀመረው ንጉሥ ማን ነበር?
5. ሴዴቅያስ የማወክለው ማንን ነው?
6. ይሁዳ ባቢሎንን አሸንፋለሁ ብላ የገመተችው በማን እርዳታ ነበረ?
7. የይሁዳ ሕዝብ ያላቸው የምን ሕግ ነው?
8. ሕዝቡ ለኃጢአታቸው የሰጡት ትርጉም ምን ነበር?
9. የባቢሎናውያንን ሠራዊት በኢየሩሳሌም ላይ ያስነሣባት ማን ነው? ለምን?
10. እግዚአብሔር ከቅጣቱ በኋላ ምን ለማድረግ አቀደ?
11. ሕዝቡ ኃጢአተኛ ቢሆንም እንኳ እግዚአብሔር ያቀደው ምንድነው?
12. በኤር. 34 መሠረት ገና በቁጥጥር ሥር ያልዋሉት ሁለት የገጠር ከተሞች ማንና ማን ነበሩ?
13. ሬካባውያንን በተለይ እንዲያውቁ ያደረጋቸው ነገር ምንድን ነው?
14. ኤርምያስ የመጨረሻዎቹን ማስጠንቀቂያዎች የጻፈው ለየተኛው ንጉሥ ነው?
15. ሴዴቅያስ መታመን የሚፈልገው በየትኛው መንግሥት ነበር?

16. ኤርምያስን ከጉድጓድ ያወጣው ማን ነበር?

17. ታስሮ ወደ ባቢሎን የተወሰደው ንጉሥ ማን ነበር?

18. ኤርምያስ መልእክቱን እንዲጽፍ እግዚአብሔር ያዘዘው ለምንድነው?

19. ሕዝቡ ኤርምያስን ነቢይ አድርገው ተቀብለውታል?

20. ከተማይቱ የምትድንበት ብቸኛ መንገድ ምን ነበር?

21. ፍርድ ከእግዚአብሔር ፍቅር ጋር የማይታረነው ለምንድን ነው?

22. እግዚአብሔር አብዛኛውን ጊዜ የሚናገረው እንዴት ነው?

23. ስለ እግዚአብሔር ቃል የምናውቀው አንድ ነገር ምንድን ነው?

## ንዑስ ክፍል ሰባት - አስተዋፅኦ

### የተስፋ ቃሎችና ትንቢቶች - ኤር. 33፡1-26

1-9 - ስለ ኢየሩሳሌም የተነገረ ትንቢት

10-11 - አስደሳች ከተማ ትሆናለች

12-13 - መንጋዎች ይመለሳሉ

14-16 - መሢሐዊ የተስፋ ቃል

17-18 - መሪዎችና ካህናት

19-22 - የማይሻረው ቃል ኪዳን

23-26 - መሢሐዊ ትንቢት

### ያለመታዘዝ ውጤቶች - ኤር. 34፡1-22

1-5 - ስለ ሴዴቅያስ ሞት የተነገረ ትንቢት

6-7 - ከተሞች በቁጥጥር ሥር ዋሉ

8-22 - የቃል ኪዳኑ መሰበር

### ታማኝ የሆኑ ሰዎች፡- ኤር. 35፡1-19

1-11 - የሬካባውያን መረተኛ

12-17 - የመልእክቱ ይዘት

18-19 - በረከት

## የመልእክቱ በጽሑፍ መስፈር - ኤር. 36፡1-32

1-3 - በጽሑፍ እንዲያሰፍር ተነገረው

4-8 - ባሮክ እንዲያነብ ተነገረው

9-10 - ለሕዝቡ ተነበበ

11-19 - ለሹማምንት የተሰጠ ምክር

20-26 - የንጉሡ ዓፀፋ

27-31 - ኤርምያስ እንደገና እንዲጽፍ ተነገረው

32 ጽሑፉ እንደገና ተጻፈ

## ከንቱ የውጊያ ሙከራ - ኤር. 37፡1-21

1-2 - የሴዴቅያስ ዘመነ መንግሥት

3-5 - የግብፃውያን ሠራዊት

6-10 - በከለዳውያን ድል መሆን

11-15 - የኤርምያስ መወገር

16-21 - የኤርምያስ መዳን

## ሴዴቅያስና ኤርምያስ፡- ኤር. 38፡1-28

1-6 - የኤርምያስ በጉድጓድ ውስጥ መጣል

7-13 - የኤርምያስ መትረፍ

14-16 - ሴዴቅያስ ለኤርምያስ የሰጠው የተሰፋ ቃል

17-23 - ሁለቱ አማራጮች

25-28 - የሴዴቅያስ አፀፋ

## የከተማይቱ መያዝ -ኤር. 39፡1-18

1-10 - የሴዴቅያስ መያዝ

11-14 - የኤርምያስ በነፃ መለቀቅ

15-18 - ለአቤሜሌክ የተሰጠ የተስፋ ቃል

## ክፍል አምስት - ኤር. 40-45

### ንዑስ ክፍል አንድ - ታሪካዊ አቀማመጥ

1. በእነዚህ ምዕራፎች ውስጥ የተጻፉት ነገሮች በሙሉ የተፈጸሙት ከ 586 ዓ.ዓ. በኋላ ነው። ኤርምያስ ሕዝቡን ባስጠነቀቃቸው መሠረት በ 586 ዓ.ዓ. በኢየሩሳሌም ከተማ ላይ የእግዚአብሔር ፍርድ መጣባት። ሕዝቅያስ ንጉሥ በነበረበት ዘመን በ702 ዓ.ዓ. እግዚአብሔር ኢየሩሳሌምን ከአሦራውያን ሠራዊት አድኗታል። እግዚአብሔር ኢየሩሳሌምን እንደሚጠብቃት ቃል ገብቷል፤ ይህም የሚሆነው ሕዝቡ ቃል ኪዳን ማክበር እስካላቋረጡ ብቻ ነበር። በሕዝቅኤል መጽሐፍ እንደምናየው ግን ሕዝቡ ኃጢአት ማድረጋቸውን ቀጠሉ፤ ስለዚህ ከተማይቱ ተደመሰሰች። በዚህ ወቅት ኤርምያስ በከተማይቱ ውስጥ ነበር ኢየሩሳሌም ከተደምሰሰችና የባቢሎናውያን ሠራዊትም ወደ ባቢሎን ከተመለሰ በኋላ እርሱ በይሁዳ ነበር፤ የተደረገውንም ነገር በዓይኑ ተመልክቶታል።

2. ከዚህ ጽሑፍ ጋር ጎን ለጎን የሚሄድ ምንም ሌላ ጽሑፍ የለም። ከዚህ ታሪክ ጋር ተመሳሳይ የሆነ ነገር የሚናገር የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል አናገኝም። ኤርምያስ ግን ይህ ነገር ሲፈጸም በዚያው ስለነበር የተደረገውን ነገር ሁሉ ሊመዘግብ ችሏል። 2ኛ ነገሥትና 2ኛ ዜና ስለ ከተማይቱ መደምሰስ ይናገራሉ፤ ሆኖም ሕዝቡ ከዚያ በኋላ ምን እንደሆኑ አይነግሩንም። ስለዚህ እነዚህ ስድስት ምዕራፎች ልዩ ስለሆኑ በጥንቃቄ መጠናት ይኖርባቸዋል። ወደ ባቢሎን የሄዱት ሰዎች ምን እንደደረሰባቸው በጥቂቱ ከትንቢተ ዳንኤል እንረዳለን። በኋላ በተመለሱት ሰዎች ላይ ምን እንደደረሰባቸው ከሐጌ፥ ከዘካርያስ፥ ከዕዝራና ከነህምያ መጻሕፍት በጥቂቱ እንረዳለን። በይሁዳ ስለቀሩት ሰዎች ግን ሊነግረን የሚችለው ጸሐፊ ኤርምያስ ብቻ ነው።

3. ይህ ክፍል ወደ ግብፅ ስለሄዱት ሰዎች ይነግረናል ናቡከደነፆር ብዙ ሰዎችን ወደ ባቢሎን የወሰደ ሲሆን ሌሎች ደግሞ በይሁዳ ቀርተዋል። የተወሰዱት ሰዎች ለምን የመጥፋት ሙከራ እንዳደረጉና ወደ ግብፅ እንደሸሹ በኤር. 40-45 ውስጥ ተገልጿል። በኋላም ልክ ኤርምያስ እንደተነበየው እግዚአብሔር ናቡከደነፆርን ወደ ግብፅ እንደላከው ታሪክ ይነግረናል። ወደ ግብፅ የሄዱት ጥቂት አይሁዶች በዚያ ቤተ መቅደስ ሠርተው የአይሁድን ጎብረተሰብ ለማቋቋም ሙከራ

አድርገዋል። የሄዱት የእግዚአብሔርን በረከት ይዘው ቢሆን ኖሮ ድርጊታቸው ይሳካላቸው ነበር። ያም ባለመሆኑ ወደዚያ ሄደው የነበሩት ሰዎች በእግዚአብሔር ቃል ውስጥ ተጽፎ እንደሚገኘው ሆኖባቸዋል።

## ንዑስ ክፍል ሁለት - የነቢዩ ሸክም

1. ሕዝቡ የነበራቸው ከፉ ድርጊት ከእግዚአብሔር ጥበቃ አርቋቸዋል። ይህም ከፍል ምንም መልካም ዜና የለውም። በኢየሩሳሌም ላይ የተወሰነው ቅጣት ፍጻሜ አግኝቷል። በዚህ ክፍል እንደምናየው በይሁዳ አንዳንድ ቦታዎችን የሚጠብቁ የባቢሎን ወታደሮች ስለነበሩ የሚቀበሉት ቅጣት ከበድ ያለ ነበር፤ ሆኖም እነርሱ ግን እግዚአብሔርን ለመታዘዝ ፈቃደኛ አልነበሩም። ከእርሱ ፍርድም እናመልጣለን የሚል ግምት ነበራቸው። እንደፈለጉ ቢሠሩም እግዚአብሔር አያየንም ብለው ይገምቱ ነበር። በምርኮ ያልተወሰዱት ሰዎችም እንኳ ቢሆን ልባቸው አልተለወጠም ነበር። ራሳቸውንም ለእግዚአብሔር ለመስጠት ፈቃደኞች አልነበሩም።

2. ጥበቃ እንዲደረግላቸው ያቀረቡት ልመና የይስሙላ ብቻ ነበር። የእግዚአብሔር ሕግ ለመከተል ምንም ፍላጎት አልነበራቸውም። ምንም እንኳ ልቦናቸው ጠንካራ ቢሆንም እግዚአብሔር ልመናቸውን ሰምቶአል። በተጨማሪም ኤርምያስ ስለ እነርሱ ላቀረበው ጥያቄ እግዚአብሔር መልስ ሰጥቶታል። በኤርምያስ አማካይነት ወደ ግብፅ እንዳይሄዱ ተናግሯቸዋል። በይሁዳ ቢቆዩና እርሱንም ለመታዘዝ ፍቃደኛ ቢሆኑ እግዚአብሔር እንደሚያድናቸው የተስፋ ቃል ሰጥቷቸው ነበር። እነርሱ ግን ይህንን ለማድረግ ፈቃደኛ አልነበሩም። ኤርምያስ ማድረግ የሚችለው ነገር ቢኖር እግዚአብሔር የተናገራቸውን ቃል ማስተላለፍ ብቻ ነበር። በግብፅም እንኳ ቢሆን እግዚአብሔር በኤርምያስ አማካይነት የሰጣቸውን ቃል አይታዘዙም ነበር።

3. እግዚአብሔር ለጸሎታቸው መልስ ሲሰጣቸው እነርሱ ለመታዘዝ እምቢተኞች ነበሩ። ይህም ለእግዚአብሔር ቃል ያላቸውን ንቀት ያሳያል። ኤርምያስ እርሱ ከእግዚአብሔር የተላከ ነቢይ መሆኑንም አረጋግጠላቸዋል። ስለ ኢየሩሳሌም ነግሮአቸው የነበረው ነገር እውነተኛ መሆኑ ተረጋግጦ ነበር። ይህም እነርሱ ራሳቸው በዓይናቸው የተመለከቱት ነገር ነበር። ወደ ግብፅ ስለ መሄድ እግዚአብሔር ምን እንዳለ ኤርምያስ ነግሮአቸዋል። የዚህ ጉዞ ውጤት ውድቀት እንደሆነ ሰምተዋል። እዚያም ሄደው ሊድኑ እንደሚችሉ ተነግሮአቸው ነበር፤ እነርሱ ግን ይህንን የእግዚአብሔርን ቃል አንቀበልም አሉ። የኤርምያስንም መልእክት ችላ ብለው ወደ ግብፅ ሄደው በመሸሸግ ራሳቸውን ለማዳን ጥበቃ ለማግኘት ሞከሩ። ናቡከደነፆርም ሄዶ በቁጥጥሩ ሥር እንዲያደርጋቸው

እግዚአብሔር ላከው ሙከራቸውም በውድቀት አበቃ።

## ንዑስ ክፍል ሦስት - ማብራሪያ

1. በኤር. 39 ውስጥ የይሁዳ የመጨረሻ ንጉሥ ሴዴቅያስ ወደ ባቢሎን እንደተወሰደ ተመልክተናል። ሆኖም ብዙ አይሁዶች በይሁዳ ቀርተዋል፤ ከእነርሱም መካከል አንዱ ኤርምያስ ነበር። እርሱም ኢየሩሳሌምን ትቶ የተቀሩትን አይሁዶች ወደሰፈሩበት ወደ ምጽጳ ሊኖር ወደዚያ ሄደ፤ 40:1-6። ሌሎቹ ሰዎች ደግሞ የዚህን ሥፍራ መኖር ሲሰሙ ከተለያዩ ሥፍራዎች መጥተው በምጽጳ ሰፈሩ፤ በእነርሱም ላይ የተሾመው ጎዶልያስ ነበር፤ 40:7-12። በዚህ ወቅት ሁለቱ የጎዶልያስ ጠላቶች ዮሐናንና እስማኤል ተነሡ። በዚህ ጊዜ ጎዶልያስ ጥንቃቄ ማድረግ ነበረበት፤ ስለዚህም ዮሐናን የነገረውን ነገር አልቀበልም አለ፤ 40:13-16። ይህም የሚያሳየው በይሁዳ ይኖሩ የነበሩት እንኳ አርፈው ለመቀመጥና በሰላም ለመኖር ፍቃደኞች አለመሆናቸውን ነው።

2. ኢየሩሳሌም በወደቀች በዘጠነኛው ወር የሴዴቅያስ ዘመድ የሆነው እስማኤል ምጽጳን ወረረ፤ 41:1-3። እስማኤልና የእርሱ ተባባሪ የነበሩ አሥር ሰዎች ጎዶልያስን በምጽጳ ይኖሩ የነበሩትን አይሁዶችና በዚያ ይኖሩ የነበሩትን የባቢሎንን ወታደሮች ገደሉ። ከሴኬም፥ ከሴሎና ከሰማሪያ ከመቶ ሰማንያ እንግዶች መካከል ሰባዎቹ ታረዱ፤ 41:4-8። እስማኤልም ሰባዎቹን ሰዎች ከቀበረ በኋላ የተቀሩትን በእስረኛ መልክ ይዞ ወደ ዓሞን ተመለሰ፤ 41:9-10። ዮሐናንም እስማኤልን ተከትሎ በመሄድ እስረኞቹን አዳናቸው። በገባዖን በተደረገው ጦርነት በኋላ ወደ ግብፅ ለመሄድ ዝግጅት ወዳደረጉበት ወደ ቤተልሄም አካባቢ ተመለሱ፤ 41:11-18።

3. ከዚያ በኋላ ሕዝቡ በእውነት የእግዚአብሔርን ምሪት የሚፈልጉ መስለው ወደ ኤርምያስ መጡ። ኤርምያስ የሚጠይቃቸውንም ለመታዘብ ማሉ፤ 42:1-6። ኤርምያስም መልስ ለመስጠት አሥር ቀን ከቆየ በኋላ ሕዝቡ በይሁዳ እንዲቆዩ እንጂ እንዳይኮበልሉ እግዚአብሔር እንደሚፈልግ ነገራቸው። እንዲሁም እግዚአብሔር ወደ ግብፅ እንዳይሸሹ በዚያው ወቅት አስጠነቀቃቸው። ወደ ግብፅ በመሄድ ዋስትና እንደማያገኙ ተናገራቸው 42:7-17። እነርሱ ግን አስቀድመው ወደዚያ ለመሄድ ወስነው ስለነበር ወደ ግብፅ በሚሄዱት ሰዎች ላይ የሚደርስባቸው ፍርድ ምን ዓይነት እንደሆነ በተጨማሪ ተገልጾአል፤ 42:18-22።

4. ወደ ግብፅ ስለሄዱት ሰዎች የሚነግረን ኤር. 43 ብቻ ነው። በ722 ዓ.ዓ. ወደ አሦርና በ586 ዓ.ዓ. ወደ ባቢሎን ስለተወሰዱት ሰዎች እናውቃለን። እዚህ ደግሞ ወደ ግብፅ ስለሄደ ስለ አንድ የተወሠነ ሕዝብ እናነባለን። ከዚህ ሕዝብ መካከልም ይበልጡ ወደ ግብፅ የሄዱ ይመስላል። እነዚህም ሰዎች ኤርምያስና

ባሮክ እነርሱን የተቃወሙአቸው መስሎ ታይቷቸው ነበር፤ 43:1-7። ጣፍናስ ወደ ግብፅ በሚወስደው ጠረፍ ላይ የምትገኝ ትንሽ ከተማ ነበረች። በ568 ዓ.ዓ. በፈርዖን አማሲስ ዘመነ መንግሥት ናቡከደነፆር ግብፅን ድል አደረጋት። በቁ. 13 ውስጥ የተጠቀሰችው ከተማ ከካይሮ በስተሰሜን ምሥራቅ 10 ኪሎ ሜትሮች ርቃ የምትገኝ ከተማ ነበረች። ግብፅ የማያሰጋ መጠጊያ ልትሰጥ አልቻለችም።

5. ወደ ግብፅ የሄዱት አይሁዶች ይኖሩ የነበረው ቢያንስ በአራት የተለያዩ ስፍራዎች ነበር። ይህም ሆኖ ሁሉም ጥሩ ምግባር አልነበራቸውም ነበር እግዚአብሔርም በይሁዳ ካደረገው ነገር ምንም አልተማሩም ነበር፤ 44:1-10። ከዚህም የተነሣ እግዚአብሔር በግብፅ ሳሉ ሊቀጣቸው ወሰነ። ልክ በአይሁድ የነበሩትን ሰዎች እንደጠፉ ሁሉ ወደ ግብፅ ሄደን ልንተርፍ እንችላለን ብለው የገመቱትንም ሰዎች እግዚአብሔር እንደሚያጠፋ ተናገረ፤ 44:11-14። በጳጥሮስ የነበሩት አይሁድ ለመስማት እንቢተኛ ከመሆናቸውም በላይ እንደቀድሞው ኃጢአት መሥራታቸውን ቀጠሉ። በተጨማሪም የባዕድ መሥዋዕቶችንም ማቅረብ ቀጠሉ፤ 44:15-19። ኤርምያስ እግዚአብሔር ለምን ይሁዳንና ኢየሩሳሌምን እንደደመሰሰ ሕዝቡ እንዲያስታውሱ ያሳስባቸዋል፤ 44:20-23። እግዚአብሔር የተናገረውን ነገር እንደሚፈጽም የሚያሳይ ምልክት ለሕዝቡ ሰጣቸው፤ ስለዚህ የግብፅ መሸነፍ በአጋጣሚ የሆነ ነገር እንዳልሆነ በመጨረሻ ይገነዘባሉ፤ 44:24-30። ባሮክ የኤርምያስን መልእክቶች አብጠርጥሮ ተረድቶ ነበር። እግዚአብሔር ልዩ መጽናኛም ሰጥቶታል። ቀድሞ የገነባው እርሱ እንደሆነና አሁንም ደግሞ የሚያፈርሰው እርሱ ራሱ መሆኑን ለባሮክ እግዚአብሔር አሳውቆታል። ስለዚህ ይህ መንኮታኮት በእግዚአብሔር ቁጥጥር ሥር እንደነበር አውቆአል። በዚህ ሁሉ ውስጥ ግን እግዚአብሔር ባሮክን ለመከላከልና ለመጠባበቅ አብሮት ነበር። እግዚአብሔር የግል እንክብካቤ እንደሚያደርግለት የተስፋ ቃል ተሰጥቶት ነበር።

## ንዑስ ክፍል አራት - ልዩ ጠቃሚ ነጥቦች

1. በእነዚህ ስድስት ምዕራፎች ውስጥ እግዚአብሔር ለሕዝቡ ቸር ስለመሆኑ ብዙ ምሳሌዎች እናገኛለን እግዚአብሔርም ተስፋ ቆርጦ ለነበረው ለባሮክ የተለየ በረከት እንደሰጠው እናያለን፤ ምዕ. 45 ባቢሎናውያን ይሁዳን በወረሩበት ወቅት እግዚአብሔር ለኤርምያስ ጠባቂና ከለላ ሆኖታል። ኤርምያስም ከኢየሩሳሌም በስተሰሜን 40 ኪ.ሜ. ወደምትርቀው ምጽጳ ሊኖር ሄዷል፤ 40:1-6። ምንም እንኳ ሕዝቡ በእውነት የእግዚአብሔርን ምሪት ለመከተል ፈቃደኛ ባይሆንም እግዚአብሔር የኤርምያስን ጸሎት ሰምቶ ምን ግድረግ እንደሚገባቸው ነግሮአቸው ነበር፤ 42:7-17። በመጨረሻም ወደ ግብፅ የሄዱት ሰዎች ትልቅ ስሕተት መሥራታቸውን የሚጠቁም ምልክት

እግዚአብሔር ሰጥቷቸው ነበር፤ 44:24-30። ምክንያቱም ግብፅ እራሱዋ ፍርድ ሊመጣባት ስለሆነ ለእነርሱ መጠጊያ ልትሆናቸው አትችልም ነበር።

2. ዮሐናንና እስማኤል ሁለቱም የጎዶልያስን ሹመት ሳይፈልጉ አይቀሩም። ዮሐናንም የእስማኤልን ሴራ በመስማት ጎዶልያስ እርሱን እንዲገድለው አሳስቦት ነበር። ያም ባለመሆኑ የኢየሩሳሌም በተያዘች በሦስተኛው ወር እስማኤል ሴራ ጠንሰሶ ጎዶልያስን ገደለው። ከዚያም ሀያ ሰዎችን ጨምሮ ገደለ። በተጨማሪም በምጽጳ የነበሩት የባቢሎን ወታደሮች ተገደሉ። በዚህ ወቅት ኢየሩሳሌም ባዶ ሳትሆን አትቀርም። ኤርምያስም እንደቀድሞው «እዚህ ቆዩ፤ እግዚአብሔር ከለላ ይሆናችኋል» የሚል መልእክት ቢያስተላልፍላቸውም እንኳ የእግዚአብሔርን ቃል ስላላመኑ ኮብልለዋል።

3. እግዚአብሔር በኤርምያስ አማካይነት ስለ ኢየሩሳሌም መደምሰስ ለብዙ ዓመታት ይናገር ነበር። ይህም ለሕዝቡ ትምህርት እንዲሆን በማለት ነበር፤ 44:1-10። በተጨማሪም እግዚአብሔር በግብፅ ላይ ስለሚደርሰው ፍርድ በኤርምያስ አማካይነት ተናግሯል፤ 42:18-22፤ 44:11-14 ና 24-30። እግዚአብሔር የሚገደው ስለይሁዳና ስለ ኢየሩሳሌም ብቻ አይደለም። ዓለም ሁሉ ጭምር በእርሱ ቁጥጥር ሥር ነው። በዚህ ክፍል የተጠቀሰውም ሕዝብ ራሳቸው ወደ ግብፅ ሄደው በመሸሸግ ከእግዚአብሔር ፍርድ ሊያመልጡ አልቻሉም። ለዚህም እግዚአብሔር በኤርምያስ አማካይነት ወደዚያ እንዳይሄዱ ነግሯቸው ነበር፤ 42:7-17። ሆኖም እነርሱ ለመስማትና ለመታዘዝ ፈቃደኛ አልሆኑም። በዚህም ምክንያት ናቡከደነፆር ልክ ኢየሩሳሌምን ወሮ እንዳጠፋት ሁሉ በጣፍናስም ላይ ተመሳሳይ ድርጊት እንደሚፈጽምባት ተናግሯል፤ 43:8-13።

## ንዑስ ክፍል አምስት፡- ከአዲስ ኪዳን ጋር ያለው ዝምድና

1. ከምዕ. 40-45 ባለው ክፍል ውስጥ እግዚአብሔር ፈቃዱን ለተለያዩ ቡድኖች ሲነግርና ሲገልጽ እንመለከታለን። ለምሳሌ ሕዝቡ ወደ ግብፅ እንሂድ ወይስ አንሂድ ብለው ወደ ኤርምያስ ጥያቄያቸውን ሲልኩ እግዚአብሔር መልስ ሰጥቷቸዋል፤ 42:7-17። ይህንንም ያደረገው ጥያቄያቸው ቅን እንዳልሆነ እየታወቀ ነበር። ግብፅ ሲደርሱም እግዚአብሔር እንደገና በዚያ ስላሉት ሁኔታዎች ነግሯቸዋል። ምዕ. 44 የሚያሳየው በአጠቃላይ በግብፅ ለነበሩት ሰዎች የተሰጠውን የእግዚአብሔርን ቃል ነው። እነዚህም ሰዎች ርቀው ቢሄዱም ግምለጥ አልቻሉም። በመጨረሻም በምዕ. 45 ውስጥ ተስፋ ቆርጦ ለነበረው ለባሮክ የተለየ ቃል ሲናገር እናያለን። እግዚአብሔርም ልዩ እንክብካቤ እንደሚያደርግለት አሳስቦታል።

2. የተፈፀሙት ፍርዶች በሙሉ በእግዚአብሔር ቁጥጥር ሥር ነበሩ። ይሁዳን ያጠፋቸውና ግብፅን የቀጣቻት ባቢሎን ሳትሆን እግዚአብሔር ራሱ ነበር። በ70

ዓ.ም. በኢየሩሳሌም ላይ የተፈጸመው እንደዚሁ ነው። ኢየሩሳሌምን የደመሰሰቻት ሮም ሳትሆን እግዚአብሔር ነበር። እነዚህ ፍርዶች በሙሉ በእግዚአብሔር እጅ ውስጥ ነበሩ። በኤርምያስና እንዲሁም በአዲስ ኪዳን ዘመናት እርግጠኛ የነበሩት ነገሮች በአሁኑም ዘመን ደግሞ እንደዚያው ናቸው። ፍርድ፣ እግዚአብሔር ራሱ በነገሮች ውስጥ በቀጥታ ላልቃ በመግባቱ የሚሆን ነገር ነው። ሰዎች ግን ፍርድን በተፈጥሮ ግዴታ ብቻ እንደሚከሰት አድርገው በግሰብ ይሳሳታሉ።

3. እግዚአብሔር ሕዝቡን ሁሉ ቢጠብቅም እንኳ እርሱን ማገልገልና ማስደሰት ለሚፈልጉት ደግሞ ልዩ እንክብካቤ ያደርግላቸዋል። እግዚአብሔር ለኤርምያስ ልዩ እንክብካቤ እንደሚያደርግለት ቃል ገብቶለት ነበር። ስለዚህ ባቢሎናውያን ባካሄዱት ወረራ ውስጥ ሁሉ አንድም ነገር አልደረሰበትም። ያም በመሆኑ ባቢሎናውያን ከእሥራቱ ፈቱት፣ እርሱም በምጽጳ ተቀመጠ። እግዚአብሔር የሚናገራቸውን ለማድረግ እውነተኛ ፍላጎት ሳይኖራቸው ጥያቄ ላቀረቡት ሰዎች እንኳ መልስ ሰጥቶአቸዋል፤ 42:7-17። ለባሮክም ልዩ መጽናኛ ተሰጥቶታል፤ ምዕ. 45። ለመታዘዝ እጅግ እምቢተኞች የነበሩትንም እንኳ ጨርሶ አልረሳቸውም ነበር፤ እግዚአብሔር መጽናኛና ብርታት ሰጥቶአቸዋል።

## ንዑስ ክፍል ስድስት-የክለሳ ጥያቄዎች

1. በኤር. 40-45 የተጠቀሱት ነገሮች የተፈጸሙት መቼ ነበር?
2. በ702 ዓ.ዓ. እግዚአብሔር ምን አደረገ?
3. ኤር. 40-45 ልዩ የሆነው ለምንድነው?
4. ኤር. 40-45 የሚነግረን ስለ ምንድነው?
5. 2ኛ ነገሥትና 2ኛ ዜና በውስጣቸው የያዙት ታሪክ ስለ ምንድነው?
6. በምጽጳ የነበሩት የማን ወታደሮች ነበሩ?
7. ሕዝቡ መኮብለል የሚፈልጉት ወዴት ነበር?
8. ጎዶልያስ ማን ነው?
9. እስማኤል ሊገድለው እንደፈለገ ለጎዶልያስ ማን ነገረው?
10. እስማኤል ጎዶልያስን የገደለው የት ነው?
11. እስማኤልን አሳዶ ጥቂት እሥረኞችን ያስለቀቀው ማን ነበር?
12. ዮሐናንና ጓደኞቹ መሄድ የሚፈልጉት የት ነበር?

13. ናቡከደነፆር ግብፅን ድል ያደረጋት መቼ ነበር?

14. በጳትሮስ የነበሩት ሰዎች በተደጋጋሚ ያደረጉት ነገር ምንድነው?

15. ኤር. 45 የተጻፈው ለማን ነበር?

16. ኤርምያስ ስለ ግብፅ የተናገረው ነገር ምንድነው?

17. ስለ ሕዝቡ ሐሰተኛ ጥያቄ የሚናገረው ምዕራፍ የተኛው ነው?

18. ኤር. 41 የሚያወራው ባጭሩ ሲጠቃለል ስለምንድነው?

19. እግዚአብሔር በምዕ. 42 ውስጥ የሚናገረው ምንድነው?

20. ኤርምያስ ምዕ. 44 ውስጥ ያለውን መልእክት የተናገረው የት ሆኖ ነበር?

## ንዑስ ክፍል ሰባት - ኧስተዋፅኦ

## የናቡከደነፆር ጉዞ - ኤር. 40፡1-16

1-6 - የኤርምያስ ተፈትቶ ወደ ምጽጳ መሄድ

7-12 - የሕዝቡ ወደ እርሻው መመለስ

13-16 - ዮሐናን ለእስማኤል የሰጠው ማስጠንቀቂያ

## የጎዶልያስ መሞት - ኤር. 41፡1-18

1-3 - እስማኤል ምጽጳን ወረረ

4-8 - ከሴኬም፣ ሴሎና ሰማሪያ የመጡት 70 ሰዎች መገደል

9-10 - የእስማኤል ምርኮኞች

11-18 - የተረፉት ሰዎች ወደ ግብፅ ለመሄድ በገባዖን ያደረጉት ዝግጅት

## ከልብ ያልሆነ ጥያቄ - ኤር. 42፡1-22

1-6 - ስለ ምሪት የተጠየቀው ጥያቄ

7-17 - እግዚአብሔር የሰጠው መልስ

18-22 - ወደ ግብፅ በሄዱት ሰዎች ላይ የሚደርስ ፍርድ

ወደ ግብፅ የተደረገው ጉዞ - ኤር. 43:1-13

1-7 - ወደ ግብፅ ያደረጉት ጉዞ

8-13 - ናቡከደነፆር በጣፍናስ ላይ ያደረገው ወረራ

በግብፅ የተሰጠው ትንቢት - ኤር. 44:1-30

1-10 - ለይሁዳ የተሰጠው ማስጠንቀቂያ

11-14 - በግብፅ ላይ የተሰጠው ፍርድ

15-19 - የጸትርስ ሰዎች መልስ

20-23 - ያለ መታዘዝ ውጤቶች

24-30 - ለሕዝቡ የተሰጠ መልእክት

ለባርክ የተሰጠ ቃል - ኤር. 45:1-5

1-5 ለባርክ የተሰጠው ልዩ የማጽናኛ ቃል።

## ክፍል ስድስት - ኤር. 2-6

### ንዑስ ክፍል 1 - ታሪካዊ አተገባበር

1. በተቀረው የመጽሐፉ ክፍል እንደተመለከትነው ኤርምያስ ትንቢት ስለተናገረበት ዘመን በቂ ሐሳብ አግኝተናል። ኤርምያስ አገልግሎቱን ያበቃው ኢየሩሳሌም ከመደቀቅ በኋላ በግብፅ ነበር። አውን ደግሞ ከተማይቱ ከመደምሰሱ በፊት ኤርምያስ ለይሁዳና ለኢየሩሳሌም ሕዝብ የተናገራቸውን ነገሮች እንመለከታለን። የኤርምያስ መጽሐፍ ታሪኩን በሰፈው አያቀርብልንም። ሆኖም በነገሥትና በዜና መጻሕፍት ውስጥ ታሪኩን እናገኛለን። በትምህርት አንድ ውስጥ ም. አንድን ተመልከተን ኤርምያስ መተንበይ ስለጀመረበት ዘመን አንዳንድ ነገሮች ተነጋግረናል። በዚህ አምስት ምዕራፎች ውስጥ የምናገኘው ጽሑፍ በመጽሐፉ መጨረሻ ካለው ፍጹም የተለየ ነው፤ በዚህ ክፍል ውስጥ ምንም ታሪክ አናገኝም።

| | | | |
|---|---|---|---|
| 640 ዓ.ዓ. | ——— | ኢዮስያስ ነገሠ | የኢዮስያስ አያት ምናሴ ነበር። 2ኛ ነገ. 21:1-18 ና 2ኛ ዜና 33:1-20 አንብቡ። |
| 627ዓ.ዓ. | ——— | ኤርምያስ የትንቢት አገልግሎቱን ጀመረ | አባቱ ደግሞ ኃጢአተኛው ንጉሥ ዓምን ነበር። 2ኛ ነገ. 21:19-26 ና 2ኛ ዜና 33:21-25 አንብቡ። |
| 622 ዓ.ዓ. | ——— | 1ኛ ነገ.22:3 | ዓምን የሞተው ኢዮስያስ ገና የ 8 ዓመት ልጅ ሳለ ነው። |
| 609 ዓ.ዓ. | ——— | ኢዮስያስ ሞተ | ሲሞት እድሜው 39 ነበር። |

18 ዓመታት 13 ዓመታት

2. ኢዮስያስ ሕዝቡ ከባዕድ ሃይማኖቶች የወረሷቸውን እንዳንድ ነገሮች ለማጥፋት ችሎ ነበር። 2ኛ ነገ. 22-23 ና 2ኛ ዜና 34:35ን በጥንቃቄ አንብቡ። ይህ ነገር የተፈጸመው ኤርምያስ ለአገልግሎት በተጠራ በ5ኛው ዓመት ቢሆንም እንኳ እርሱ በትንቢቱ ውስጥ በፍጹም አልጠቀሰውም። ምክንያቱም ኤርምያስ ሕዝቡ ውጫዊ ነገራቸው ብቻ እንጂ ልባቸው በጭራሽ እንዳልተለወጠ በመገንዘቡ ይሆናል፤ ያም ቢሆን ኢዮስያስ ያዘዛቸውን ነገሮች መፈጸም አስፈላጊ ነበር። ሆኖም ይህ ብቻ በቂ አልገበረም። የሕዝቡ ልብ ካልነጻ እግዚአብሔር ሊባርካቸው አይችልም፤ ዘወትር ከኃጢአት ጋር ትን ለትን የሚሄደውም ፍርድ ሊመጣ አይችልም። ኤርምያስ ለሕዝቡ ያተረበው ልመና ይህ ነበር።

## ንዑስ ክፍል ሁለት - የነቢዩ ሸክም

1. ታማኝነት - ሕዝቡ ከእግዚአብሔር ጋር ቃል ኪዳን ገብቷል፤ እንዲሁም እግዚአብሔርም ከእነርሱ ጋር ተመሳሳይ ድርጊት ፈጽሟል። ሕዝቡም ለእርሱ ታማኝ መሆን የነበረባቸው ከዚህ የተነሣ ነበር። ታማኝ ማለት ለተናገሩት ቃል እውነተኛ መሆን ማለት ነው። ሕዝቡ እግዚአብሔርን ለመከተልና ለመታዘዝ ከተስማሙ በኋላ በመጨረሻ ባዕድ አምላኮችን በመከተል ከከነዓናውያን ሃይማኖት ውስጥ ተዘፍቀዋል። ከዚህም ባሕርይ ያገኙት ነገር ቢኖር የእግዚአብሔርን ፍርድ ብቻ ነበር። ይህም መጥፎ ባሕርይ ይታይ የነበረው ካህናትንና ነቢያትንም ጨምሮ በእያንዳንዱ የኅብረተሰብ አባል ላይ ነበር። ኤር. 2:4-8ና 26-32፤ 3:6-10፤ 5:4-9 ና 18-31፤ 6:9-15 ና 27-30 ተመልከቱ።

2. ጥሪ - እግዚአብሔር ለንስሐ ያደረገው ጥሪ በሌሎች ክፍሎች ውስጥ እንደሚገኝ በዚህ ክፍል ውስጥ በተደጋጋሚ አይገኝም። ለዚህ ምክንያቱ ምናልባት እነዚህ ምዕራፎች የተጻፉት ተሐድሶ ባደረገበት ዘመን ስለሆነ ሕዝቡ ወደ እውነተኛ አምልኮ እንዲመለሱ ተገደው ይሆናል። ወይም ኃጢአታቸው በጣም የከፋ ከመሆኑ የተነሣ ንስሐ ከመግባታቸው በፊት በመጀመሪያ በቅርብ ጊዜ ውስጥ ስለሚደርስባቸው ፍርድ ማወቅ ስለነበረባቸው ይሆናል። ታማኞች ያልነበሩ ቢሆኑም እንኳ እግዚአብሔር ሳይረሳቸው ጥሪ አድርጎላቸዋል፤ ኤር. 2:1-3፤ 3:11-14፥ 21-25፤ 4:1-4 ና 6:16-21 ተመልከቱ።

3. ፍርድ - ይህ ዐቢይ ትምህርት ለሕዝቡ እጅግ የማይስማማ መስሎ ሳይታያቸው አይቀርም። ኢዮስያስ በበኩሉ የሃይማኖት መነቃቃት አስነሥቶ ነበር። ላይ ላዩን ትልቅ መሻሻል አድርጓል። ኤርምያስ የሕዝቡ ልብ ካልተለወጠ በሰማሪያ ላይ የሆነው ነገር በኢየሩሳሌም ላይ እንደሚፈጸም ያውቅ ነበር። በዚያን ጊዜ አምር እየተዳከመች ሲሆን ይሁዳ ግን እየተጠናከረች ነበር፤ ፍርድም የቀረበ መስሎ አይታይም ነበር። ነገር ግን የኤርምያስ ትንቢቶች የተመሠረቱት ሕዝቡ በሚሰጡት ዓፀፋ ላይ ሳይሆን በእግዚአብሔር በራሱ ባሕርይ ላይ ነበር፤ ኤር. 2:14-19፥ 33-37፤ 4:5-12፥ 23-31፥ 5:10-17፤ 6:1-5 ና 22-26 ተመልከቱ።

## ንዑስ ክፍል ሦስት - ማብራሪያ

በእነዚህ ምዕራፎች ውስጥ የሚገኘውን ጽሑፍ በተከታታይ ከመመልከት ይልቅ ኤርምያስ ይናገራቸው በነበሩት ዋና ዋና ነጥቦች ላይ እናተኩራለን።

1. የእነዚህ ምዕራፎች ዋና ትምህርት ፍርድ ነው። ሕዝቡ ከእግዚአብሔር መራቃቸው ስደተኛ አድርጓቸው ነበር፤ 2:14-19። ኃጢአት በማድረግ ላይ

ያሉ ቢሆኑም እንኳ ራሳቸውን ንጹሕ አስመስለው ለማቅረብ ጥረዋል፤ 2፡33-37። ከባቢሎን የሚመጣው ሠራዊት ልክ እንጓንበሳ በላያቸው ሊመጣ ነው፤ 4፡5-10። ጠላት ከተማይቱን በሙሉ እንዲያጠፋ ተልኳል። ሕዝቡ በአጠቃላይ ማድረግ የሚችሉት ነገር መሸሽ ብቻ እንደሆነ ተገልጾላቸዋል፤ 4፡11-12። ነቢዩ በየትኛውም አቅጣጫ ቢመለከትም በሁሉም አቅጣጫ የነበረው ጭንቀት ብቻ ነው። የእግዚአብሔር ቁጣ በየትኛውም ሥፍራ ግልጽ ነበር፤ 4፡23-26። ከፍተኛ ፍርድ በመምጣት ላይ የነበረ ቢሆንም እግዚአብሔር ምሕረት እንደሚያደርግ ተናግሯል፤ 4፡27-31። የባዕድ መንግሥት ወደ ይሁዳ መጥቶ እርቃኗን ያስቀራታል። ይሁዳም በአጠቃላይ ሙሉ በሙሉ ተደምስሳለች፤ 5፡10-17። በዚህ ክፍል እንደሚታየው ወራሪዎች ይሁዳን ለማውደም በዝግጅት ላይ ሲሆኑ፥ 6፡1-5 የይሁዳ ሕዝብም የጠላትን መምጣት በፍርሐት እየተጠባበቁ ናቸው፤ 6፡22-26። ኤርምያስም ሕዝቡ ንስሐ እንዲገቡ ያሳስባል።

2. የእነዚህ ሁሉ ፍርዶች ምክንያት የሕዝቡ እምነት ማጣት ነው። ምክንያቱም እግዚአብሔር ቢመራቸውና የሚያስፈልጋቸውን ቢያዘጋጅላቸውም እንኳ እነርሱ ተቃውሞ አስነሥተውበታል፤ 2፡4-8። እግዚአብሔርን ከማምለክ ፈንታ ፊታቸውን ወደ ጣዖታት መልሰው ነበር፤ 2፡26-32። ይሁዳም የከነዓናውያንን ሃይማኖት በመከተል በእግዚአብሔር ላይ አመንዝራለች፤ 3፡6-10። ነቢዩ ወደ የተኛውም አቅጣጫ ቢመለከት የሚያየው ተመሳሳይ ነገር ነበር። የሕዝቡ ፍላጎት ኃጢአት ማድረግ ብቻ ነበር፤ 5፡4-9። እነርሱን ከኃጢአት ለመመለስ እግዚአብሔር የፈለገውን ቢያደርግም እንኳ ከእርሱ ከመራቅ ወደኃላ አላሉም፤ 5፡18-31። የኤርምያስን ቃል አንሰማም በማለት ራሳቸውን ምንም ስሕተት እንደሌለባቸው በማድረግ ይመላለሱ ነበር፤ 6፡9-15። ፈተና ቢቀርብላቸውም መልስ አልሰጡም። ጥፋታቸውን ቢያውቁም እንኳ መመለስ አልፈለጉም ነበር፤ 6፡27-30።

3. ይህ በዚህ እንዳለ እግዚአብሔር ለሕዝቡ ተከታታይ ጥሪ አቅርቦላቸዋል። ንስሐም እንዲገቡ ጋብዟቸዋል። ወደ እርሱ ሊመለሱ የሚችሉበት ጊዜ ነበራቸው፤ እሥራኤል ግን አንድ ጊዜ ከእግዚአብሔር ስለተለየች ምንም ግንኙነት አልነበራትም፤ 2፡1-3። የእሥራኤልም ኃጢአት ከይሁዳ ስለሚሻል እርሷ የተለየ ጥሪ ተደርጎላታል፤ 3፡11-14። ባልተሰተካከለ ባሕርይም ውስጥ ቢሆኑም እግዚአብሔር ወደ እርሱ እንዲመለሱ ጠርቷቸዋል፤ 3፡21-25። ወደ እርሱ በሚመለሱበትም ወቅት የእግዚአብሔርን በረከት እንደሚቀበሉ ተናግሯቸዋል፤ 4፡1-4። እንዴት ወደ እግዚአብሔር ሊመለሱ እንደሚችሉ ተናግሯቸዋል። መንገዱም ክፍት ሆኖ ይጠብቃቸው ነበር፤ 6፡16-21።

4. አልፎ አልፎ እግዚአብሔር የገሰፃቸው ሲሆን የሚያደርጓቸውን ነገሮች ከንቱነት አሳይቷቸዋል፤ 2:9-13። በመጨረሻም ኢየሩሳሌም ምንም ተስፋ የሌላት እንደሆነች ቀርቧል። አእምሮዋን ወደ እግዚአብሔር እንድትመልስ የሚያደርጋት ነገር ቅጣት ብቻ ነው፤ 6:6-8።

5. ሕዝቡን ኃጢአት አታሏቸው ነበር። ከእግዚአብሔርም ምን ያህል እንደራቁ እንኳን ማወቅ በማይችሉበት ደረጃ ላይ ነበሩ። ዓይናቸው ታውሯል፤ ጆሮአቸውም ለእነርሱ የተሰጠውን ቃል እንዳያደምጥ ደንቁሮአል፤ 2:20-25። በከነዓናውያን ሃይማኖትና በጣዖት አምልኮ ውስጥ ስለመዘፈቃቸው ምንም ነገር አይሰማቸውም ነበር። እውነተኛውን መንገድ አውቀው ነበር፤ አሁን ግን ወደ ጨለማ ተመልሰዋል፤ 3:1-5። ይህ የግታለል ተግባር የሕዝቡ ባሕርይ ነበር። ባሕርያቸው በአጠቃላይ መጥፎ ነበር። ከእነርሱ መካከል አንድም እውነተኛ ሰው አልነበረም፤ 5:1-3።

6. በምዕ. 2-6 ውስጥ እግዚአብሔር ለሕዝቡ ብዙ የተስፋ ቃሎች ሲሰጥ እናይም። ያስገነዘባቸው አስቀድሞ ወደ እርሱ መመለስ እንደሚያሻቸውና፤ ከዚያ በኋላ እርሱ ቁስላቸውን እንደሚፈውስ ነው። የተስፋ ቃል ሊገባላቸው የሚችለውም ከዚህ በኋላ ነበር፤ ኤር. 3:15-20።

7. ምናልባት እነዚህ ምዕራፎች የተነገሩት በተለያዩ ጊዜያት ሳይሆን አይቀርም። ይህ ቢሆን በእነዚህ ምዕራፎች ውስጥም ነቢዩ በተለያዩ መንገዶች ለሕዝቡ ሲናገር እንመለከታለን። እነዚህም ኤርምያስ ነቢይ በነበረበት ወቅት በይሁዳና በኢየሩሳሌም የነበሩትን ሰዎች መንፈሳዊ ሁኔታ በግልጽ ያሳዩናል።

## ንዑስ ክፍል አራት - ልዩ ጠቃሚ ነጥቦች

1. በኤር. 2:2 እንደተገለጠው እግዚአብሔር የጋብቻን ውል በሚመስል ከሕዝቡ ጋር አድርጎአል ይላል። ከዚህም የተነሣ እነርሱ የእርሱ ልዩ ሕዝብ ሆነዋል። ሕዝቡ ግን ስምምነቱን ቸል በማለት ልክ ውል እንደሌለ የማስመሰል ሙከራ አድርገዋል፤ 2:20። ነቢዩ የይሁዳን ኃጢአት ዝሙት ብሎ የሚጠራው ለዚህ ነው፤ 3:1-2። የእነርሱ ኃጢአት ከማንኛውም ሕዝብ ኃጢአት ይልቅ የከፋ ነበር። ምክንያቱም እነርሱ የእግዚአብሔር ሕዝብ ስለሆኑ ሊሰጡት የሚችሉት ምክንያት ከሌላው በጣም ያነሰ ነው። ከእነርሱ ጋር ስምምነት ያደረገው እርሱ ብቻ ሳይሆን እነርሱም በበኩላቸው ከእርሱ ጋር ስምምነት አድርገዋል። እርሱ የእነርሱ እንደመሆኑ መጠን እነርሱም የእርሱ ናቸው። እንደ ካህናትና ነቢያት የመሳሰሉት ሕዝቡን መርዳት የነበረባቸው ሰዎች ቢሆኑም እንኳ ያደረጉት ነገር ሕዝቡን ግታለል ብቻ ነበር፤ 5:30-31።

2. ሕዝቡ የአምስቱን የሙሴ መጻሕፍት ጥቂት ሥርዓታትን መታዘዝ እና በተጨማሪም የአባቶችን ልምዶችና ወጎችንም ማክበር ይቻላል የሚል ግምት ነበራቸው። ስለዚህ እንደገና ተመልሰው በከነዓናውያን ሃይማኖት ሊዘፈቁ በቅተዋል። እግዚአብሔር ግን አስቀድሞ እርሱንና የከነዓናውያን ሃይማኖት አንድ ላይ ቀላቅለው ሊያመልኩት እንደማይችሉ ደጋግሞ አስጠንቅቆአቸዋል፤ 2፡9-13። ይህም ድርጊታቸው እግዚአብሔር እጅግ የሚጠላቸውን ነገሮች ወደ ማድረግ መራቸው፤ 3፡1-5። መጀመሪያ ወደ ከነዓን ሲገቡ እነዚህን ነገሮች እንዲያጠፉ ነግሮአቸው ነበር። እነርሱ ግን ይህንን እግዚአብሔር የሰጣቸውን ትዕዛዝ መጠበቅ ስለተዉ በእነዚህ ነገሮች ተሸንፈዋል።

3. ይህ ሁሉ ቢሆንም እግዚአብሔር ለእነርሱ ምሕረት ለማድረግ ዝግጁ ነበር። ጊዜው ሳያልፍባቸው ወደ እርሱ እንዲመለሱ በኤርምያስ አማካይነት ተማፅኖአቸዋል። ዋና ዋና ትምህርታቸው ስለ ፍርድ ብዙ ክፍሎችን የተመለከትን ቢሆንም ለዚህም ፍርድ ምክንያት የሆነው ቃል ኪዳን መጥቶላቸው ነበር። እግዚአብሔር ግን ከፍርድ ይልቅ ምሕረት ስለሚመርጥ ወደ እርሱ እንዲመለሱ ብዙ ጊዜ ጥሪ አድርጎላቸዋል። በመጨረሻ ግን የኤርምያስ መልእክት ይዘቱ ሲለወጥ ይታያል፤ ይኸውም ሕዝቡ ከሚደርስባቸው ጥፋት ሊያመልጡ የሚችሉት እጃቸውን ለባቢሎናውያን በመስጠትና እግዚአብሔር በእነርሱ በኩል የላከባቸውን ፍርድ በመቀበል ብቻ ነው የሚል ነበር።

## ንዑስ ክፍል አምስት - ከአዲስ ኪዳን ጋር ያለው ዝምድና

1. እነዚህ ምዕራፎች በጠቅላላ ፍርድ የሚሰጥ ራሱ እግዚአብሔር እንደሆነ ያሳዩናል። እርሱም የኃጢአተኝነታቸው ውጤት ፍርድ ብቻ ነው በማለት አልተዋቸውም፤ ወይም ሕዝቡን በጦርነት ውስጥ በመከተት በባቢሎናውያን እንዲሸነፍ አላደረገም። እግዚአብሔር ራሱ ምን እንደሚደርስባቸው ከማሳሰቡም በላይ እርሱ ራሱ የባቢሎናውያንን ሠራዊት አስነሥቶባቸዋል። በዚህም የተነሣ በይሁዳ የሚኖረው ሕዝብ በባቢሎን ሳይሆን በእግዚአብሔር እንደተሸነፈ ያውቅ ነበር። ይህን የመሰለው ፍርድ ባለፈው ጊዜ ብቻ የሆነ አይደለም፤ አሁንም ቢሆን አውቀው የማይታዘዙትን እግዚአብሔር ይቀጣቸዋል።

2. ሕዝቡ ሌላ ሁለተኛ ረዳት ሲፈልጉ እግዚአብሔር በዚህ አይከበርም። ሕዝቡም እርሱን ራሱን ብቻ እንዲያመልኩት ይፈልጋል። ሕዝቡም አስቀድሞ እርሱን ስለመረጠ ከዚያ በኋላ ሁለት ምርጫ ሊኖራቸው አይችልም። እርሱን ከመረጡ በኋላ ወደ ከነዓን ሃይማኖት መመለስ እግዚአብሔርን እንደመስደብ የሚቆጠር ነው። በሮምም የሚኖሩ አንዳንድ ክርስቲያኖች ያደረጉት ጥፋት ከዚህ ጋር ይቀራረባል። ጳውሎስ በዕብራውያን መልእክቱ ውስጥ ለእነዚህ ሰዎች የጻፈ

ሊሆን፤ የክርስቶስ መሆንና በሌሎች የሃይማኖት ሥርዓቶች ውስጥ ደግሞ መሳተፍ የማይቻል መሆኑን አሳስቦአቸዋል።

3. እነዚህ ምዕራፎች በሙሉ የተሞሉት በነቢዩ ኤርምያስ አማካይነት ለሕዝቡ በተሰጠ የእግዚአብሔር ቃል ነው። ሕዝቡ እግዚአብሔር ስለተናገራቸው እርሱ ከእርሱ የሚፈልገው ምን እንደሆነ አውቀዋል። የእግዚአብሔርን ዕቅዶችና ዓላማዎች በሚመለከት ምንም ጥያቄ አልነበራቸውም። በዚያ ዘመን እግዚአብሔር ለይሁዳና ለኢየሩሳሌም ሕዝብ በኤርምያስ አማካይነት የተናገረው ቃል ዛሬም ቢሆን በእኛ ላይ ሥልጣን አለው። ምክንያቱም የእግዚአብሔር ቃል ስለሆነ አይለወጥም፤ ዋጋውም አይቀንስም። እግዚአብሔር በኤርምያስ ዘመን በኢየሩሳሌም ለነበረው ሕዝብ ያስብ እንደነበረ ሁሉ ለእኛም ያስብልናል።

## ንዑስ ክፍል ስድስት - የክለሳ ጥያቄዎች

1. ኤርምያስ የሞተው የት ነበር?
2. ኤር. 2፡6 ከሌላው ክፍል የተለየ የሆነበት ምክንያት ምንድነው?
3. ኢዮስያስ አባት ማን ነበር? አያቱስ?
4. ኢዮስያስ የሞተው በስንት ዓመቱ ነው? ዘመኑስ?
5. በኢዮስያስ ዘመን ስለተደረገው የሃይማኖት መነቃቃት የሚናገሩት የትኞቹ ምዕራፎች ናቸው?
6. ኤርምያስ ይህንን የሃይማኖት መነቃቃት በመጽሐፉ ውስጥ ለምን አልጠቀሰውም?
7. ሕዝቡ እምነተቢስ ተብለው ሊጠሩ የቻሉት ለምንድነው?
8. እምነተቢስ የነበሩት መሪዎችስ እነማን ናቸው?
9. በኤር. 2-5 ውስጥ ለሕዝቡ የተሰጡት የንስሐ ጥሪዎች ጥቂት የሆኑበት ምክንያት ለምንድነው?
10. ፍርድ በዚያ ዘመን የማይመጣ የመሰላቸው ለምንድነው?
11. ነነቄ የአሦር ዋና ከተማ ነበረች። ይህችም ከተማ በባቢሎን የተሸነፈችው መቼ ነበር?
12. በኤር. 2-6 ውስጥ በተደጋጋሚ የሚታየው ዋና ትምህርት ምንድነው?
13. በይሁዳ ላይ ፍርድ የሚያስከትልባት ነገር ምንድነው?
14. እግዚአብሔር የይሁዳና የኢየሩሳሌምን ሕዝብ የገሠፀው ለምንድነው?

15. የይሁዳ ሕዝብ የኮበለለው የትኛውን ሃይማኖት ለመከተል ሲል ነው?

16. ሕዝቡ አሁንም ሊያደርገው የሚችለው ነገር ምንድነው?

17. ባቢሎናውያን ይሁዳን እንዲወሩ ያደረገው ማን ነው?

18. ሕዝቡ እግዚአብሔርን የሰደቡት በምንድነው?

19. በኤር. 2-6 ውስጥ የምናገኘው የማንን ቃል ነው?

## ንዑስ ክፍል ሰባት አስተዋፅኦ

### የይሁዳ ኃጢአተኝነት - ኤር. 2፡1-37

1-3 - የይሁዳ የመጀመሪያ ፍቅር

4-8 - እምነተቢስነት

9-13 - ክሕደት

14-19 - እሥረኞች

20-25 - ኃጢአት የማድረግ ምኞት

26-32 - ክሕደት

33-37 - ውርደት

### የኃጢአት ማታለያ - ኤር. 3፡1-25

1-5 - ዝሙት

6-10 - የይሁዳ መታለል

11-14 - ለእሥራኤል የተደረገ ጥሪ

15-20 - የሕዝቡ መሰብሰብ

21-25 - ንስሐ

### የማይቀር ፍርድ - ኤር. 4፡1-31

1-4 - የንስሐ ጥሪ

5-8 - የተበቃዮች መምጣት

9-10 - ፍርሐት

11-17 - ፍርድ

18-22 - ጥፋት

23-26 - መራቆት

27-31 - መከራና ሞኝነት

### የኃጢአት መዛመት - ኤር. 5፡1-31

1-3 - የእውነት መጥፋት

4-6 - በሁሉ ላይ የሚደርስ ጥፋት

7-9 - ቅጣት

10-17 - መገረዝ

18-31 - ገደብ የለሽ ኃጢአት

### ኃጢአተኛ ከተማ - ኤር. 6፡1-30

1-5 - የማይቀር ሰልፍ

6-8 - ኃጢአተኛዋ ኢየሩሳሌም

9-15 - በኃጢአት መሸነፍ

16-21 - አለመታዘዝና ቅጣት

22-26 - ጥፋት

27-30 - ለዘላለም አለመንጻት

## ክፍል ሰባት - ኤር. 7-12

### ንዑስ ክፍል አንድ - ታሪካዊ አቀማመጥ

1. ምናልባት ኢሳይያስ የሞተው በደጉ ንጉሥ ሕዝቅያስ ልጅ በምናሴ ዘመነ መንግሥት ሳይሆን እንደማይቀር ተመልክተናል። በይሁዳ ከነገሡት ነገሥታት መካከል ምናሴና ልጁ አሞን እጅግ በጣም ዓመፀኞች ነበሩ። አሞን የመራው ለአጭር ጊዜ ብቻ ሲሆን ከእርሱ ቀጥሎ ልጁ ኢዮስያስ በፈንታው ነግሦአል። በምናሴና በአሞን ዘመን በይሁዳ ምንም ነቢያት አልንበሩም። ሕዝቡ በተለያዩ መንገዶች ይሰቃዩ ነበሩ። በሁሉም ቦታ ተሰራጭቶ ከነበረው ኃጢአት የተነሣ አብዛኛዎቹ ጻድቃን መከራ ይደርስባቸው ነበር። ከምናሴ ዘመነ መንግሥት

በፊትም ቢሆን የሰማሪያ ከተማ በአሦራውያን ቁጥጥር ሥር ውላ ስለነበር አሥሩ ነገዶች ተማርከው ነበር። ይሁዳ ይህንን ትምህርት ጨርሳ ረስታዋለች።

2. በኤርምያስ ዘመን አስደናቂ ለውጥ ተደርጎ ነበር። አሦር በመዳከም ላይ ነበረች። ዋና ከተማዋም ነነዌ በ612 ዓ.ዓ. ተደምስሳለች። ባቢሎንም እጅግ በመጠናከር ላይ ነበረች። ኢሳይያስ ባቢሎን ኃያል መንግሥት እንደምትሆን ለሕዝቅያስ አሳስቦታል፤ ኢሳ. 39። ኢዮስያስ በአሦር አማካይነት በጣም ስቃይ ሰለደረሰበት ባቢሎን አሦርን ድል ስታደርግ ለማየት የናፈቀ ሲሆን በአንፃሩ ግን ባቢሎን ልክ እንደ አሦር ጨካኝ እንደማትሆንና በመጨረሻም ኢየሩሳሌምንና ይሁዳን እንደምትደመስስ አልተገነዘቡም።

3. ሦስተኛዋ ኃያል መንግሥት ግብፅ የነበረች ሲሆን በኤርምያስም ዘመን ስለ ግብፅ አንዳንድ ነገሮች ተጽፈዋል። ባቢሎን ኃያል መንግሥት ስትሆን ማየት አትፈልግም ነበር። የግብፅ ንጉሥ አሦር ከባቢሎን ጋር ስትዋጋ እርዳታ ለማድረግ ወደ ሰሜን ተጉዛ ነበር። ኢዮስያስ ግን አሦር እርዳታ እንድታገኝ ስላልፈለገ የግብፅ ንጉሥ ወደ ሰሜን እንዳይሄድ ለመከላከል ሲል ከእርሱ ጋር በመጊዶ ውጊያ አድርገዋል። በዚህም ምክንያት በ609 ዓ.ዓ. ኢዮስያስ በግብፅ ንጉሥ ተገድሏል። ከዚህ በኋላ የግብፅ ንጉሥ ብዙ የአሦር ከተሞችን በመያዝ ለብዙ ዓመታት ከባቢሎን ጋር ተዋግቷል። በእነዚህም ዓመታት ውስጥ የይሁዳ እንቅስቃሴ በግብፅ ቁጥጥር ሥር ነበር።

## ንዑስ ክፍል ሁለት - የነቢዩ ሽክም

1. ሕዝቡም የባቢሎናውያን ወረራ ካስከተለባቸው ችግር ለመዳን ንስሐ የመግባት ዕድል ተሰጥቶአቸዋል። ምንም እንኳ ሕዝቡ ኃጢአታቸውን እንደተሸከሙ ያሉት ሆነ ብለው ስለሆነ ኤርምያስ ዘወትር የንስሐ ጥሪ ባያደርግላቸውም እስከ መጨረሻው ቀን ድረስ እግዚአብሔር ወደ እርሱ እንዲመለሱ ጋብዞአቸዋል፤ 7፡1-7። ኤርምያስም ሕዝቡ የባሕሪያቸውን አስቀያሚነት እንዲመለከቱ አዘውትሮ ፀባያቸው ምን እንደሚመስል ያሳያቸው ነበር። በዚህ ምክንያት የእግዚአብሔር ፍርድ እንደሚገባቸው ግልጽ ነበር። ይህም የእግዚአብሔርን ቃል ኪዳን መጣሳቸውን ሙሉ በሙሉ ያረጋግጣል፤ ከዚያም የተነሣ የእርሱን ጥበቃ እናገኛለን ብለው መጠበቅ አይችሉም።

2. ሐሰተኛ ሃይማኖት ሕዝቡን ከእግዚአብሔር አርቆአቸዋል። የእግዚአብሔርን ታላቅነት ቢያስታውሱና ጣዖታትን የመከተል ፍጹም ጥቅመቢስነት ቢረዱ ኖሮ፥ ከእግዚአብሔር ነገዶች ፈቀቅ አይሉም ነበር። የኤር. 10 ዓቢይ ትምህርት ይህ ነው። ሕዝቡ ለራሳቸው ጣዖታትን የሚፈጥሩበት መንገድ ምን እንደሆነ በቁ. 1-5 ውስጥ ተገልጿል። ሰው እንዴት እግዚአብሔር ከጣዖታት ጋር ሊያወዳድር እንደሚችል ኤርምያስ በዚህ ክፍል አስቀምጧል፤ ቁ. 6-10። እግዚአብሔር

እነዚህን ጣዖታት ያወግዛል፤ ቁ. 11። የእግዚአብሔር የበላይነት የመፍጠር ችሎታው እንደተገለጠ ያሳያል፤ ቁ. 12-16። ጣዖታትን የሠሩትን ግን ይፈርድባቸዋል፤ ቁ. 17-18።

3. ኤርምያስ በእነዚህ ምዕራፎች ውስጥ ራሱ የተሰማውን ስሜት በጣም ግልጽና ልዩ በሆነ መንገድ ይገልጻል። እነዚህ ምዕራፎች ኤርምያስ ምን ያህል እንደተስማማው ብቻ ሳይሆን በተጨማሪም እግዚአብሔርም ለሰጣቸው መልእክት ሕዝቡ በሰጠው መልስ የተሰማውን ስሜት ይገልጽልናል፤ ለዚህም 8፡18-21 ና 10፡19-25 ተመልከቱ። ኤርምያስ የሰጠውን መልስ እግዚአብሔር ከመላው ሕዝብ የሚሻው እንጂ በእነርሱ መካከል ከሚገኝ አንድ ጻድቅ ሰው ብቻ የሚፈልገው አልነበረም። አንዳንዴ የኤርምያስ መልስ ከሚፈለገው በላይ ይመስላል። ሆኖም የእርሱን ዕንባ በፍጥነት ከሚሆነው የባቢሎናውያን ወረራ አንፃር ልንገመግመው ያሻል። ምክንያቱም የሕዝቡ ልበ ደንዳናነት ይህን ጥፋት በምድሪቱ ላይ ሊያመጣባት ነበርና ነው።

## ንውስ ክፍል ሦስት - ማብራሪያ

1. በቤተ መቀድሱ እናምናለን እያሉ በኃጢአት መኖር ሕዝቡን ከእግዚአብሔር ቁጣ አያድናቸውም። ምክንያቱም የእግዚአብሔር ጥያቄ ንጽሕናን የሚመለከት ነው፤ 7፡1-7። በሳሙኤል ዘመን ታቦቱ የነበረው በሴሎ ቢሆንም እንኳ፤ እግዚአብሔር ሴሎን አጥፍቶአታል። ኢየሩሳሌምም የሚደርስባት ከዚሁ ጋር ተመሳሳይ ነገር እንደሆነ ተገልጿል፤ 7፡8-15። የኢየሩሳሌምም ነዋሪዎች ምንም ተስፋ አልነበራቸውም። እያወቁ ለባዕድ አማልክት መሥዋዕትን ያቀርቡ ነበር፤ 7፡16-20። አስፈላጊው ነገር ... መሥዋዕት ነው ወይስ መታዘዝ? አኗኗራቸው በእግዚአብሔር ፊት ንጽሕና ከሌለው መሥዋዕታቸው ምንም ጥቅም አይሰጥም፤ 7፡21-26። የእግዚአብሔርን ቃል አንሰማምና አንታዘዝም በማለታቸው ከእግዚአብሔር ተቃውሞ እንደሚደርስባቸው ይጠቁማል፤ 7፡27-29። በመጨረሻም በ586 ዓ.ዓ. ናቡከደነፆር ኢየሩሳሌምን ሲደመስስ በኤር. ምዕ. 7፡30-34 ያለው ትንቢት ፍጻሜ ሊያገኝ ችሏል።

2. የሕዝቡ ኃጢአት ከፍተኛ ውርደትና ሐፍረት እንደሚያስከትልባቸውና አጥንታቸውም ከመቃብር ወጥቶ በምድር ላይ እንደሚሰጣ ይናገራል፤ 8፡1-3። እንስሳትና ወፎች እንዴት መኖር እንደሚገባቸው ያውቃሉ፤ እነዚህ ሰዎች ግን የእግዚአብሔርን ፍርድ ማወቅ አልቻሉም፤ 8፡4-7። ማስተማር የነበረባቸው ነቢያትና ካህናትም ማስተማር ሲገባቸው ምግባራቸው ሕዝቡን ከእግዚአብሔር እንዲርቅ አድርጎት ነበር፤ 8፡8-13። ይህ ጠባያቸው ፍርድ እንደሚያመጣባቸው እርግጥ ነበር፤ እንዲያውም በመምጣት ላይ የነበረውን

ሠራዊት ድምፅ እየሰሙ ነበር፤ 8:14-17። ኤርምያስም የሕዝቡን ግትርነት ስለተመለከተ ልቡ ተሰብሯል፤ 8:18-22።

3. ሕዝቡ በጣም ኃጢአተኛ ስለሆነ የኤርምያስ ፍላጎት ከሕዝቡ ራቅ ማለት ብቻ ነበር፤ 9:1-3። ምንም እምነት የሚጣልበት ሰው አልነበረም፤ የሁሉም ሰው ፍላጎት ወገኑን መሸንገልና ማታለል ነበር 9:4-6። የዚህም ሥነ ምግባር ብልሽት ውጤት አንድ ብቻ እንደሆነ እግዚአብሔር ተናግሯል። ይኸውም ሕዝቡን በፍርድ ማንጻት እንዳለበት ነው፤ 9:7-9። በዚህም ምክንያት አገሪቱ በአጠቃላይ ሥቃይ ልትቀበል ነው። ፍርዱም የሚያጠቃው ሕዝቡን ብቻ ሳይሆን ከተሞቹንም ጭምር ነው፤ 9:10-11። ለዚህም ጥፋትና ደም መፍሰስ ምክንያት የሆነውን ነገር ለሚጠይቅ ሁሉ ግልጽ ነበር። ይኸም የሕዝቡ እግዚአብሔርን መካድ ነበር፤ 9:12-16። በመምጣት ላይ ከነበረው መከራ የተነሣ አገሩ ሁሉ በለቅሶና በጩኸት ተሞልቶ ነበር፤ 9:17-19። ሞትም በየቦታው ነበር፤ 9:20-22። አገሪቱ በሕይወትና በሰላም ከመሞላት ፈንታ በራሳ እንደምትሞላ እግዚአብሔር ተናግሯል። እውነተኛ ያልሆነንን እምነት ማስወገጃውና በእግዚአብሔር ብቻ የመታመኛው ወቅት አሁን ነው፤ 9:23-24። የይሁዳ ሥራ በአካባቢዋ እንዳሉት አሕዛብ ጎረቤቶችም ስለሆኑ ልክ እንደ እነርሱ ተቆጥራለች፤ 9:25-26።

4. ሕዝቡ ከጫካ እንጨት የተሠሩትን ጣዖታት መፍራትና ማምለክ እንደሌለባቸው አሳስቦአቸዋል፤ 10:1-5። እግዚአብሔር ብቻ ኃያል ነው፤ 10:6-11። ፈጣሪ በመሆን ሊፈራ የሚገባው እርሱ ብቻ ነው። ሕዝቡም ግራና ቀኛቸውን በመመልከት እግዚአብሔር በፍጥረት ላይ ያለውን ኃይል ነው፤ 10:6-11። ፈጣሪ በመሆን ሊፈራ የሚገባው እርሱ ብቻ ነው። ሕዝቡም ግራና ቀኛቸውን በመመልከት እግዚአብሔር በፍጥረት ላይ ያለውን ኃይል ማየት ነበረባቸው፤ 10:12-16። ከዚህ በኋላ እርሱንና የአሕዛብ ጣዖታትን ሊያወዳድሩ ይችላሉ። እግዚአብሔር ሕዝቡን ሊያስጨንቅ እንደሆነ ይናገራል፤ 10:17-18። ከዚያም በኋል በባዕድ አገር ይበታተናሉ። ኤርምያስም ይህንን ሲሰማ ልቡ ተሰብሯል፤ 10:19-22። እግዚአብሔር ለእርሱና ለሕዝቡ ምሕረት እንዲያደርግ ጠይቋል፤ 10:23-25። ምክንያቱም ሊያድናቸው የሚችል የእግዚአብሔር ምሕረት ብቻ ነው።

5. ኤርምያስ ቃል ኪዳኑ በምን ላይ እንደተመሠረተ ከእግዚአብሔር ግሳሰቢያ ተሰጥቶታል፤ 11:1-5። በረከትና መርገም ሁለት አማራጮች የተሰጣቸው ሲሆን፥ ቃል ኪዳኑ በእነርሱ መታዘዝ ላይ የተመሠረተ መሆኑን ሕዝቡን እንዲያስጠነቅቅ ለነቢዩ ተነግሮታል፤ 11:6-8። የይሁዳና የኢየሩሳሌም ሕዝብ ግን እግዚአብሔርን አንታዘዝም ብለው ባዕድ አማልክትን ወደ ማምለክ ሄዱ፤ 11:9-13። ስለዚህ እግዚአብሔር ማድረግ የሚችለው በሕዝቡ ላይ መፍረድና

መቅጣት ብቻ ነው፤ 11:14-17 ምክንያቱም ሕዝቡ እርሱንና ምሕረቱን አንፈልግም ብለዋል። በተጨማሪም ሕዝቡ ኤርምያስ ላይ አደጋ ለማድረስ እንዳሰቡ እግዚአብሔር አሳይቶታል፤ 11:18-20። ኤርምያስ ግን ይህን አልተገነዘበም ነበር። እግዚአብሔርም በእናቶት ሕዝብ ላይ የፍርድ ቃል የተናገረበት ምክንያት ይህ ነበር፤ 11:21-23።

6. እግዚአብሔር ትዕግሥቱን ለሕዝቡ ለምን እንዳበዛላቸው ኤርምያስ ሊረዳው ያልቻለ ነገር ነበር፤ 12:1-4። የሕዝቡ ክፋት ከፊት ይልቅ እየባሰ መሄዱን እግዚአብሔር ለኤርምያስ ያሳስበዋል፤ 12:5-6። ኤርምያስ ለዚህ ነገር እራሱን ማዘጋጀት ነበረበት። እግዚአብሔርም ፍርዱ በሚሰጥበት ወቅት ከኃጢአታቸው የተነሣ ምድሪቱን ዕርቃኗን ያስቀራታል፤ 12:7-13። ሆኖም እግዚአብሔር በሕዝቡ ላይ የሚነሡትንም ባዕድ መንግሥታት ደግሞ እንደሚፈርድባቸው ይናገራል፤ 11:14-17።

## ንዑስ ክፍል አራት - ልዩ ጠቃሚ ነጥቦች

1. ምዕ. 7 ና 12 የያዙት ተመሳሳይ ዓቢይ ትምህርት ነው። ሁለቱም ምዕራፎች ምድራዊ ፍርድ የሚፈረድባቸው ከባሕርያቸው አንፃር እንጂ ከእግዚአብሔር ጋር ባላቸው የቃል ኪዳን ስምምነት አይደለም ይላሉ። እግዚአብሔር ሰፊ በሆኑና የተለያዩ መንገዶች ጻድቅ መሆኑን ለሕዝቡ ሲገልጽላቸው እናያለን፤ እነዚህም ሁለት ገጽታዎች አሏቸው:- 1ኛ ሕዝቡ ጻድቅ እንዲሆኑ ይጠይቃል። ምክንያቱም ሕዝቡ እርሱ ያዘዘውን ዓይነት አኗኗር መኖራቸው የቃል ኪዳኑ አንድ ክፍል ነው። 2ኛ እነርሱ እነዚህን ነገሮች ባያደርጉ ይፈርድባቸዋል፤ ሰላልታዘዙም ቅጣት ይቀበላሉ። በተቃራኒው ግን በኤርምያስ ዘመን የነበሩት አይሁዶች እግዚአብሔር እንደሚጠብቃቸውና የእነርሱ መጥፎ ጠባይ ግድ እንደማይሰጠው አድርገው በተሳሳተ አኳኋን ያስቡ ነበር።

2. በምዕ. 8ና 9 ውስጥ ፍርዱ የማይቀር መሆኑን ሕያው በሆነ አገላለጽ አቅርቦታል። ምክንያቱም በየትኛውም አቅጣጫ ሲመለከት የሚያየው የጥፋትና የመራቆት ምልክቶችን ነው። እነዚህ ምልክቶች ሁለት ጥቅሞች ሳይኖራቸው አይቀርም። አንደኛ:- ንስሐ ካልገቡ ፍርድ የማይቀር ነገር መሆኑን ለሕዝቡ ሳያሳስቧቸው አይቀርም፤ 9:12-19። ሁለተኛ:- ይህንን ፍርድ ያወጀው እግዚአብሔር ራሱ መሆኑን ለሕዝቡ ሳያሳውቃቸው አይቀርም። በመጨረሻም የኤርምያስ ትንቢት እውነት መሆኑን የሚያሳየን ምዕ. 52 ነው። ከዚያም በኋላ ሕዝቡ ወደ ኋላቸው ተመልሰው የቀደሙትን ምልክቶች ማየት ይችላሉ።

3. በምዕ. 10ና 11 ውስጥ እግዚአብሔርና ሕዝቡ ተነፃፅረዋል። የጣዖታት ከንቱነት በምዕ. 10 ውስጥ ቀርቧል። ሕዝቡም በጣም ሞኞችና ዕውሮች ከመሆናቸውም የተነሣ እግዚአብሔር የላከላቸውን መልእክተኛ እንኳ ሊገድሉት ፈልገው ነበር፤

11፡18-23። ኤርምያስ ግን በእነርሱ ላይ ምንም ያደረገባቸው ነገር አልነበረም። በእርግጥ ከኃጢአተኝነታቸው የተነሣ ልቡ አንዝኖ ነበር፤ 10፡19-25። በተጨማሪም የእርሱ ሐዘን እግዚአብሔር ስለ ሕዝቡ የተሰማውን ሐዘን የሚያሳይ ነበር። ሆኖም ሕዝቡ የዚህ ተቃራኒ ነበሩ። ከእንጨትና ከድንጋይ ለተሠሩ ጣዖታት ተመልሰው እስኪሰግዱ ድረስ እጅግ የታወሩ ነበሩ። ከዚህም የተነሣ እግዚአብሔር ሊተዋቸውና ለቅጣት አሳልፎ ሊሰጣቸው ተነሣ፤ 11፡14-17። ሕዝቡም ይህን ሁሉ ችግር በላያቸው ላይ አምጥተዋል።

## ንዑስ ክፍል አምስት - ከአዲስ ኪዳን ጋር ያለው ዝምድና

1. ኤር. 7-12 እግዚአብሔር እርሱን አልሰማም ያለውን ሕዝብ እንደሚቀጣው በግልጽ ያሳየናል። የኢየሩሳሌምና የአሁኑንም ዘመን ሕዝብ ሊቀበሉት ያልቻሉት ነገር ይሄ ነው። ይህ ቅጣት ግን ከመጨረሻው ፍርድ ጋር አንድ አይደለም። ይህ ፍርድ በቃል ኪዳን ከእግዚአብሔር ጋር በተሳሰሩ ሰዎች ላይ የሚፈጸም ነገር ነው። እነርሱ የእግዚአብሔር ቤተሰብ አካል ናቸው። ሕዝቡ ግን ኃጢአት በማድረጋቸው ወደ እግዚአብሔር ለመመለስ እምቢ ብለዋል። እንዲያውም በኤርምያስ አማካይነት የተሰጠውን የእግዚአብሔርን ቃል አልተቀበሉም። ስለዚህ አንቀበልም ያሉት ሰዎች ሁሉ ይቀጣሉ። ይህም ቅጣት እነርሱ የእግዚአብሔር መሆናቸውንና ወደ እርሱም መመለስ እንዳለባቸው ያሳስባቸዋል።

2. እግዚአብሔር ጻድቅ ነው። ስለዚህም የእርሱም ስም የተሸከሙት ሰዎች እንዲያጠፉት አይፈቅድላቸውም። እግዚአብሔር ልጆቹን ወደ ንስሐ ለማምጣት ብቻ ሳይሆን እርሱ ጻድቅ መሆኑንም ደግሞ ለዓለም ለማሳየት ሥራውን ይጀምራል። ሁሉም የፈለገውን ቢያደርግም እንኳ እግዚአብሔር መልካም የሆነውን ነገር ለሚያደርጉ እንደ ኤርምያስ ላሉት ሰዎች እንክብካቤ ያደርግላቸዋል። የእርሱን ስም የሚሰድቡትንና ሕዝቡን የሚያሳድዱትን የማያምኑ ሰዎች ግን ይፈርድባቸዋል። ከጥፋት ሥራቸው ንስሐ ገብተው ወደ እርሱ የሚመጡትን ሰዎች ያድናቸዋል።

3. እግዚአብሔር የእርሱ በሆነው ሕዝብ አኗኗርና ድርጊት ውስጥ ልዩ ሥፍራ እንዲሰጠው ይፈልጋል። ለእግዚአብሔር የተሰጠው ሁለተኛውን ሥፍራ ከሆነ ግን አንደኛውን ሥፍራ አንድ ነገር ወይም አንድ ሰው ወስዶታል ማለት ነው። ይህም ነገር ጣዖት ነው። ስለዚህ ለእግዚአብሔር የሚገባውን ክብር ወስዷል። ይህም እግዚአብሔርን ያስቆጣዋል። እግዚአብሔር ምን ጊዜም የመጀመሪያው ሥፍራ እንዲሰጠው ይፈልጋል። እግዚአብሔር ፈጣሪ የመልካምና የበጎ ስጦታ ሁሉ ምንጭ ነው። እርሱ ከሕዝቡ ጋር ቃል ኪዳን ገብቷል። እነርሱ የእርሱ ስለሆኑ ንብረቱ ናቸው። ስለዚህ የእርሱ በሆነው ውስጥ ምንም ነገር

የመጀመሪያውን ሥፍራ እንዲወስድ አይፈልግም፤ እርሱ የመጀመሪያውን ሥፍራ በሚወስድበት ጊዜ ሁሉ ነገር ይስተካከላል። ካልሆነ ግን የሁሉም ነገር ቅደም ተከተል መዘበራረቁ አይቀርም።

## ንዑስ ክፍል ስድስት - የክለሳ ጥያቄዎች

1. ከኢዮስያስ በፊት የነገሡት ማንና ማን ናቸው?
2. ኢሳይያስ የሞተው መቼ ነው?
3. ኤርምያስ መተንበይ ሲጀምር ኃያል የነበረችው መንግሥት ማን ነበረች?
4. ኢዮስያስ ባቢሎንን የመርዳት ሙከራ ያደረገው ለምንድነው?
5. የግብፅ ንጉሥ የተዋጋው ከማን ጋር ነው?
6. ኢዮስያስን በመጊዶ የገደለው ማን ነው?
7. የኤር. 7፡1-7 መልእክት ምንድነው?
8. የሕዝቡ እጅግ ከፍተኛ የሆነ ስሕተት ምን ነበር?
9. የኤርምያስ ዕንባ ምን ያሳየናል?
10. ኤርምያስ በምዕ. 7-12 ውስጥ በሰፊው ስለ ፍርድ የተናገረው ለምንድነው?
11. የእግዚአብሔር ዋና ጥያቄ ሥርዓት ነው ወይስ ንጽሕና?
12. የአጥንቶቹ መበታተንና መሰጣት የምን ምልክት ነው?
13. ካህናትና ሽማግሌዎች ሳይቀሩ ምን ይሠሩ ነበር?
14. ኤር. 9 ስለ ሕዝቡ አኗኗር ምን ያሳየናል?
15. እግዚአብሔርንና ጣዖታትን የሚያነፃፅረው የትኛው ምዕራፍ ነው?
16. ኤርምያስ ይኖርባት የነበረችው ከተማ ማን ትባላለች?
17. ኤር. 7 ና 12 ያላቸው ተመሳሳይ ትምህርት ምንድነው?
18. ኤርምያስ በዙሪያው የሚያያቸው የምን ምልክቶች ነበሩ?
19. እግዚአብሔር በሕዝቡ ኑሮ ውስጥ የሚፈልገው ምን ዓይነት ሥፍራ ነው?
20. እግዚአብሔርን ሕዝቡን የሚቀጣው በምን ምክንያት ነው?

## ንዑስ ክፍል ሰባት - የኤር. 7-12 አስተዋፅዖ

### ጠባይና ሥርዓት - ኤር. 7፡1-34

1-7 - የንስሐ ጥሪ

8-15 - ማስጠንቀቂያ

16-20 - የሕዝቡ መጥፎ ድርጊት

21-26 - የሕዝቡ አለመታዘዝ

27-29 - ልበ ደንዳናነት

30-34 - ደም መፍሰስ

### የማይቀረው ፍርድ - ኤር. 8፡1-21

1-3 - የተበታተኑ እና የተሰጡ አጥንቶች

4-7 - ምሕረት የማይደረግለት ቸልተኝነት

8-13 - ጥበበኞች

14-17 - ጥፋት

18-21 - የኢየሩሳሌም ጩኸት

### ፍርዱ - ኤር. 9፡1-26

1-3 - የሕዝቡ ሐሰተኝነት

4-6 - የማጭበርበር ኑሮ

7-9 - ማንጻት

10-11 - መቸገር

12-16 - ፍርድ

17-19 - ጩኸት

20-22 - ሞት

23-24 - በእግዚአብሔር መከበር

25-26 - የይሁዳ ሥፍራ

## እግዚአብሔርና ጣዖታት - 10፡1-25

1-5 - ጣዖታት

6-10 - ውድድር

11 - አግልከት

12-16 - ፈጣሪ

17-18 - ጥፋት

19-22 - የኤርምያስ ሐዘን

23-25 - የኤርምያስ ጸሎት

## ቃል ኪዳኑና ዓፀፋው - ኤር. 11፡1-23

1-5 - ቃል ኪዳኑ

6-8 - የቃል ኪዳኑ መሪዎች

9-13 - ዓመፅ

14-17 - ውግዘት

18-20 - በኤርምያስ ላይ የተጠነሰሰ ሤራ

21-23 - ኤርምያስን ለመግደል የተደረገ ሙከራ

## ኃጢአት - ኤር. 12፡1-17

1-4 - የቀረበው ጥያቄ

5-6 - ምክር

7-13 - መራቆት

14-17 - አማራጭ ሁኔታዎች

## ክፍል ስምንት - ኤር. 13-18

### ንዑስ ክፍል አንድ - ታሪካዊ አቀማመጥ

| | |
|---|---|
| ኢዮስያስ | 640 ዓ.ዓ. |
| ኢዮአካዝ | 609 ዓ.ዓ. |
| ኢዮአቄም | 598 ዓ.ዓ. |

1. ኤርምያስ ያገለገለው በአምስት የተለያዩ ነገሥታት ዘመን ሲሆን፥ በዚህ ክፍል ውስጥ ሦስቱን እንመለከታለን። እነዚህን ታሪኮች ከ2ኛ ነገ. 22-24፡7 እና ከ2ኛ ዜና 34-36፡8 ባለው ክፍል ውስጥ ማንበብ እንችላለን። አሁን በዚህ ሥፍራ ግን የአገልግሎታቸውን ዓበይት ነጥቦች እንመለከታለን።

2. ኢዮአካዝ የነገሠው ግብፃውያን በ609 ዓ.ዓ. ኢዮስያስን በመጊዶ ከገደሉት በኋላ ነው። እርሱም ለሦስት ወራት ብቻ ከመራ በኋላ ታሥሮ ወደ ግብፅ ተወስዷል። ግብፃውያንም የእርሱን ወንድም አንግሠውት ሄደዋል። የኢዮአካዝም ዘመን ሊታወስ እስከማይችል ድረስ በጣም አጭር ነበር።

3. ኢዮአቄም የነገሠው ለ11 ዓመታት ነው። በ609 ዓ.ዓ. የግብፃውያን ሠራዊት አሦራውያንን በመደገፍ ከባቢሎናውያን ጋር ለመዋጋት ወደ ሰሜን መጥቶ ነበር። ግብፃውያንም ከ609-605 ዓ.ዓ. ድረስ ባቢሎናውያንን በቁጥጥራቸው ሥር ያደረጓቸው ሲሆን በመጨረሻ ግን በባቢሎናውያንን ተሸንፈውና ሥፍራቸውን ለቀው ወደ አገራቸው ተመልሰዋል። ኢዮአቄምም ለባቢሎን ታማኝ ለመሆን ቃል ገብቶ ነበር፤ 2ኛ ነገ. 24፡1-4።

4. ኢዮአቄምም ልክ እንደ ይሁዳ ሕዝብ ከግብፅ ጋር ብሻረክ ከባቢሎን የባርነት ቀንበር አመልጣለሁ የሚል ሐሳብ ነበረው። ናቡከደነፆርም ይህንን ሐሳቡን ሰምቶ ኢየሩሳሌምን ለሁለተኛ ጊዜ ሊወርር መጣ። የመጀመሪያው ወረራ የተደረገው የግብፃውያንን ሠራዊት ድል ባደረገበት ወቅት ነበር።

5. ናቡከደነፆር እዚያ ከመድረሱ በፊት ኢዮአቄም ሞቶ በኢየሩሳሌም ተቀብሮ ነበር። ኢዮአካዝ፥ ኢዮአቄምና ሴዴቅያስ ወንድማማች ሲሆኑ እነርሱም የኢዮስያስ ልጆች ነበሩ። ከኢዮአቄም በኋላ የነገሠው የእርሱ ልጅ የአኪን ሲሆን ናቡከደነፆርም ከአባቱ ዓመፅ የተነሣ ዮአኪንን ቀጥቶታል።

1. ሕዝቡ ወደፊት የሚቀበሉት መከራ ለኤርምያስ ግለጽ ነበር። ምክንያቱም ከፊታቸው ተደቅኖ የሚጠባበቃቸው ምን እንደሆነ እግዚአብሔር ገልጾለት ነበር። ሕዝቡ ግን ይህንን ሊመለከቱ ስላልቻሉ ኤርምያስ የሚናገራቸውን ቸል ብለው ነበር። ሕዝቡም በዚህ አኳኋን እንዲሰቃዩ በጭራሽ የእግዚአብሔር ዕቅድ አልነበረም። እግዚአብሔር እነርሱን ለማዳን የተቻለውን ሁሉ አድርጓል፤ እነርሱ ግን ለመስማትና ለመታዘዝ ፈቃደኛ አልነበሩም። እግዚአብሔርም ትናንሽ የሆኑ ብዙ መቅሰፍቶች አድርሶባቸዋል፤ እነርሱ ግን ከነዚህ ሁኔታዎች መማር አልፈለጉም። እነዚህ ነገሮች የታላቁ የባቢሎናውያን ወረራ ማስጠንቀቂያዎችም እንደነበሩ አልተረዱም ነበር። በመጨረሻም የኤርምያስ ማስጠንቀቂያዎች በ586 ዓ.ዓ. ተፈጽመዋል።

2. የተሰቃዩት ሕዝቡ ብቻ ሳይሆኑ ኤርምያስም ጭምር ነበር። የእርሱም ስቃይ ከእነርሱ በጣም የተለየ ነበር። ኤርምያስ የተሰቃየው እግዚአብሔር በእርሱ በኩል ስላስተላለፈው መልእክት ሕዝቡ ምላሽ አንሰጥም በማለታቸው ነበር። እግዚአብሔርን አንታዘዝም ማለታቸው የሚያመጣባቸው ውጤት ጥፋት ብቻ መሆኑን ኤርምያስ ያውቅ ነበር፤ ለዚህም የኤርምያስን ጸሎት በምዕ. 15:10-12 ና 18-19 እንዲሁም የጸሎቱን መልስ በምዕ. 15:20-21 ተመልከቱ። በተጨማሪም ኤር. 18:19-23 አንብቡ። በመሠረቱ ስለ ኃጢአታቸውና ስለሚመጣባቸው ፍርድ ማልቀስ የነበረባቸው ኤርምያስ ሳይሆን ሕዝቡ ነበር።

3. ሕዝቡ ኤርምያስ ያመጣላቸውን መልእክት ባለመቀበላቸው የእግዚአብሔር ዕቅድ አልፈረሰም፤ ምክንያቱም ተግባራዊ የሚሆንበት ወቅት ተለወጠ እንጂ ዕቅዱ እንዳለ ነበር። በመሠረቱ ንስሐ ሲገቡ እነርሱን መልሶ በማቋቋምና በመባረክ ፈንታ እግዚአብሔር በ70 ዓመታት የባቢሎን ምርኮ ሊቀጣቸው ይገባ ነበር። ነገር ግን ከቅጣቱ በኋላ መልሶ እንደሚያቋቁማቸውና እንደሚባርካቸው ተስፋ ሰጥቶአቸዋል፤ 16:14-15። በምዕ. 1-25 ውስጥ ብዙ የመልካም ምኞትና የተስፋ ቃል ምንባቦች አናገኝም፤ የኤር. 18:1-11 መልእክት ግን የሚያሳየን መልስ ስለመቋቋም ነው። የባቢሎን ምርኮ የመጨረሻው ነገር ሳይሆን እግዚአብሔር ለሕዝቡ ለሚያደርጋቸው አዳዲስ ነገሮች መክፈቻ ነው። የፍርድ መልእክት ትርጉም የተሰጠው የመጨረሻ ነገር አለመሆኑን መሠረት በማድረግ ነው።

1. ይሁዳ ልትዋረድ ሲሆን በእግዚአብሔር የተመረጠው ሕዝብም በዓመፅ ውስጥ ሊጣሉ ነው። ኤርምያስ መልእክቱን በምሳሌ እንዲያሳይ ከእግዚአብሔር ታዟል፤ 13:1-7። ማንኛውንም በምሳሌ የተላለፈውን መልእክት እንዲረዳ ትርጉሙ ተሰጥቷል፤ 13:8-11። ሕዝቡ የበረከት ምልክት አድርገው የወሰዱት ነገር ወደ ጥፋት ይለወጣል፤ 13:12-14። ሕዝቡ ቢሰሙ ሊድኑ ይችላሉ፤ አለበለዚያ ግን ይጠፋሉ፤ 13:15-17። የባቢሎናውያን ወረራ ሴዴቅያስን የመሳሰሉትን ንጉሣዊ ቤተሰብንና በስተደቡብ የሚገኙት ራቅ ያሉ ከተሞችንም የሚጨምር ሲሆን ወራሪዎቹም የሚመጡት ከሰሜን ነው። የእግዚአብሔርም ሕዝብ ከኃጢአታቸው የተነሣ ይበታተናሉ፤ 13:20-27።

2. እግዚአብሔር ባመጣባቸው መቅሰፍት ምንም ትምህርት አላገኙም። አገሪቱ በጣም አስከፊ በሆነ ድርቅ ተመትታ ነበር፤ 14:1-6። ኤርምያስ ስለ ራሱና ስለ ሕዝቡ ይጸልያል፤ እነርሱ ግን አሁንም ንስሐ ገብተው ወደ እግዚአብሔር ለመመለስ ፈቃደኛ አልነበሩም፤ 14:7-9። እግዚአብሔርም ለኤርምያስ መልስ የሰጠው ሲሆን ቁ. 10፥ ኤርምያስም ለሕዝቡ እንዳይጸልይ ነግሮታል፤ ቁ. 11። ንስሐ ካልገቡ እግዚአብሔር ጸሎታቸውን አይሰማም፤ ቁ. 12 ሐሰተኛ ነቢያት ከእግዚአብሔር ያልተላኩትን በመናገር ሕዝቡን ለማሳመንና ለማታለል ይሞክራሉ፤ 14:13-16 ሐዘንና መከራ በሁሉ ቦታ ይገኛል፤ 14:17-18 ኤርምያስም ለሕዝቡና ለምድሪቱ መጸለዩን ይቀትላል፤ 14:19-22።

3. ባቢሎናውያን እንዳይመጡ ንስሐ የመግቢያው ወቅት አልፏል። ምክንያቱም ሕዝቡ ለረጅም ጊዜ እምቢተኞች ነበሩ። አሁን ግን ያለው አማራጭ ፍርድ ብቻ ነው። ምንም ዓይነት ጸሎት ሊያድናቸው አይችልም፤ 15:1-4 መከራ የማይቀበል አንድም የጎበረተሰብ ክፍል አይገኝም። ማንም ማምለጥ አይችልም፤ 15:5-9 ኤርምያስ በሕዝቡ ልበ ደንዳናነት የተሸነፈ ሲሆን ሁኔታውም እርሱ ሊገነዘበው ከሚችለው በላይ ነበር፤ 15:10-12 የይሁዳ ሀብታሞችና ነዋሪው ሕዝብ በጠቅላላ በአጥፊዎች እጅ ይወድቃሉ፤ 15:13-14 ኤርምያስ በበኩሉ ለእግዚአብሔር ተከታታይ ጥያቄዎች ያቀርባል፤ 15:15-18 እግዚአብሔርም ለታማኝ አገልጋዩ ለኤርምያስ ልዩ የተስፋ ቃሉች ይሰጠዋል፤ 15:19-21።

4. ኤርምያስ የሕዝቡን ምላሽ ሲመለከት በሐዘን ይዋጣል። ይህንንም ሁኔታ ለሕዝቡ የሚገልፀው ሚስት ባለማግባትና በተጨማሪም በምንም ዓይነት የቀብር ሥነ ሥርዓት ላይ ባለመገኘት ነው፤ 16:1-4፤ 16:5-9። ሕዝቡም ሌሎች አማልክትን ስላመለኩ እግዚአብሔር ይህን ከፉ ነገር እንዳደረገባቸው ይነግራቸዋል፤ 16:10-13። እግዚአብሔር ግን ሕዝቡን አይተዋቸውም። ወደ ባቢሎን ካስግረካቸው በኋላ መልሶ ያመጣቸዋል፤ 16:14-15። ከዚህ ሁሉ

በፊት ግን ምድሪቱ በሚደርስባት ፍርድ መንጻት አለባት፤ 16:16-18። የነቢዩም እምነት ኃይሉን ለሕዝቡ በሚገልጸው በእግዚአብሔር ላይ ይሆናል፤ 16:19-21።

5. የይሁዳ ሕዝብ ኃጢአት እንደገና በዝርዝር የቀረበ ሲሆን እነዚህም ኃጢአቶች በጣም ከባድ ከመሆናቸው የተነሣ ምንም ነገር ሊፍቃቸው እንደማይችል ተገልጸአል፤ 17:1-4 ሕዝቡ ለመምረጥ እንዲችሉ ሁለት መንገዶች ቀርቦላቸዋል፤ 17:7-8 እግዚአብሔርም እነርሱ የሚመርጡት የቱን እንደሆነ ያውቃል፤ 17:9-10 ለገንዘብ ብሎ እግዚአብሔርን መክዳት ውጤቱ ውርደት ነው፤ ኤር. 17:11-13 ኤርምያስ በዚህ ሁሉ ማድረግ የሚችለው እግዚአብሔር እንዲረዳው በጸሎት መጥራት ብቻ ነው፤ 17:14-18 ሕዝቡ የሰንበትን ቀን ቸል ስላሉና ስላላከበሩ ማስጠንቀቂያ ከእግዚአብሔር ተሰጥቶአቸዋል፤ 17:19-23 መታዘዝም በረከትን እንደሚያስገኝላቸው ተገልጸአል፤ 17:24-27

6. እግዚአብሔር ከሕዝቡ ጋር ያደረገው ግንኙነት በምሳሌያዊ አነጋገር ተገልጸአል። ኤርምያስ ሸክላ ሠሪውን በሥራ ላይ እንዳለ የተመለከተ ሲሆን 18:1-4፥ ልክ እንደዚሁ እግዚአብሔር መበተንና መሰብሰብም ጭምር ይችላል፤ በመዳፍ ውስጥ እንዳለ ሸክላ ነው፤ 18:5-11 ሕዝቡ በእግዚአብሔር እጅ ውስጥ ሆነው ታዛዦች በመሆን ፈንታ ዓምጸው በራሳቸው መንገድ ሄደዋል። ቃል ኪዳኑንም እንኳ ሳይቀር ተቃውመው በጣዖታት መደገፍ ጀምረው ነበር፤ 18:12-17። በተጨማሪም የእግዚአብሔርን መልእክተኛ ለማጥፋት አሢረዋል፤ 18:18። ኤርምያስ ሕዝቡ በተነሳበት ጊዜ እግዚአብሔር እንዲረዳው ሲማፀን እናያለን። ኤርምያስ በመፈጸም ላይ የነበረው ነገር ሁሉ በእግዚአብሔር ቁጥጥር ሥር መሆኑ እንዲያምን የሚያስችለው እምነት ነበረው፤ 18:19-23።

## ንዑስ ክፍል አራት - ልዩ ጠቃሚ ነጥቦች

1. ኤርምያስ ለብዙ ዓመታት ለኢየሩሳሌም ነዋሪዎች ቢሰብክላቸውም እንኳ ንስሐ የመግባት ፍላጎት ግን በጭራሽ አልነበራቸውም። ኢዮሳይስ ያስነሣው የሃይማኖት መነቃቃት የተደረገው በኤርምያስ አገልግሎት መጀመሪያ አካባቢ ነበር፤ 2ኛ ነገ. 22-23። ምንም እንኳ ሕዝቡ ሃይማኖታቸውን እንዲያነጹ ንጉሡ ቢያስገድዳቸውም የሕዝቡ ልብ ግን አልነጻም ነበር። ኤርምያስ ትንቢት ሲነግራቸው ስሜት እርሱን ለመግደል ባደረጉት ሤራ ገልጸውታል። የሰማሪያን ውድቀትና በሌላ በኩል ደግሞ የአሦር፥ የግብፅና የባቢሎንን ሕልውና ስንመለከት ይህ ሁኔታ አስደናቂ ነው። ይሁዳ ግን እግዚአብሔርን በመታመን ፈንታ በጠላቶቹዋ ተመክታ ነበር።

2. እነዚህ ምዕራፎች በማስጠንቀቂያ የተሞሉ ናቸው። እግዚአብሔር በኤርምያስ አማካይነት ለሕዝቡ የሰጣቸው የቃል ማስጠንቀቂያ ብቻ አልነበረም፤ በተጨማሪም ሕዝቡም ሊያስጠነቅቁ የሚችሉ ሌሎች ምልክቶችንም ሰጥቶአቸው ነበር፤ 14:1-6፤ 17:18 ና 16:1-9። ለዚህም በቂ ማስረጃ የሚሆነው ኤርምያስ በባዕድ መንግሥታት ላይ የተናገራቸው ትንቢቶች አብዛኞቹ እርሱ በሕይወት እያለ እንደተፈጸሙ አይተናል። በዚህ ሁሉ ሕዝቡ ፍላጎት ካላቸው ኤርምያስ እውነተኛ ነቢይ መሆኑን መመልከት ይችሉ ነበር። እነርሱ ግን እርሱን በመስማት ፈንታ ተሟገቱት፤ በመግር ፈንታ እንዳልተሳሳቱ አድርገው ራሳቸውን ለማቅረብ ሞከረዋል፤ ማስጠንቀቂያዎቹን ማዳመጥ ስላልፈለጉ የኢየሩሳሌም ከተማ በ586 ዓ.ዓ. ተደመሰሰች።

3. ሕዝቡ ቃል ኪዳኑን መጣሳቸውና ለደኅንነት የተሰጠውን ውል መተላለፋቸውን ጠባያቸው ያረጋግጣል። በእርግጥ እግዚአብሔር አምላካችን ነው ግለታቸው ጥፋት አይደለም። ጥፋታቸው ግን እንደፈለግን ብንናርም የእርሱ ጥበቃ አይለየንም በግለታቸው ላይ ነው። በብዙ ቦታ ኤርምያስ ደግሞ ደጋግሞ ኃጢአታቸውን ሲጠቅስ እናያለን፤ ስካር-13:12-14፤ ሐሰተኛ ነቢያት - 14:13-16፤ ጣዖት አምልኮ - 16:10-13፤ ወደኋላ መመለስ - 18:12-17 የመሳሰሉት ነበሩ፤ እነዚህም ፍርድ የሚመጣባቸው መሆኑን የሚጠቁሙ ምልክቶች ነበሩ። እነዚህ ነገሮች ፍርድ ማምጣታቸው እንደማይቀር ኤርምያስ ያውቅ ነበር። ሕዝቡ ንስሐ ካልገቡ እግዚአብሔር እንደሚቀጣቸው ግልጽ ሲሆን እነርሱ ግን ባለመስማታቸው ንስሐ መግቢያው ጊዜ ሊያልፍ ችሏል።

## ንዑስ ክፍል አምስት - ከአዲስ ኪዳን ጋር ያለው ዝምድና

1. አይለያዩም ማለት ትክክል ባይሆንም አብዛኛውን ጊዜ ኃጢአትና መከራ የተቀራረበ ግንኙነት አላቸው። በኤርምያስ ዘመን በነበሩት አይሁዶች ላይ ግን በትክክል የታየ ሐቅ ነበር። አይሁድ ይሰቃዩ የነበረው በኃጢአታቸው ምክንያት ነበር። እግዚአብሔር ኤርምያስን ወደ እነርሱ ቢልከውም ንስሐ ለመግባት ፈቃደኛ አልነበሩም። ንስሐ እንዲገቡ ለማድረግም እግዚአብሔር ብዙ መከራ አድርሶባቸዋል፤ እነርሱ ግን አልተመለሱም። በኤር. 14:1-6 ውስጥ ስለደረሰባቸው ድርቅ እናነባለን። ይህም የሆነው ከኃጢአታቸው የተነሣ ነበር። አሁንም እግዚአብሔር ወደ እርሱ ለመመለስ እምቢ ያሉትን የእርሱን ቤተሰቦች ይቀጣል። የዚህ መከራ ዓላማው እግዚአብሔር ሊታዘዙትና ሊያከበሩት የሚገባው መሆኑን ለሰዎች ለማሳወቅ ነው።

2. ኤርምያስ እግዚአብሔርን ለማገልገል መክፈል ከነበረበት ዋጋ አንዱ ሐዘን ነበር። እግዚአብሔርን ማገልገል ለኤርምያስ በጣም ከባድ ነበር። ምክንያቱም ኤርምያስ ሕዝቡ የእግዚአብሔርን ቁጣ ከማስነሣት ይልቅ ወደ እርሱ እንዲመለሱ ይፈልግ

ነበር። ኢየሱስም ራሱ ኢየሩሳሌም ለንስሐ የነበራትን እምቢተኝነትና የ70ውን ዓ.ም. ፍርድ ሲመለከት አልቅሶላታል። ጳውሎስም የቆሮንቶስን ክርስቲያኖች ኃጢአትና ንስሐ ባለመግባታቸው አልቅሷል። እግዚአብሔር ለእስራኤል ሕዝብ የነበረውን ፍቅር ለመግለጽ በሆሴዕ ቤተሰብ ላይ አሳዛኝ የሆነ ሁኔታ ተጠቅሟል።

3. እግዚአብሔር፥ ሕዝቡ ኃጢአት ቢሠሩም እንኳ ዕቅዶቹን ሳይፈጽም አይቀርም። ከላይ እንዳየነው ዕቅዶቹ ተግባራዊ ሳይሆኑ የመዘግየት ሁኔታ ቢያጋጥማቸውም እግዚአብሔር ወደ ባቢሎን ተወስደው ከነበሩት መካከል እርሱን ማገልገል የሚችሉ ሰዎች አድኗል። እግዚአብሔር አንዳንድ ጊዜ እንደ ዔሳው ያሉትን ምላሽ የማይሰጡትን ሰዎች አስወግዶ ያዕቆብን የመሳሰሉትን ሰዎች በቦታቸው ይተካል። አይሁድ ወንጌልን አንቀበልም ሲሉ ጳውሎስ ወደ አሕዛብ ሄዷል! ስለዚህ ለተቀረው ዓለም መልእክቱን የሚያደርሱት አሕዛብ ሆነዋል። ከዚህም የምንረዳው ከኃጢአት የተነሣ እግዚአብሔርን ለማገልገል እምቢተኛ የሆኑትን ሰዎች በረከቱን ያጣሉ እንጂ የእርሱን ዕቅዶች አያጨናግፉም። ምክንያቱም እግዚአብሔር ያቀደውን በሌላ መንገድ ተግባራዊ ያደርጋል። የእግዚአብሔርም የአሠራር መንገዶች ዘወትር ትክክልና አግራሞ የማይገኝላቸው ናቸው።

## ንዑስ ክፍል ስድስት - የክለሳ ጥያቄዎች

1. ኤርምያስ ያገለገለው በስንት ነገሥታት ዘመነ መንግሥት ነው?
2. በ609 ዓ.ዓ. በመጊዶ የተገደለው ማን ነው?
3. ኢዮስያስ በንጉሥነት የቆየው ለምን ያህል ጊዜ ነው? ከዚያስ ምን ደረሰበት?
4. ባቢሎን ግብፅን ድል ያደረገችው መቼ ነው?
5. ለባቢሎን የተገዛው የይሁዳ ንጉሥ ማን ይባላል?
6. ኢዮአቄም የሞተው መቼ ነው?
7. ናቡከደነፆር ኢየሩሳሌምን ለሁለተኛ ጊዜ የወረረው መቼ ነው?
8. ከኢዮአቄም በኋላ የነገሠው ማን ነው?
9. ኤርምያስ ለአገልግሎት የተጠራው በኢዮስያስ ዘመን በስንተኛ ዓመት ነበር?
10. ኢዮስያስ የነገሠው መቼ ነው?
11. ኤርምያስ መከራ የማይቀር መሆኑን የተገነዘበው ለምንድነው?

12. ኤርምያስ ለሕዝቡ ሰብኮላቸው ሕዝቡ ንስሐ አንገባም ብለዋል። ታዲያ ለምን ያለቅስላቸዋል?

13. የሕዝቡ ዓመጽ የእግዚአብሔርን ዕቅድ ሊያበላሽ ችሎአል ወይ?

14. በኤርምያስ 13 የተሰጠው ምሳሌ ትርጉም ምንድነው?

15. ድርቁ ምን ውጤት አስከተለ?

16. ንስሐ አንገባም ያሉትን ሰዎች ጸሎት ሊያድናቸው ችሏል ወይ?

17. ኤርምያስ በመምጣት ላይ የነበረውን ፍርድ በምሳሌ እንዲያሳይ የታዘዘው ምን በማድረግ ነበር?

18. የሕዝቡ መታዘዝ የተፈተነው በምድነው?

19. ኤርምያስ ከሸክላ ሠሪው የተማረው ምን ነበር?

20. ኢየሩሳሌም ለኤርምያስ መልእክት የሰጠችው ምላሽ ምን ነበር?

21. እግዚአብሔር የሰጣቸው ምን ዓይነት ማስጠንቀቂያዎችን ነው?

22. የሕዝቡን ልበ ደንዳናነት የሚያሳዩት ነገሮች ምንድናቸው?

## ንዑስ ክፍል ሰባት - አስተዋፅዖ

<u>ውርደት</u>፡- ኤር. 13፡1-27

1-7 - ምሳሌ

8-11 - የተሰጠው ትርጉም

12-14 - ስካር

15-17 - ሕዝቡ እንዲሰማ የተደረገው ጥሪ

18-19 - እውነተኛ ትሕትና

20-27 - በመምጣት ላይ የነበረው ውርደት

<u>አገር አቀፍ መቅሰፍት</u> - ኤር. 14፡1-22

1-6 - ድርቅ

7-9 - ጸሎት

10-12 - የእግዚአብሔር መልስ

13-16 - ሐሰተኛ ነቢያት

17-18 - ቸነፈር

19-22 - ንስሐና ጸሎት

<u>የማይቀር ፍርድ</u> - ኤር. 15:1-21

1-4 - አማላጅ ማጣት

5-9 - የሚመጣው ፍርድ

10-12 - የኤርምያስ ልመና

13-14 - ፍርድ

15-18 - የኤርምያስ ጸሎት

19-21 - የእግዚአብሔር መልስ

<u>ሐዘንተኛው ነቢይ</u> - ኤር. 16:1-21

1-4 - የጋብቻ መከልከል

5-9 - በቀብር ሥነ ሥርዓት ላይ አለመገኘት

10-13 - ጣዖት አምልኮ

14-15 - ስለ መመለስ የተሰጠ ተስፋ

16-18 - ኩብላዮችን ማዳን

19-21 - የእግዚአብሔር ኃይል በተግባር መገለጽ

<u>የይሁዳ ኃጢአት</u> - ኤር. 17:1-27

1-4 - የኃጢአት ዓይነቶች

5-18 - ሁለቱ መንገዶች

19-23 - ሰንበት

24-27 - ስለ መታዘዝ የቀረበ ጥሪ

<u>መለኮታዊ ሽክላ ሠሪ</u> - ኤር. 18:1-23

1-4 - ሽክላ ሠሪው በሥራ ላይ

5-11 - የእግዚአብሔር ዕቅድ

12-17 - ወደኋላ መመለስ

18 - ዛቻዎች

19-23 - የኤርምያስ ጸሎት

## ክፍል ዘጠኝ - ኤር. 19-25

### ንዑስ ክፍል አንድ - ታሪካዊ አቀማመጥ

1. ኢዮስያስ ከሞተ በኋላ ሁለቱ ልጆቹ ኢዮአክስና ኢዮአቄም ነግሠዋል። እነርሱም የነገሡበት ወቅት በአገሪቱ ውስጥ ለውጥ የሚካሄድበት ዘመን ነበር። ግብፅም ደካማ የነበረችውን የባቢሎን መንግሥት ኃያል አንዳትሆን ለብዙ ዓመታ ተዋግታታለች። ባቢሎን ነነዌን በቁጥጥሯ ሥር ማድረግ የቻለችው በ612 ዓ.ዓ. ሲሆን በአሦር የነበሩትን ነገሮች ግን በሙሉ በቁጥጥሯ ሥር ለማድረግ ገና ብዙ የሚቀራት ነገር ነበር። ይህ ማለት ከ612-606 ዓ.ዓ. ድረስ ለስድስት ዓመታት ያህል ባቢሎን የግብፅን ሠራዊት ድል አደረገች፤ እነርሱም እራሳቸውን ለማዳን ሲሉ ወደ ግብፅ መሸሽ ነበረባቸው። ወደ አገራቸውም በሚሸሹበት ወቅት ፈርዖን ኒካው ኢዮአክስን ይዞ ወደ ግብፅ ወሰደው፤ 2ኛ ነገ. 23:33። እርሱም ለ11 ዓመታት ያህል ከነገሠ በኋላ ግብፅን ደግፎ በባቢሎን ላይ ተነሣ። ናቡከደነፆር ወደ ኢየሩሳሌም ከመድረሱ በፊት ኢዮአቄም ታምሞ ስለሞተ ልጁ ዮአኪን በምትኩ ነግሦ ነበር።

2. ናቡከደነፆር በ597 ዓ.ዓ. ኢየሩሳሌምን ለ2ኛ ጊዜ ከመውረሩ በፊት ዮአኪን የነገሠው ለሦስት ወራት ብቻ ነበር፤ 2ኛ ነገ. 24:8 ዮአኪንም ከነ ሕዝቅኤል ጋር በአንድ ላይ ወደ ባቢሎን በምርኮ ተወሰደ፤ 2ኛ ነገ. 24:10-16ና ኤር. 22:24-30። ዮአኪን እስከሚሞት ጊዜ ድረስ ሙሉ ሥልጣኑን የጨበጠ የመጨረሻው የይሁዳ ንጉሥ ነበር፤ 2ኛ ነገ. 25:27-30 ና ኤር. 52:31-34። የአይሁድ ሕግ አንድ ንጉሥ በሕይወት እስካለ ድረስ ሌላ ንጉሥ ሙሉ ሥልጣን አይጨብጥም ስለሚል ዮአኪን በባቢሎን እሥረኛ ቢሆንም እንኳ ሴዴቅያስ ሙሉ ሥልጣን የጨበጠ ንጉሥ አልነበረም። ባቢሎናውያን እርሱን ለምን እንዳነገሡት ለይሁዳ ሊገባቸው ያልቻለ እንቆቅልሽ ነበር።

3. ሴዴቅያስ የመራው ከ597-586 ዓ.ዓ. ነበር፤ 2ኛ ነገ. 24:18-20፤ 2ኛ ዜና 36:11-12 እና ኤር. 52:1-3 ተመልከቱ። እርሱም መጥፎ ንጉሥ ነበር፤ በሌላ በኩል ደግሞ ስለዚህ ዘመን የተነገረ ብዙ ነገር የለም። ኤርምያስም በነዚህ

11 ዓመታት ውስጥ በኢየሩሳሌም ሊተነብይ የቆየ ሲሆን ሕዝቡም ምንም ተስፋ እንዳልነበራቸው ለእርሱ በጣም ግልጽ ሳይሆንለት አይቀርም። እዚህም ሁኔታ ላይ ያደረሳቸው ንስሐ ለመግባት በተደጋጋሚ እምቢተኛ መሆናቸው ነበር። ስለዚህም በመጨረሻ ምንም ሊያደርጉ እማይችሉበት ደረጃ ላይ ሊደርሱ በቅተዋል። ንስሐ ካልገቡ እግዚአብሔር ምሕረት ሊያደርግላቸው አይችልም። ምንም እንኳ ሁኔታው የተስፋ ጭላንጭል የማይታይበት ቢሆንም ኤርምያስ ተስፋ ሊቆርጥ አናይም። እንዲያውም እስከመጨረሻው በታማኝነት ቆይቷል።

## ንዑስ ክፍል ሁለት - የነቢዩ ሸክም

1. ኤርምያስ ከምዕ. 19-25 ባለው ክፍል ውስጥ የሚያተኩረው በመሪዎች ላይ ነው። ለዚህም ሁለት ምክንያቶች ሊኖሩት ይችላል፡- 1ኛ፥ የተቀረውን ሕዝብ እርምጃ የሚቀይሱት እነርሱ ስለሆኑና ሕዝቡ አብዛኛውን ጊዜ መሪዎቻቸውን ስለሚመስሉ ይሆናል። ሆኖም ቀደም ካሉት ምዕራፎች እንደተረዳነው ሕዝቡ የዋህ ነው ማለት አስቸጋሪ ነው። ምክንያቱም የሕዝቡን ኃጢአትና ስሕተት አስቀድሞ ሲጠቁም እናያለን። 2ኛ፥ መሪዎች የሕዝቡ ወኪል ናቸው፤ ስለዚህም ሕዝቡ ምን እንደሚመስል የሚያሳዩን እነርሱ ናቸው። ኤርምያስ በነዚህ ምዕራፎች ውስጥ ስለ ነቢያት፥ ካህናትና ነገሥታት የሚናገር ሲሆን። በተለይም በነገሥታት ላይ ትኩረት ያደርጋል። ስለዚህም በነዚህ ክፍሎች ውስጥ ከኢዮስያስ በኋላ የነገሡትን ሁለት ልጆቹን ኢዮአክስንና ኢዮአቄምን እንመለከታለን። በመጨረሻም የኢዮአቄምን ልጅ ዮአኪንንና ከዚያም ሌላውን የኢዮስያስን ልጅ ሴዴቅያስን እናገኛለን በአጠቃላይ ግን ሁሉም ዓመፀኞች ነበሩ።

2. እግዚአብሔር ለአንዳንድ ሰዎች በሕልምና በራዕይ ይናገር ይሆናል፤ አብዛኛውን ጊዜ ግን ለሕዝቡ በአጠቃላይ ከነቢያቱ መካከል በአንዱ አማካይነት ይናገር ነበር። ሕዝቡም የእግዚአብሔርን ቃል መስማት ስለነበረባቸው እነዚህ ነቢያት በይሁዳና በእሥራኤል የክብር ሥፍራ ተሰጥቶአቸው ነበር። ይህንንም ክብር ለማግኘት ሲሉ ብዙ የሐሰት ነቢያት ተነሥተው ነበር። እነዚህ ነቢያት እውነተኞቹን ነቢያት ከመጥላታቸውም በላይ፤ የተለያየ መልእክትም ያቀርቡ ነበር። ሕዝቡ መስማት የሚፈልጋቸውንና ደስ የሚያሰኙትን እግዚአብሔር ያልተናገራቸውን ነገሮች በማምጣት የሕዝቡን ልብ በቁጥጥራቸው ሥር አድርገው ነበር። ኤርምያስም ይህንን ለመሰለው ሕዝብ ያለው የፍርድ ቃል ብቻ ነበር።

3. ይሁዳ ከኃጢአቷ ያተረፈችው ነገር ቢኖር ፍርድ ብቻ ነው። እግዚአብሔር ቢሆን ይሁዳንና ኢየሩሳሌምን ከመቅጣት በቀር ሌላ አማራጭ አልነበረውም። ያም ቢሆን የእሥራኤል ሕዝብ ታሪክ እዚህ ላይ አላበቃም፤ እግዚአብሔር ምን ጊዜም ቢሆን ያቀደውን ያደርጋል። ለዚህም ማረጋገጫ የሚሆነን እግዚአብሔር ምርኮው ከ606-536 ዓ.ዓ. ለ70 ዓመታት እንደሚቆይ በኤርምያስ አማካይነት በግልጽ የተናገረ ሲሆን ከዚያ በኋላ እግዚአብሔር ከሕዝቡ መካከል ጥቂቶቹን በመመለስ

ለመሢሑ መምጣት እንደሚያዘጋጃቸው ተናግሯል። ከዚህ ትንቢት ውስጥ አብዛኛው ነገር በዘሩባቤል፥ ዕዝራና ነህምያ ዘመን ተፈጽሟል። ይህም እግዚአብሔር ሕዝቡን ከኃጢአትና ከራስ ወዳድነት ቀንበር ነፃ እንደሚያወጣ የሚያሳየን ምሳሌ ነው።

## ንዑስ ክፍል ሦስት - ማብራሪያ

1. ሄኖም የተባለው ሸለቆ የሚገኘው ከከተማይቱ በስተደቡብ በኩል ሲሆን፤ የዚህ ሸለቆ ስም ተለውጦ የሞት ሸለቆ እንደሚባል ይናገራል፤ ኤር. 19፡1-9። ኤርምያስ በእጁ የያዘው ገንቦ ከተማይቱን የሚወክል ሲሆን ይህም ገንቦ ተመልሶ ሊጠገን እስከማይችል ድረስ እንደሚሰባበር ያሳያል፤ ኤር. 19፡10-13። ኤርምያስ ከከተማይቱ በስተደቡብ ከሚገኘው ሸለቆ ተነሥቶ እስከ ከተማይቱ ሰሜናዊ ጫፍ ድረስ በመሄድ በቤተ መቅደስ ውስጥ ቆሞ ቃሉን አውጇል፤ ኤር. 19፡14-15። ኤርምያስ ልክ እንደ እስጢፋኖስ ፍርሐት የማይታይበት ሰው ነበር።

2. ካህኑ የአሜር ልጅ ጳስኮር ነቢዩ ኤርምያስን ደብድቦ እንደ ተራ ሌባ እሥር ቤት አስገብቶታል፤ ኤር. 20፡1-6። ጳስኮር ሌላ አዲስ ስም ተሰጥቶታል፤ ቁ. 3 ኤርምያስ የትንቢት አገልግሎቱን እጅግ አድካሚ ሆኖ ቢያገኘውም መናገሩን አላቋረጠም፤ ኤር. 20፡7-12። በዚህ ክፍል ውስጥ ሳይወለድ ቢቀር የተሻለ መስሎ ታይቶታል፤ ኤር. 20፡13-18። ኤርምያስ ከሕዝቡ ኃጢአት የተነሣ እንደዚህ ከተሰማው እግዚአብሔር ስለ እነርሱ ምን ያህል ያዝንና ይሰቃይ ይሆን?

3. የኢዮስያስ ልጅ ሴዴቅያስ ለራሱ የፈለገውንና የተለየ ነገር እንጂ እግዚአብሔር በነቢዩ ኤርምያስ አማካይነት የላከውን መልእክት አይቀበልም ነበር፤ 21፡1-2። ይህም ንጉሥ ከነቢዩ ሊያመልጥ የሚችልበት ምንም መንገድ አልነበረም። ስለዚህም ኤርምያስ ከእግዚአብሔር የተላከ ልዩ መልእክት ለሴዴቅያስ አምጥቶለታል፤ 21፡3-7። ይህንን መልእክት በኤርምያስ 39፡1-10 ካለው ክፍል ጋር አነፃፅሩ። ከዚህ ቦታ እንደምናነበው እግዚአብሔር የተናገረው ነገር በትክክል ተግባራዊ ሆኗል። ይህም ኤርምያስ በእርግጥ ከእግዚአብሔር የተላከ መሆኑን ለሁሉም የሚያረጋግጥ ነበር። ከመጣባቸውም ቁጣ ማምለጫው መንገድ በባቢሎናውያን እጅ መስጠት ብቻ ነበር። ስለዚህም ሕዝብ ኤርምያስን ቢጠላው ምንም የሚያስደንቅ ነገር የለም፤ 21፡8-10። ክፉ ባሕርይውን በመለወጥ እንጂ በንግግር ብዛት ምንም ዓይነት ንስሐ ማድረግ አይቻልም። ክፉ ድርጊት የሚያመጣው ነገር ቢኖር ጥፋት ብቻ ነው፤ 21፡11-14።

4. ምዕ. 22 ጠቅላላ የተጻፈው ለይሁዳ ነገሥታት ነው። ከኤር. 22፡1-7 ያለው ክፍል ከአምስቱ ነገሥታት ማለት ከኢዮስያስ፥ ኢዮአክስ፥ ኢዮአቄም፥ ዮአኪን እና ሴዴቅያስ መካከል ለአንዱ የተነገረ ነው። ይህም እግዚአብሔር ከእርሱ

የሚፈልገው ምን ዓይነት ባሕርይ እንደሆነ ያሳያል። እግዚአብሔርን የማያውቁት አሕዛብም በእነርሱ ላይ የደረሰውን ፍርድ ተመልከተው ምክንያቱ ምን እንደሆነ ይረዳሉ፤ 22፡8-10። ሰሎም ተብሎ የተጠቀሰው ንጉሥ ኢዮአክስ ነው፤ 22፡11-17። እርሱም በግብፃዊያን ወደ ግብፅ አገር ተወስዶ በዚያ ሞቷል፤ ቁ. 12። ይህም የክፋት ኑሮው ውጤት ነበር፤ ቁ. 13-17። ወንድሙ ኢዮአቄምም ከእርሱ የሚሻልበት ነገር አልነበረውም፤ 22፡18-23። እርሱም በኢየሩሳሌም እንደሚሞት ከመናገሩም በላይ ቁ. 19 ሕዝቡ በእርሱ ሞት ይደሰታሉ እንጂ አያዝኑም። ይህም ንጉሥ ልክ እንደ ወንድሙ ኃጢአተኛ ንጉሥ ነበር። ኢኮንያን የተባለው ንጉሥ የኢዮአቄም ልጅ ዮአኪን ነው፤ 22፡24-30። እርሱም በ597 ዓ.ዓ. በናቡከደነፆር ተማርኮ ወደ ባቢሎን ከተወሰደ በኋላ እዚያው ሞቷል፤ ቁ. 26። ይህ ሁሉ የተፈጸመው እግዚአብሔር በኤርምያስ አማካይነት ይሆናል ብሎ በተናገረው መሠረት ነው።

5. ኤርምያስ በምዕ. 23 ውስጥ ስለተለያዩ መሪዎች በተለይም ስለ ነቢያት ይተነብያል። ስለ እረኞች ሲናገር የሚያመለክተው ነቢያትን፥ ካህናትንና ነገሥታትን ነው፤ 23፡1-4። እንዲጠባበቁት የተነገራቸው ፍጹም የሆነው መሪ እና እረኛ ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ነው፤ 23፡5-6። ፍጹም ሰላምና ደስታ የሚያስገኝ የእርሱ ዘመነ መንግሥት ብቻ ነው። የባቢሎናውያን ምርኮ በእሥራኤል ሕዝብ ዘንድ አዲስ አባባል እንዲፈጥር ያደርጋል፤ 23፡7-8። ሆኖም እግዚአብሔር ያድናቸዋል። የኢየሩሳሌም ነቢያት ጠባይ ለማመን እስኪያዳግት ድረስ በኃጢአት የተበከለ ነበር፤ 23፡9-15። ከገዛ ልባቸው የወጣውን ነገር ይናገሩ ነበር። ከእግዚአብሔር የተቀበሉት አንድም መልእክት የላቸውም፤ 23፡16-22። ሕዝቡን ለማሳሳት ስለ ራሳቸው ሕልም ያወራሉ፤ 23፡23-32። የእግዚአብሔር ቃል ይፈርድባቸዋል። የተቀበሉት መልእክት ወደ ባቢሎን እንዲሸጋገሩ ያደረጋቸውን የራሳቸውን ውድቀት እንጂ የእግዚአብሔርን ሸክም አልነበረም፤ 23፡33-40። እነርሱም ሊሰሙት ተቃውመውት የነበረውን ነገር ይለማመዱታል።

6. ኢዮአቄም የሞተው በ598 ዓ.ዓ. ነበር፤ ልጁ ዮአኪን የተማረከው ደግሞ በ597 ዓ.ዓ. ነበር፤ በምዕ. 24፡1-3 ውስጥ የሚገኝ ራዕይ የተገለጸው በ597 ዓ.ዓ. በሴዴቅያስ ዘመን ነበር። መልካሙም በለስ የሚያሳየው በኢየሩሳሌም የቀሩትን ሰዎች ሳይሆን፤ ወደ ምርኮ የተወሰዱትን ሰዎች ነበር የሚያሳየው፤ 24፡4-7። ሴዴቅያስና በኢየሩሳሌም የቀሩት ሰዎች ሁሉ ዓመፀኞች ስለነበሩ ምንም ተስፋ አልነበራቸውም። ሁሉም ለማንም የማይጠቅሙ ነበሩ፤ 24፡8-10።

7. ከ627-606 ዓ.ዓ. ድረስ ኤርምያስ ለማይታዘዝ ሕዝብ ይሰብክ ነበር፤ 25፡1-7። በመጨረሻም ቃሉን ባለመስማታቸው እነዚህ ሰዎች ወደ ባቢሎን ምርኮ እንደሚወሰዱ ይናገራል፤ 25፡8-14። እግዚአብሔርም የሚፈርደው

በይሁዳ ላይ ብቻ ሳይሆን በዙሪያዋ ባሉት መንግሥታት ሁሉ ላይ ነው። ሁሉም የእርሱን ጻድቅ ፍርድ ይቀበላሉ፤ 25:15-26። ኤርምያስ በሰበከበት ወቅት ምላሽ መስጠት የሚያስችል ምቹ ሁኔታና ምርጫም ነበራቸው። ፍርድ ሲመጣ ግን የመቀበል ወይም የመተው መብቱ የእነርሱ አይደለም፤ 25:27-32። የእግዚአብሔር ፍርድ ሁሉን ነገር አመድ ያደርጋል። በዚህ ጊዜ ምንም መጠለያና ተስፋ አይኖርም፤ 25:33-38።

## ንዑስ ክፍል አራት - ልዩ ጠቃሚ ነጥቦች

1. ነቢያት በአይሁድ መካከል የነበራቸው የሥራ ድርሻ የእግዚአብሔርን ቃል ለሕዝቡ ማሥረዳት ሲሆን፤ አልፎ አልፎም ራዕዮችን ይመለከቱ ነበር። አንዳንዱም ሕልሞችንም ያልሙ ነበር። አልፎ አልፎ ሊመጣ ብዙ ዓመታት ቀርቶ ስለነበረው ስለ መሢሑ ትንቢት ይናገሩ ነበር፤ ለምሳሌ:- 23:5-6ን ተመልከቱ። ሕልም፥ ራዕይና የወደፊቱን ሁኔታ መጠቆም ከነቢያት ተግባር ውስጥ የተወሰኑትና አነስተኛ ክፍል የሆኑት ናቸው። ነቢያት በሕዝቡ መካከል የእግዚአብሔር አፍ ስለነበሩ ሕይወታቸውም ደግሞ ስለ እግዚአብሔር የተረዱትን ዕውቀት ማንፀባረቅ ነበረባቸው። አብዛኞቹ ነቢያት ባሕርያቸው መጥፎ ስለነበር የሚያንፀባርቁትም ነገር በጣም መጥፎ ነበር። በተጨማሪም በእንደዚህ ያለ ወቅት ከእግዚአብሔር ምንም መልእክት አይደርሳቸውም ነበር። እግዚአብሔርም ሕልውናውን አይገልጽላቸውም ነበር። በዚህም ምክንያት ያልተቀበሉትን ውሸት የሆነን ነገር ለሕዝቡ ይናገሩ ነበር። ሐሰተኛ ትንቢቶችን በመናገር ሕዝቡን ለማስደሰት ይሞክሩ ነበር፤ 23:9-32። እነዚህ ሐሰተኛ ነቢያት የኤርምያስ ዋና ጠላቶች ነበሩ።

2. ካህናትም ደግሞ በእግዚአብሔርና በሰው መካከል ልዩ ተግባር እንዲኖራቸው የተመረጡ ነበሩ። ንስሐ ለገቡትም ሰዎች የእግዚአብሔርን ምሕረትና ይቅርታ ያደርሱ ነበር። እነዚህ ሰዎች የሚያመጧቸውን መሥዋዕቶች በቤተ መቅደስ ውስጥ በእግዚአብሔር ፊት ያቀርቡ ነበር። በሕዝቡም ኑሮ ውስጥ ገብተው ያስተምሩ ነበር። እግዚአብሔርም የተለየ የአገልግሎት ሥፍራ ስለሰጣቸው በቀላሉ ሊታበዩ በሚችሉበት ሁኔታ ላይ ነበሩ፤ 20:1-6 ና 23:33-34። በዚህም ምክንያት በመካከላቸው ጥቂቶቹ የመልካም ነገር ምሳሌ በመሆን ፈንታ የክፉ ምሳሌ ሆነው ነበር። ሕይወታቸውም በእግዚአብሔር ምሕረት ስላልተለወጠ የሌሎቹን ሕይወት ለመለወጥ ምንም ድርሻ አላበረከቱም፤ ስለዚህ የእግዚአብሔር ጠላት ሆነው ነበር።

3. በሦስተኛ ደረጃ የእግዚአብሔር አገልጋይ የነበሩ አስተዳዳሪዎች ነበሩ። ከሳኦል አንሥቶ እስከ ሴዴቅያስ ዘመን ድረስ በይሁዳም ሆነ በእሥራኤል የአስተዳደርን ሥራ የሚያከናውኑት ነገሥታት ነበሩ። እነዚህ ሰዎች ልክ እንደ ነቢያትና ካህናት

ሥፍራ ተሰጥቶአቸው ነበር። የሕዝቡን አንድነት መጠበቅ የእነርሱ ተግባር ነበር። ሕዝቡንና የሚኖሩበትን አገር መጠበቅ ነበረባቸው። ልክ እንደ ነቢያትና ካህናት እነርሱም ደግሞ የእግዚአብሔር አገልጋዮች ነበሩ። እነርሱም ልክ እንደሌሎቹ ከእግዚአብሔር ርቀው ነበር፤ 21:3-7 ና 22:1-30። ሁሉም እግዚአብሔርን መታዘዝ እምቢ ስላሉ ተራ በተራ ከእርሱ ዘንድ አስወግዶአቸዋል። ካህኑ ጳስኮር፤ ንጉሡ ሴዴቅያስና ነቢዩ ኤርምያስ ሦስቱም የተለያዩ የሥራ ድርሻዎች የነበሯቸው የእግዚአብሔር አገልጋዮች እንደነበሩ አስተውሉ።

## ንዑስ ክፍል አምስት - ከአዲስ ኪዳን ጋር ያለው ዝምድና

1. ነቢያት ይሁኑ፥ ካህናት ወይም ደግሞ ነገሥታት፥ መሪዎች ሁሉ ከእግዚአብሔር ቃል በታች እንጂ በላይ አይደሉም። ኤርምያስ እግዚአብሔር የተናገረውን ቃል አዳምጦ ታዝዞታል። እርሱ በኢየሩሳሌም ለሰበከላቸው ሰዎች ምሳሌ ሆኖ ነበር። የሌሎችም ሥልጣን ተመሳሳይ ነበር። ካህናትና ነገሥታትም የእግዚአብሔርን ቃል ለመታዘዝ ግዴታ ነበረባቸው። በአዲስ ኪዳንም ውስጥ እግዚአብሔር ቤተ ክርስቲያኑን እንዲመሩ የሾማቸው እንደ ሐዋርያት፥ ዲያቆናት ወዘተ ... የመሳሰሉት የተለያዩ ሠራተኞች እንደሆኑ እንመለከታለን። እነዚህም ሰዎች በአጠቃላይ ቤተ ክርስቲያንን እንዲገነቡ የተለያዩ ሥልጣን ተሰጥቶአቸዋል። ከእነርሱም ገደብ የለሽ ሥልጣን ያለው ሰው የለም፤ ሁሉም ለእግዚአብሔር ቃል መታዘዝ አለባቸው፤ የሚፈረድባቸውም በዚህ መለኪያ ነው።

2. ዘወትር በእግዚአብሔር ሕዝብ ይደርሱ የነበሩት መቅሠፍቶችና መዓቶች የመጡት በእግዚአብሔር ነበር። ሁልጊዜ እግዚአብሔር እነዚህን ነገሮች የሚለካው ከኃጢአት የተነሣ ብቻ አይደለም፤ በተጨማሪም ለሕዝቡ ትምህርት እንዲሆኑትም ነው። ዛሬም በእኛ ላይ የሚመጡብን ማስጠንቀቂያዎች አእምሮአችንን የሰረቁትን ነገሮች በመተው በእግዚአብሔር ላይ እንድናተኩር የሚያሳስቡን ናቸው። ይህን ነገር ብንዘነጋና ችላ ብንል ማስጠንቀቂያዎች ዓላማቸውን ስተው ጭንቀት የሚፈጥሩብን ነገሮች ይሆናሉ።

3. የእውነተኛ ነቢይ ኑሮ ቀላል አይደለም። እግዚአብሔር ለሚያገለግሉት ሰዎች ብዙ ነገሮችን እንደሚያደርግላቸው ተስፋ ገብቶላቸዋል፤ ሆኖም አገልግሎቱ ቀላል ይሆንላችኋል አላለም። ለዚህም ምሳሌ የሚሆነን የእናቶች ነዋሪዎች ኤርምያስን ለመግደል አሚረዋል። በእስያ የነበሩት ሰዎች ጳውሎስን ለመግደል አድመዋል። እስጢፋኖስና ያዕቆብ ታማኝ ምስክሮች ስለነበሩ ተገድለዋል። ሌሎችም እግዚአብሔርን ማገልገል ከመተው መሞት መርጠዋል። ሌሎች ደግሞ እግዚአብሔርን ለማገልገል ስለተጠሩ ብቻ በብዙ የተለያዩ መንገዶች መከራ ተቀብለዋል። ኤርምያስ አንዳንድ ጊዜ አገልግሎቱን እርግፍ አድርጎ እስከመተው ደርሶ ነበር። ተስፋውንም ሁሉ አጥቶ ነበር። በነዚህ ጊዜያቶች ሁሉ

ግን ተስፋ መቁረጥን ድል ለማድረግ እንዲችል እግዚአብሔር ከእርሱ ጋር ነበር።

## ንዑስ ክፍል ስድስት - የክለሳ ጥያቄዎች

1. የነገሡት ሦስት የኢዮስያስ ልጆች እነማን ነበሩ?
2. ከ612-606 ዓ.ዓ. በባቢሎን ምን ዓይነት ሁኔታ ነበር?
3. በ606 ዓ.ዓ. ምን ተደረገ?
4. በባቢሎናውያን አመለካከት የይሁዳ የመጨረሻ ሕጋዊ ንጉሥ ተደርጎ የተቆጠረው ማን ነበር?
5. ከመጨረሻዎቹ አምስት ነገሥታት መካከል እያንዳንዳቸው ለ11 ዓመታት የነገሡት ሁለት ነገሥታት ማንና ማን ናቸው?
6. ኤር. 19-25 በተለይ የሚያተኩረው በማን ላይ ነው?
7. እግዚአብሔር ለሁሉም መናገር ሲፈልግ አብዛኛውን ጊዜ የሚመርጠው የትኛውን መንገድ ነው?
8. ኤርምያስ ከምርኮ ባሻገር ስለሚሆነው ነገር ሲናገር ምን ብሏል?
9. በኤር. 19 ውስጥ የተጠቀሰው ሸለቆ የተሰጠው አዲስ ስም ማን ይባላል?
10. ኤርምያስን የደበደበው ካህን ማን ነበር?
11. በኤር. 21 ውስጥ የሚገኘው የሴዴቅያስ ጥያቄ ምን ነበር?
12. በኤር. 22 ውስጥ የተጠቀሱት ነገሥታት የትኞቹ ናቸው?
13. ኤር. 23 በተለይ የሚጠቁመው የትኞቹን የሕዝቡን መሪዎችን ነው?
14. በኤር. 24 ውስጥ የሚገኘው ምሳሌ ትርጉም ምንድነው?
15. ከሕዝቡ አቋም የተነሣ ፈጽሞ የማይቀር የሆነው ነገር ምንድነው?
16. እግዚአብሔር ለአገልግሎቱ የሚጠቀምባቸው ሦስት ዓይነት ሰዎች ምን ምን ናቸው?
17. የእግዚአብሔርን አገልጋዮች ተግባር የሚቆጣጠረው ምንድነው?
18. ኤርምያስ ብዙ ችግር የሚቀምሰው ለምንድነው?

<u>ፍፃሜ ያገኘ ትንቢት</u> - ኤር. 19፡1-15

1-9 - የሸለቆው መልእክት

10-13 - የገንቦው መሰበር

14-15 - የቤተ መቅደሱመልእክት

<u>ካህኑ ጳስኮር</u> - 20፡1-18

1-6 - የጳስኮር ኤርምያስን መደብደብ

7-12 - የኤርምያስ ማጉረምረም

13-18 - የኤርምያስ የተወለደበትን ቀን መርገም

<u>ሴዴቅያስ</u> - ኤር. 21፡1-14

1-2 - የሴዴቅያስ ጥያቄ

3-7 - በሴዴቅያስ ላይ የተነገረው ትንቢት

8-10 - ሁለቱ መንገዶች (አማራጮች)

11-14 - በንጉሡና በከተማይቱ ላይ የተገጠመ ግጥም

<u>የይሁዳ የመጨረሻ ነገሥታት</u> - 22፡1-30

1-7 - ለንጉሡ የተሰጠ ቃል

8-10 - ራስ መነቅነቅ/ የአሕዛብ እግዚአብሔር ስላደረገው ነገር መገረም

11-17 - ኢዮአክስ / ሰሎም/

18-23 - ኢዮአቄም

24-30 - ዮአኪን / ኢኮንያን/

ለተለያዩ መሪዎችና አገልጋዮች የተጻፈ ክፍል - ኤር. 23፡1-40

1-4 - እረኞች

5-6 - መሢሐዊ ትንቢት (ስለመሢሑ የተነገረ ትንቢት)

7-8 - ባቢሎን /የሠራዊት ጌታ እግዚአብሔር አባባል መቀየር

9-15 - ስለ ሐሰተኛ ነቢያት የተጻፈ ክፍል

16-22 - ስለ ሐሰተኛ ነቢያት የተጻፈ ክፍል

23-32 - ስለ ሐሰተኛ ነቢያት የተጻፈ ክፍል

33-40 - ነቢያትና ካህናት

ስለ መመለስ የተሰጠ የተስፋ ቃል - ኤር. 24፡1-10

1-3 - ከ597 ዓ.ዓ. በኋላ ስለሚሆነው

4-7 - ትርጉም /ለኤርምያስ የተሰጠ ራዕይ ትርጉም

8-10 - መጥፎው በለስ

የማይቀረው ፍርድ - ኤር. 25፡1-38

1-7 - 605 ዓ.ዓ. /የእግዚአብሔር ደጋግሞ ማስጠንቀቅ

8-14 - ምርኮ / የማይቀረው ምርኮ/

15-26 - ጽዋ

27-32 - ፍርድ

33-38 - ብጥብጥ /መከራና ችግር/

## ክፍል አሥር - ከለሳ

### ንዑስ ክፍል አንድ - ታሪካዊ አቀማመጥ

1. ኤርምያስ በ627 ዓ.ዓ. የትንቢት አገልግሎት እንዲጀምር ከመጠራቱ በፊት እግዚአብሔር ብዙ ሌሎች ነቢያትን በይሁዳና በእሥራኤል አስነሥቶ ነበር። ከእነዚህ መካከል የመጀመሪያዎቹ በእሥራኤል ያገለግሉ የነበሩት እና ስማቸውን በደንብ የምናውቃቸው ኤልያስና ኤልሳዕ ነበሩ፤ 1ኛ ነገ. 17-2ኛ ነገ. 13።

ከነዚህ ቀጥሎ ደግሞ የተነሡት ሆሴዕና ዓሞን ነበሩ። እነዚህ ሁሉ ይተነብዩ የነበረው ከኤርምያስ በጣም ቀደም ብለው ነበር። ኢሳይያስ መተንበይ የጀመረው በ740 ዓ.ዓ. ንጉሥ ዖዝያን በሞተበት ዘመን ሲሆን። ይህም ከኤርምያስ 113 ዓመታት ቀደም ብሎ ነው። የኢሳይያስ ባልደረባ ሚክያስ ነበር። ሚክያስም ይተነብይ የነበረው ከኢሳይያስ ጋር በአንድ ዘመን ውስጥ ነበር። ሁለቱም ይተነብዩ የነበረው በሦስት የይሁዳ ነገሥታት በኢዮአታም፥ አካዝና፥ ሕዝቅያስ ዘመነ መንግሥት ነበር። ሕዝቅያስ መልካም ንጉሥ ነበር። በተቃራኒው ግን ልጁ ምናሴና የልጁ ልጅ ዓሞን ግን ሁለቱም በጣም ዓመፀኞች ነበሩ። በነርሱ ዘመነ መንግሥት በይሁዳ ምንም ነቢይት አልነበረም።

2. ከሁሉም መልካም ንጉሥ የነበረው የዓሞን ልጅ ኢዮስያስ ነበር። በእርሱም ዘመነ መንግሥት እግዚአብሔር ሁለት ነቢያትን ለይሁዳ ልኳል። ኢዮስያስ መልካም ንጉሥ በመሆኑ የነቢያቱን ሥራ አላቃለለም ነበር። እንደ እውነቱ ከሆነ በጣም አስቸጋሪ ዘመን የነበረው የኢዮስያስ ዘመን ነበር። ኤርምያስና ሰፎንያስም ይተነብዩ የነበረው በኢዮስያስ ዘመነ መንግሥት ነበር። ኤርምያስ ከ627 ዓ.ዓ. እንሥቶ እስከ 586 ዓ.ዓ. እና ከዚያም በኋላ ከ40 ዓመታት በላይ አገልግሏል። ኤርምያስ ባቢሎናውያን ከተማይቱን ለማጥፋት እንደተቃረቡ ተናግሮ ነበር። ዕንባቆምም ለምን እግዚአብሔር ይህንን ኃጢአተኛ መንግሥት እንደመረጠ ጠይቆታል።

3. ኤርምያስ በሕይወት በኖረበት ዘመን ውስጥ በሦስት የተለያዩ ጊዜያቶች የይሁዳ ሰዎች ወደ ባቢሎን ተወስደዋል፤ ይኸውም በ606፥ በ597 ና እንደገናም በ586 ዓ.ዓ. ነበር። በዚያን ጊዜ ተስፋ የነበራቸው ወደ ባቢሎን የተወሰዱት ሰዎች ብቻ ሲሆኑ እግዚአብሔርም በጣም የተለየውን ነቢይ ሕዝቅኤልን ልኮላቸው ነበር። በይሁዳ ግን ከ586-536 ዓ.ዓ. ባለው ጊዜ ምንም ነቢይ አልነበረም፤ ባቢሎን ግን ሕዝቅኤልና ዳንኤል ሁለት ነቢያት ነበሩ። የእነዚህ ሰዎችም የተለየ ተግባር በባቢሎን የነበሩትን አይሁዶች ማጠናከርና ወደ ኢየሩሳሌም እንዲመለሱ የሚፈቅድላቸው ቂሮስ የተባለው ንጉሥ ለሚነሣበት አስደናቂ ቀን ሕዝቡን ማዘጋጀት ነበር። ኤርምያስ ግን ምርኮኞቹ ሳይመለሱ ወደ ግብፅ ተወስዶ በዚያው ሞቶ ነበር።

## ንዑስ ክፍል ሁለት የነቢዩ ሽክም

1. ኤርምያስ የመልእክቱ ሽክም ይህ ቢሆንም እንኳ ሕዝቡን አዘውትሮ ለንስሐ አይጠራም ነበር። ምክንያቱም እርሱ በሚተነብይበት ጊዜ ሕዝቡ ለንስሐ የተዘጋጀ ልብ አልነበራቸውም ነበር። ዝግጁ ሳይሆኑ ደግሞ ንስሐ ቢገቡ ምንም ጥቅም የለውም። ሕዝቡም ኃጢአታቸውን አልተገነዘቡም ነበር። የእግዚአብሔርን ቃል ኪዳን እንደጣሱ አልተረዱም ነበር። ፍርድ የማይቀር መሆኑን ማየት ተስኗቸው ነበር። ስለዚህም ወደ እግዚአብሔር ከመመለሣቸው

በፊት እነዚህን ነገሮች ሁሉ መረዳት ነበረባቸው፤ በአጠቃላይ ከኤርምያስ ሸክሞች መካከል አንዱ ሕዝቡ ንስሐ ገብተው ወደ እግዚአብሔር እንዲመለሱ ነበር። ምክንያቱም ይህንን ካላደረጉ የእግዚአብሔር ትዕግሥት እንደሚያልቅና ፍርድ እንደሚመጣባቸው ያውቅ ነበር።

2. በአጠቃላይ ፍርድ ተግባራዊ ሊሆን እንደሚችል ግልጽ ነበር። ኤርምያስ ከመጠራቱ 100 ዓመታት ቀደም ብሎ ከ12ቱ ነገዶች መካከል አሥሩ በአሦር አማካይነት በምርኮ ተወስደው ነበር። የተረፉትም ይሁዳና ቢኒያም ብቻ ነበሩ። ነነዌ ስትሸነፍ ደግሞ ኤርምያስ ተመልክቷል። ይህም የይሁዳ ሕዝብ በትዕቢት እንዲነሳ ሳያደርገው አይቀርም። በዚህም የተነሣ ትልቋ ጠላታችን ተሸንፋለች ብለው አስበው ነበር። እንደዚህ በማለታቸው ተሳስተዋል። ምክንያቱም በአካባቢው ሌላ ኃያል መንግሥት በባቢሎን ብቅ ልትል ችላለች። ስለዚህ በደቡብም ያለው ሕዝብ ከልቡ ንስሐ ካልገባ እግዚአብሔር ባቢሎንን እንደሚጠቀምበት ግልጽ ነበር። ይህም በ586 ዓ.ዓ. ተግባራዊ ሆኖአል።

3. በኤርምያስ መጽሐፍ በተደጋጋሚ የምናገኘው ሦስተኛው ዓቢይ ትምህርት የተስፋ ቃል ነው። እግዚአብሔር ለሕዝቡ ሁለት ዓይነት የተስፋ ቃሎች ሰጥቶአቸው ነበር፤ አንደኛው ታዛዥነታቸውን የተመረኮዘ ነበር። ይኸውም ባቢሎናውያን ሲመጡ እጃቸውን ከሰጡ እነርሱና ከተማቸው እንደሚድኑ የተሰጣቸው የተስፋ ቃል ነበር። ሕዝቡ ግን ይህንን የተስፋ ቃል አልተቀበሉም። በሁለተኛ ደረጃ ደግሞ ከምርኮው በኋላ እግዚአብሔር የተወሰነ ሕዝብ ከባቢሎን ወደ ይሁዳ መልሶ እንደሚመጣ የተስፋ ቃል ገብቶላቸዋል። ይህም ሕዝብ ልክ እንደተስፋ ቃሉ በዳንኤልና በሕዝቅኤል አገልግሎት አማካይነት ይህንን ሕዝብ ያዘጋጀ ሲሆን፤ ይህ ሕዝብም በዘሩባቤል፥ በዕዝራና በነህምያ ሥራ ሆኖ ወደ ይሁዳ ሊመለስ በቅቷል።

## ንዑስ ክፍል ሦስት - ማብራሪያ

1. መጽሐፉ በአጠቃላይ ስለምን እንደሚያስተምር በአጭሩ መረዳት እንድንችል ንድፉ ከተጠና በኋላም ብዙ ነገሮችን መጨመር ሳያስፈልግ አይቀርም። ምክንያቱም ይህ የመጽሐፉ ጥናት ጅማሬ እንጂ ፍጻሜ አይደለም። ስለዚህ ይህንን በደምብ ካጠናችሁ በኋላ ራሳችሁ ሌላ ጨምሩበት።




2. የመጀመሪያዎቹና የመጨረሻዎቹ ምዕራፎች ከተቀረው የመጽሐፉ ክፍል የተለዩ ስለሆኑ ለብቻቸው አቅርበናቸዋል። በምዕ. 1 ውስጥ ኤርምያስ ነቢይ እንዲሆን የመጣለት ጥሪ በዝርዝር ቀርቧል። በምዕ. 52 ውስጥ ደግሞ የይሁዳና የኢየሩሳሌም የመጨረሻ ሁኔታ ማጠቃለያ ተሰጥቶናል። ይህም በ2ኛ ነገ. 25 ውስጥ ከምናገኘው ታሪክ ጋር ተመሳሳይ ነው።

3. ምዕ. 26ን የመጽሐፉ ማዕከል አድርገን ያቀረብነው ሲሆን እንደገና መነበብ አለበት። ይህም ክፍል የተለያዩ የሕዝቡ ንዑሳን ክፍሎች ለኤርምያስና ለመልእክቱ የነበራቸውን አመለካከት የሚያሳይ አጭር ማጠቃለያ ነው።

በእርግጥ ኤርምያስ ታማኝ ሰው ነበር። ሕዝቡ ግን ዓመፀኞች ነበሩ። በተጨማሪ ምዕ. 26 መጽሐፉን በሁለት ክፍሎች ይከፍለዋል።

4. በምዕ. 2-25 ውስጥም ሁለት ክፍሎች እናገኛለን። በምዕ. 2-13 ባለው ክፍል ውስጥ ኤርምያስ ስለ ሁለት ነገሮች ማለት ስለ ቤተ መቅደሱና ስለ ቃል ኪዳኑ ሲሟገት እናያለን። ሕዝቡ እነዚህን ሁለት ነገሮች ካሉን እንደፈለግነው መመላለስ እንችላለን ብለው ያስቡ ነበር፤ እግዚአብሔርም ምንም ዓይነት እርምጃ የሚወስድባቸው አይመስላቸውም ነበር። ኤርምያስ ግን ለሕዝቡ ቃል ኪዳኑና ቤተ መቅደሱ ሁለቱም የእግዚአብሔር ሕግ መጠበቅ እንዳለባቸው እንደሚያስገነዝቡ ያሳያቸዋል።

5. በምዕ. 14-25 ባለው ክፍል ውስጥም ፍርዱ የማይቀር ነገር መሆኑን በተደጋጋሚ ነግሮአቸዋል። ሕዝቡ በአሦር ውድቀት በመደሰታቸው እጅግ ተታልለዋል። ምክንያቱም በአሦር ቦታ እግዚአብሔር ባቢሎንን ሊያስነሳ ችሏል። ስለዚህም ይሁዳንና ኢየሩሳሌምን ለመቅጣት ይጠቀምበታል።

6. የመጽሐፍ የመጨረሻ ግማሽ ክፍል ማለትም ከኤር. 27-51 ያለው ክፍል በሁለት ክፍሎች ተከፍሏል። መጽሐፉ በአጠቃላይ የሠፈረው በተነገረበት ዘመን ቅደም ተከተል ሳይሆን በርዕሶች ተከፋፍሎ ነው። ምዕ. 46-51 በቀላሉ ሊታወስ የሚችል ክፍል ከመሆኑም በላይ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ከምናገኘው ከየትኛውም ክፍል የተለየ ነው። ምክንያቱም ከ586 ዓ.ዓ. በኋላ በይሁዳ እና በኢየሩሳሌም ምን እንደተፈጸመ የሚነግረን ይህ ክፍል ነው። ኤርምያስም ተገዶ ወደ ግብፅ እንደተወሰደና እዚያም ሳይሞት እንዳልቀረ የሚነግረን ይኸው ነው።

7. ኤር. 27-45 የሚያቀርበው በሴዴቅያስ ዘመነ መንግሥት ማለት ከ597-587 ዓ.ዓ. ባለው ዘመን ውስጥ የተፈጸሙ የተለያዩ ነገሮችን ሳይሆን አይቀርም። ሕዝቡ የኤርምያስን መልእክት ሲቃወሙ እናያለን፤ ምዕ. 27-29። እግዚአብሔር ግን እንደማይተዋቸው ይናገራል ምዕ. 30-33። በኤርምያስ መጽሐፍ ውስጥ ወደ ፊት ስለሚፈጸሙ ነገሮች የተሰፋ ቃል የሚያቀርበው ከምዕ. 30-33 ያለው ክፍል ነው። ኤርምያስ በምዕ. 34-39 ባለው ክፍል ውስጥ ሕዝቡ ከእግዚአብሔር የመጣላቸውን መልእክት እንዲታዘዙ ለማሳመን የመጨረሻ ሙከራ ሲያደርግ እናያለን። ምዕ. 40-45 ደግሞ በ586 ዓ.ዓ. በኢየሩሳሌም ላይ ስለመጣባት ጥፋት ይናገራል።

1. የኤርምያስ ትንቢት የእግዚአብሔርን ትዕግሥት ያሳያል። እግዚአብሔር ከነቢዩ ኤርምያስ በተጨማሪ ሕዝቡ ንስሐ ገብተው ወደ እግዚአብሔር እንዲመለሱ ያበረታታቸውን መልካም ንጉሥ ኢዮስያስን ልኮ ነበር። ሕዝቡም የሚነግራቸውን የሚያደርጉ ይመስሉ ነበር። ሆኖም በልባቸው ውስጥ የነበሩትን ጣዖታት አውጥተው መጣል አልቻሉም ነበር። ኤርምያስ ለ40 ዓመታት ሰብኳል። እግዚአብሔር ለ40 ዓመታት ሳይፈርድባቸው ታግሶአቸዋል። ከዚህም በተጨማሪ እግዚአብሔር በባቢሎን በምርኮ ለነበሩት ሰዎች ሁለት ነቢያት ማለት ሕዝቅኤልንና ዳንኤልን ልኮላቸው ነበር። ከ586 ዓ.ዓ. በኋላም ቢሆን በይሁዳ ቀርተው የነበሩትን ሰዎች እግዚአብሔር ታግሶአቸዋል። እንደገና ካመጹም በኋላ እንኳ ጥበቃ እንደሚያደርግላቸው ቃል ገቦላቸው ነበር። እነርሱ ግን በዚህ ፈንታ ወደ ግብፅ ለመኮብለል ወሰኑ፤ ስለዚህ ሕዝቡ የተፈረደባቸው እግዚአብሔርን ትዕግሥት ስላስጨረሱት ብቻ ነበር።

2. የኤርምያስ ትንቢት የእግዚአብሔርን ምሕረት ያሳያል። እግዚአብሔር በምናሴና በዓሞን ዘመነ መንግሥት የሕዝቡን ዓመፅ ተመልከቷል፤ ሆኖም አላጠፋቸውም። መልካም ንጉሥና በርከት ያሉ ነቢያትን ልኮላቸዋል። በጣም በማይጎዷቸው ትናንሽ ፍርዶች አስጠንቅቆአቸዋል ናቡከደነፆር በ606 ዓ.ዓ. ለመጀመሪያው ጊዜ፥ በ597 ዓ.ዓ. ለሁለተኛ ጊዜ ወደ ኢየሩሳሌም በመምጣት ወሯታል፤ እነርሱ ቢቃወሙትም እንኳ እግዚአብሔር በምሕረቱ ሕዝቡን ያስጠነቅቅ ነበር። የ586 ዓ.ዓ. ፍርድም እንኳ ቢሆን ምሕረት ያለው ነበር።

3. የኤርምያስ ትንቢት የእግዚአብሔርን ታማኝነት ያሳያል። እግዚአብሔር ከሕዝቡ ጋር ቃል ኪዳን መሥርቷል፤ ከሕዝቡ መካከል ብዙዎቹ ባያከብሩትም እንኳ እግዚአብሔር ታማኝነቱን ጠብቋል። ምንም እንኳ ብዙ ሕዝብ ካለመታዘዙ የተነሣ እነዚህን የተስፋ ቃሎች ባይወርስም የእግዚአብሔር የተስፋ ቃሎች በጭራሽ አይሻሩም። በይሁዳም ቢሆን እግዚአብሔር ከሰጣቸው የተስፋ ቃሎች መካከል ጥቂቶቹ ሳይፈጸሙ በፊት እግዚአብሔር ሕዝቡን ወደ ባቢሎን ምርኮ መላክ ነበረበት። ታማኝ የሆነ የሕዝቡ ቅሬታ ከኢየሩሳሌም ከመምረጥ ይልቅ ከባቢሎን መምረጥ ነበረበት። ይህ ሁሉ የሚያሳየን የሕዝቡ ኃጢአተኝነትም ቢሆን እንኳ እግዚአብሔር ዕቅዶቹን እንዲለውጥ ለማድረግ አልቻለም። ስለዚህ የሕዝቡ እምነተ ቢስነት በግልጽ የሚያሳየው የእግዚአብሔርን ታማኝት ነበር። ኤርምያስ የእግዚአብሔር ቃል ዘላለም እንደሚጸናና እንደማይለወጥ ተረድቶ ነበር።

## ንዑስ ክፍል አምስት-ከአዲስ ኪዳን ጋር ያለው ዝምድና

1. እግዚአብሔር የእርሱ ቤተሰብ ከሆኑት ሰዎች ሁሉ መታዘዝን ይፈልጋል። የይሁዳ ሕዝብ የሚያስፈልጋቸው ቃል ኪዳኑ ብቻ መስሎአቸው ነበር። ቃል ኪዳኑ ደግሞ እግዚአብሔር በመታዘዝ የተሞላ መሆኑን ለመቀበል አልፈለጉም ነበር። በመሠረቱ የቃል ኪዳኑ ተካፋይ መሆን የሚችለው በመታዘዝ ሳይሆን በጸጋ ነው። ሆኖም ግብዣውን የተቀበሉት ሰዎች በኤርምያስ ሆነ በእኛም ዘመን በቃል ኪዳኑ መመሪያዎች መሠረት መኖር አለባቸው። በእርግጥ ባለመታዘዛቸው በቃል ኪዳኑ ውስጥ ያላቸውን ድርሻ አያጡም፤ ነገር ግን የቃል ኪዳኑን ቅጣቶች ይቀበላሉ። ቃል ኪዳኑን መጠበቃቸውም እግዚአብሔርን በመታዘዛቸው ይገለጻል። ይህም በኤርምያስም ዘመን ሆነ በእኛ ዘመን በረከትን ያስገኛል።

2. እግዚአብሔር በቃል ኪዳኑ ውስጥ ያሉትን የማይታዘዙ ሰዎች ጽድቁን ለማሳየትና በአገልግሎታቸው ጠቃሚ እንዲሆኑ ለማድረግ ይቀጣቸዋል። የኢየሩሳሌምና የይሁዳ ኃጢአት ለሁሉ የተገለጠ ነበር። ለዚህም ኃጢአታቸው ግልፅ በሆነ አኳኋን ቅጣት ካልተቀበሉ እግዚአብሔር በችልተኝነት ያለፋቸው መስሎ ይታያቸዋል። እግዚአብሔር ደግሞ በባሕርይው እንደዚህ ሊያደርግ አይችልም። ምክንያቱም ኃጢአት ሕዝቡን ለእርሱ አገልግሎት መስጠት እስከማይችል ድረስ ከጥቅም ውጭ ያደርጋል። ሕዝቡ የነቢዩን ቃል ሰምተው ካልተመለሱ እግዚአብሔር ያለው አማራጭ ቢኖር እነርሱን መቅጣት ብቻ ነው። የኤርምያስ መጽሐፍም ይህንን እውነት በብዙ ሥፍራዎች ይገልጻል።

3. የእግዚአብሔር ፍላጎት አሁንም የጠፋውን ወደ እርሱ መመለስ ነው። በዚህ ዘመንም ሰዎች ወደ ቃል ኪዳኑ ውስጥ ሊገቡ የቻሉት በጸጋ ነው። ከዚህ በኋላ የቃል ኪዳኑን ትዕዛዛት ከፍቅር የተነሣ እንዲጠብቁ ይገደዳሉ። በኃጢአት ቢታለሉ ወይም ቢጠመዱ እግዚአብሔር አይተዋቸውም። እርሱ አፍቃሪና ቸር ስለሆነ ወደ እርሱ እንዲመለሱ ይጠራቸዋል። እግዚአብሔር ኢዮስያስንና ኤርምያስን የላከበት ዓላማ ሕዝቡ ከጥፋት እንዲመለስ ጥሪ ለማድረግ ነበር። ወደ ባቢሎን ምርኮ ልኳቸው እነርሱን በቀጣበት ወቅትም እንኳ ቢሆን ከዋና ዋናዎቹ ዓላማዎች መካከል አንዱ እነርሱን መልሶ ለማቋቋም ነበር። የመሢሑን መምጣት የሚጠባበቅ የተጣራ ሕዝብ ከባቢሎን ሊመለስ በቅቷል።

## ንዑስ ክፍል ስድስት - የክለሳ ጥያቄዎች

1. ከ1ኛ ነገ. 17-2ኛ ነገ. 13 ያለው ክፍል የሚነግረን ስለ ማንና ማን ነው?
2. በ740 ዓ.ዓ. መተንበይ የጀመረው ማን ነው?
3. ኢሳይያስና ሚክያስ ትንቢት የተናገሩት በማን ዘመነ መንግሥት ነበር?

4. የሕዝቅያስ ልጅ ማን ነው?

5. የዓሞን ልጅ ማን ነው?

6. በኢዮስያስ ዘመነ መንግሥት የተነበዩት ሁለት ነቢያት እነማን ናቸው?

7. ምርኮኞች ከይሁዳ የተወሰዱት መቼ ነበር?

8. በባቢሎን ይተነብዩ የነበሩት ነቢያት ማንና ማን ነበሩ?

9. ኤርምያስ ከንስሐ ይልቅ ስለ ምን ይናገር ነበር?

10. እስራኤል በአሦር የተያዘችው መቼ ነበር?

11. የአሦር ዋና ከተማ ነነዌ የተያዘችው መቼ ነበር?

12. አሦር የተተካችው በየትኛው መንግሥት ነበር?

13. በኤርምያስ መጽሐፍ ውስጥ የሚገኙት ሁለት ዋና ዋና የተስፋ ቃሎች ምንና ምን ናቸው?

14. የተወሰነ ሕዝብ የተመለሰው መቼ ነበር?

15. ሥዕላዊ መግለጫ ለምን ይጠቅመናል?

16. ኤር. 1ና 52 የሚናገሩት ስለ ምንድነው?

17. ኤር. 26 የሚናገረው ስለ ምንድነው?

18. በኤር. 2-13 ውስጥ የሚገኙት ሁለት ዋና ዋና ትምህርቶች ምን እና ምን ናቸው?

19. ኤር. 46-51 ያለው ክፍል የሚነግረን ስለ ምንድነው?

20. የኤር. 27-45 አራት ዓበይት ትምህርቶች ምን ምንድናቸው?

21. ኤርምያስ ስለ ቤተ መቅደሱና ቃል ኪዳኑ የሚገልጽላቸው ነገር ምንድነው?

22. በ612 ዓ.ዓ. ይሁዳ የተደሰተችው በማን ውድቀት ነበር?

23. ኤርምያስ የተነበየው ለስንት ዓመታት ነው?

24. በኤርምያስ መጽሐፍ ውስጥ በተገለጸው መሠረት የእግዚአብሔርን ትዕግሥት የሚያሳዩ ምሳሌዎች ስጥ?

25. በ586 ዓ.ዓ. የነበረው የባቢሎን ንጉሥ ማን ነበር?

26. እግዚአብሔር ከ640-536 ዓ.ዓ. ባለው ዘመን ውስጥ ምሕረትን በይሁዳ የገለጸው በምን ዓይነት መንገድ ነው?

27. የባቢሎን ምርኮ የእግዚአብሔርን ቃል ኪዳን ይሽራል?

28. እግዚአብሔር ታማኝ የሕዝብ ቅሬታ የመረጠው ከነማን መካከል ነው?

29. የይሁዳ ሕዝብ እምነተ ቢስነትን አጉልቶ የሚያሳየው ምንድነው?

30. የእስራኤል ሕዝብ የቃል ኪዳኑ ተካፋይ የሆነው በምንድነው?

31. ቃል ኪዳኑ ከተካፋዮቹ የሚሻው ምንድነው?

32. እግዚአብሔር የማይታዘዙትን የሚቀጣው ለምንድነው?

33. እግዚአብሔር ወደ ባቢሎን ከሄዱት መካከል ብዙዎቹን ያዳነው ለምንድነው?

## መልሶች

### ክፍል አንድ

1. በ627 ዓ.ዓ.
2. በ687 ዓ.ዓ. ገደማ
3. ምናሴና ዓሞን
4. ኢዮስያስ ስላስነሣው መነቃቃት
5. ለ 40 ዓመታት ያህል
6. ሶፎንያስ
7. ሕዝቅኤልና ዳንኤል
8. የኢየሩሳሌም በ586 ዓ.ዓ. መደምሰስ
9. ባቢሎን
10. አሦር
11. ቃል ኪዳኑን ስለሰበረ
12. የኢየሩሳሌም በ586 ዓ.ዓ. መደምሰስ
13. በአናቶት

14. እግዚአብሔር ስለቀባው
15. ቅርንጫፍ
16. በባቢሎናውያን የሚደረገው ወረራ
17. ሴዴቅያስ
18. እጁን ለባቢሎን ከሰጠ በኋላ እንደገና ማመፅና ሕዝቡንም ማሳመፅ
19. ሙሉ በሙሉ ከደመሰሳት በኋላ አቃጠላት
20. በሙሉ ወደ ባቢሎን ተወሰዱ
21. በሪብላ
22. ሦስት ጊዜ
23. የእኪን
24. ከእግዚአብሔር ሕዝብ ኃጢአት የተነሣ
25. ቅጣት

## ክፍል ሁለት

1. በባዕድ መንግሥት ላይ ፍርድ የሚናገር
2. አብዛኛዎቹ ከ586 ዓ.ዓ. በፊት
3. ስለ ባቢሎን
4. ከ606-5 ዓ.ዓ.
5. ግብፅ፥ ፍልስጢኤምና ባቢሎን
6. አሞን፥ ሞዓብና፥ ኤዶም
7. ደማስቆ፥ ቄዳር፥ አሦር
8. አካዝ
9. እግዚአብሔር እነዚህን መንግሥታት በሙሉ በቁጥጥሩ ሥር ማድረጉ
10. የፍልስጤም ከተሞች መደምሰስ
11. ከጨው ባሕር በስተምሥራቅ የምትገኘውን ሞዓብን
12. ባቢሎን

13. ናቡከደነፆር

14. ባቢሎን በሜዶንና በፋርስ ተደመሰሰች፤ ከዚያም በአሸዋ ሥር ተቀብራ ለዘመናት ተረስታ ቆይታለች

15. ከንቱነታቸው ተገለጠ

16. በእግዚአብሔር ሥራ ላይ ተቃውሞ በሚያደርሱ የተባበሩ ኃይሎች

## ክፍል ሦስት

1. የኤርምያስ ጥሪን የ586 ዓ.ዓ. ድርጊቶች

2. በባዕድ መንግሥታት ላይ ስለሚደርሰው የእግዚአብሔር ፍርድ

3. ምዕ. 41-45

4. እግዚአብሔር ወደፊት ለሕዝቡ ስለሚያደርግላቸው ነገሮች የተሰጠ የተስፋ ቃል ነው

5. ጻድቅነቱ

6. ጣዖት አምልኮ

7. እግዚአብሔር መልሶ እንደሚያቋቁማቸው የተስፋ ቃል ስለ ሰጠ ነው

8. ሚክያስ

9. ስለ ሸሸ ተገደለ

10. ለናቡከደነፆር

11. ሐናንያ

12. ሕዝቡ ኤርምያስን ይዘው እንዲቀጡት

13. እግዚአብሔር ሕዝቡን መልሶ እንደሚያቋቁም

14. ኤር. 31

15. እግዚአብሔር ለኤርምያስ መሬት እንዲገዛ መንገሩ

16. እጃችሁን ለባቢሎን ስጡና እግዚአብሔር ያድናችኋል የሚል ነው

17. ተቃውሞ

18. የተወሰነ ሕዝብ ከባቢሎን ተመልሶ መምጣት

## ክፍል አራት

1. 597-586
2. በአርዕስት ተከፋፍለው ነው
3. 627
4. ኢዮስያስ
5. ሕዝቡን
6. በግብፅ
7. የቃል ኪዳን ሕግ
8. ነፃነት
9. እግዚአብሔር፤ ከኃጢአታቸው የተነሣ ሊቀጣቸው
10. የተጣራ የሕዝቡን ቅሪታ
11. ሕዝቡን መልሶ ማቋቋምና ማነቃቃት
12. አዜቃና ለኪሶ
13. እምነት
14. ለኢዮአቄም
15. በግብፅ
16. አቤሜሌክ
17. ሴዴቅያስ
18. ለሌሎች እንዲተላለፍ ነው
19. አብዛኞቹ አንቀበልህም አሉት
20. እጃቸውን ለባቢሎናውያን ቢሰጡ ነው
21. ሁለቱም የባሕርይ ነፀብራቆች ስለሆኑ ነው
22. በመልእክተኞች አማካይነት
23. የማይታጠፍ መሆን

## ክፍል አምስት

1. ከ586 ዓ.ዓ. በኋላ
2. ኢየሩሳሌምን አዳናት
3. በውስጡ የሚገኘው ታሪክ የትም ቦታ ስለማይገኝ
4. ወደ ግብፅ ስለሄዱት ሰዎች
5. የኢየሩሳሌም መደምሰስ ታሪክ
6. የባቢሎን
7. ወደ ግብፅ
8. በናቡከደነፆር የተሾመ የአይሁድ መሪ
9. ዮሐናን
10. በምጽጳ
11. ዮሐናን
12. ወደ ግብፅ
13. በ568 ዓ.ዓ. ገደማ
14. የባዕድ መሥዋዕቶችን መሠዋት
15. ለባሮክ
16. እንደሚፈርድበት
17. ኤር. 42
18. ስለ ጎዶልያስ መገደል
19. ወደ ግብፅ እንዳይሸሹ ነበር
20. በግብፅ እስረኛ ሆኖ

## ክፍል ስድስት

1. በግብፅ
2. ታሪክ አዘል ስላልሆነ
3. ዓሞን፣ ምናሴ
4. በ39 ዓመቱ፣ በ609 ዓ.ዓ.
5. 2ኛ ነገ. 22-23ና 2ኛ ዜና 34-35
6. ከልብ የተደረገ አለመሆኑን ስለተገነዘበ ሊሆን ይችላል።
7. ከእግዚአብሔር ጋር የገቡትን ውል ስላፈረሱ
8. ካህናትና ነቢያትም በሙሉ ናቸው
9. ሀ. በዚህ ወቅት ንጉሥ የነበረው ኢዮስያስ ንስሐ እንዲገቡ አስገድዶአቸው ስለነበረና

   ለ. እግዚአብሔር በማይታዘዝ ሕዝብ ላይ የሚያመጣው ፍርድ የማይቀር መሆኑን በቅድሚያ መገንዘብ ስለነበረባቸው።
10. በዚህ ወቅት ኢዮስያስ መነቃቃት አስነሥቶ ስለነበር
11. ኢዮስያስ በመጊዶ ከመገደሉ ሦስት ዓመታት በኋላ በ612 ዓ.ዓ.
12. ፍርድ
13. እምነተቢስነት
14. ከእነርሱ ጋር ቃል ኪዳን ስለመሠረተ
15. የከነዓናውያንን ሃይማኖት
16. ወደ እግዚአብሔር መመለስና ይቅርታ መቀበል
17. እግዚአብሔር ራሱ
18. ከእነርሱ ጋር የገባውን ቃል ኪዳን በመጣስ
19. የማይሻረውን ዘለዓለማዊ የእግዚአብሔርን ቃል

## ክፍል ሰባት

1. ምናሴና ዓሞን
2. በምናሴ ዘመነ መንግሥት
3. አሞር
4. አሞርን ይጠላ ስለነበር
5. ከባቢሎን
6. ፈርዖን
7. ንስሐ መግባትን የያዘ ነው
8. ሐሰተኛ ሃይማኖት መከተል
9. እግዚአብሔር ከእያንዳንዱ ግለሰብ ይጠብቅ የነበረው መልስ
10. ሕዝቡን ወደ ንስሐ ለማምጣት
11. ቅድስና
12. በከፍተኛ ደረጃ መዋረዳቸው
13. በሕዝቡ ኃጢአት ውስጥ ተዘፍቀው ነበር
14. ባጠቃላይ የተበላሸ መሆኑን
15. ምዕ. 10
16. እናቶች
17. ባሕርይና ፍርድ
18. በመምጣት ላይ የነበረ ፍርድ
19. ዘወትር የመጀመሪያውን ሥፍራ
20. በኃጢአት

## ክፍል ስምንት

1. በአምስት
2. ኢዮስያስ
3. ለሦስት ወራት፥ ወደ ግብፅ ተወሰደ
4. 605 ዓ.ዓ.
5. ኢዮአቄም
6. በ598 ዓ.ዓ.
7. በ597 ዓ.ዓ.
8. ልጁ ዮአኪን
9. በ13ኛው ዓመት
10. በ640 ዓ.ዓ.
11. ከይሁዳ ኃጢአት የተነሣ
12. የእግዚአብሔርን ፍቅር ሊያሳያቸው
13. አልቻለም፤ እንዳውም የተመረጡትን ከባቢሎናውያን ምርኮ ጠርቶአቸዋል
14. ኤር. 13፡8-11 ተመልከት
15. ሕዝቡ አውንም ንስሐ አልገባም አለ፤ ሐሰተኛ ነቢያትንም ተቀበለ
16. ኤር. 15ን እንደገና አንብብ
17. ሚስት ባለማግባትና በቀብር ሥነ ሥርዓት ላይ ባለመገኘት
18. ሰንበትን በማክበር፤ ኤር. 17ን አንብብ
19. እግዚአብሔር በምርኮው አማካይነት አዲስ ሕዝብ እንደሚፈጥር
20. ሕዝቡ ከኤርምያስ የተላለፈላቸውን መልእክት አንቀበልም አሉ።
21. ትንቢቶችና ድርቅን የመሳሰሉ ፍርዶች
22. በሰፈው የተዘረዘሩት ከፉ ድርጊቶች

## ክፍል ዘጠኝ

1. ኢዮአክስ፡ ኢዮአቄምና ሴዴቅያስ
2. ግብፅ ከባቢሎን ጋር ትዋጋ ነበር
3. ባቢሎን ግብፅን ድል አደረገች፡ ኢዮአክስ እስረኛ ሆኖ ወደ ግብፅ ተወሰደ፡ ናቡከደነፆር ኢየሩሳሌምን መረረ
4. ዮአኪን
5. ኢዮአቄምና ሴዴቅያስ
6. በሕዝቡ መሪዎች ላይ
7. ከነቢያቱ በአንዱ አማካይነት መናገር
8. ሕዝብ ከምርኮ ይመለሳሉ
9. የሞት ሽለቆ የሚል ነው
10. ጳስኮር
11. ከዚህ የተለየ መልእክት ልታመጣልን አትችልም
12. ኢዮአክስ፡ ኢዮአቄምና ዮአኪን
13. ካህናትን
14. በባቢሎን ያሉት ሰዎች በኢየሩሳሌም ካሉት ይልቅ የተሻለ ተስፋ እንዳላቸው የሚጠቁም ነው
15. ፍርድ
16. ነቢያት፡ ካህናትና ነገሥታት
17. የእግዚአብሔር ቃል
18. እግዚአብሔር ስለማይታዘዘውና ዓመፀኛ ሕዝብ ምን ያህል እንደተሰማው እንዲገነዘቡ ለማድረግ

## ክፍል አሥር

1. ስለ ኤልያስና ኤልሳዕ
2. ኢሳይያስ
3. በኢዮአታም፡ አካዝና ሕዝቅያስ ዘመነ መንግሥት
4. ምናሴ
5. ኢዮስያስ
6. ኤርምያስና ሶፎንያስ
7. በ606፥ በ597 ና በ586 ዓ.ዓ.
8. ሕዝቅኤልና ዳንኤል
9. ሕዝብ በቃል ኪዳኑ ላይ ስለሚሠሩት ኃጢአት
10. በ722 ዓ.ዓ.
11. በ612 ዓ.ዓ.
12. በባቢሎን
13. እጃችሁን ለባቢሎናውያን ሰጥታችሁ ዳኑ፤ ከምርኮው በኋላ ቅሬታ ሕዝብ ተመልሶ ይመጣል
14. በዘሩባቤል፥ ዕዝራና ነህምያ ዘመን
15. መጽሐፍን በአጠቃላይ በአጭሩ ለመመልከት
16. የኤርምያስን ጥሪና አጭር ታሪካዊ ማጠቃለያ
17. ስለ ኢዮአቄም
18. ስለ ቤተ መቅደሱና ቃል ኪዳኑ የተደረገ ሙግት
19. ከ586 ዓ.ዓ. በኋላ ስለተፈጸሙት ድርጊቶች
20. ሙግት፥ የተሰፋ ቃሎች፥ ጥርጥርና ጥፋት
21. የሥነ ምግባር ግዴታዎች እንዳሏቸው / እግዚአብሔርን መታዘዝ እንዳለባቸው/
22. በአሦር
23. ከ627-586 ዓ.ዓ. - ለ 40 ዓመታት ያህል

24. ተማሪዎች ከሰጡት መካከል ትክክለኛውን መልስ ይመሰድ
25. ናቡከደነፆር
26. ነቢያትን በመላክ
27. አይሻርም፤ ነገር ግን ሊያዘገየው ይችላል
28. ወደ ባቢሎን ተወስደው ከነበሩት ሰዎች መካከል
29. የእግዚአብሔርን ታማኝነት
30. በጸጋ
31. መታዘዝ
32. ጻድቅ መሆኑን ለመግለጽና ከእርሱ ርቀው የሄዱትን ሰዎች ወደ ራሱ ለመለስ
33. እርሱን የሚያገለግል ሕዝብ መልሶ ለማቋቋም ሲል ነው።